# ባለራእይነት



## ክፍል 1
## Vol. 1

ለራእይዎ
ስኬት መልካምን
በመመኘት የተበረከተ

ከ ________________________

ለ ________________________

# ባለራእይነት

ፀጋአብ በቀለ

ታኅሣሥ 2004 ዓ.ም
ሐዋሳ

Copyright©2011 – Tsega-Ab Bekele
All right reserved

አዘጋጅና አሳታሚ
ፀጋአብ በቀለ

አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር መጽሐፉን በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛትና ማሠራጨት በሕግ የተከለከለ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከመጀመሪያው እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የዘመን አቆጣጠር በተመለከተ ለአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር (እ.ኤ.አ) በማለት የኢትዮጵያን ዘመን አቆጣጠር ለማመልከት ደግሞ (ዓ.ም) በማለት ተለያይተዋል።

For more information

Email: gfuntb@yahoo.com Mobile: +251916824930
P.O.Box 1077, Hawassa, Ethiopia.

የሽፋንና የገጽ ዲዛይን:- ዘካርያስ ግርማ
ሞባይል:- 0911945840

# አበርክቶት

ይህ መጽሐፍ ባለፈው መልካም የታሪክ ገጽታችን ለሚኮፈሱና በመጥፎው ደግሞ ለሚከፉ ሳይሆን ያለፈውን እምንታዊ ሆነ አሉታዊ ታሪካችንን እንደ መስፈንጠሪያ በመጠቀም በመጪው ዘመናት ከራስ በላይ ትልልቅ ራእይን ሰንቆ በመነሣት ሁለንተናዊ ለውጥና ዕድገት በማምጣት ለሀገርና ለዓለም በረከት ሊሆን ራሱን ለሰጠ ለዚህ ባለራእይ ትውልድ በታላቅ ትሕትና አበረክታለሁ።

# አስተያየት

ዓለም አቀፋዊ፣ ሀገራዊ፣ ቤተ ክርስቲያናዊ፣ ቤተሰባዊና ግለሰባዊ ገጽታዎች በመዘበራረቃቸው ግራ መጋባት በነገሠበት በዚህ ዘመን «ባለራእይነት» የተሰኘችው መጽሐፍ በትውልዱ ልብና አውድ ለአዎንታዊ ለውጥ ታላቅ ንቅናቄን የሚፈጥር መልዕክት ይዛ ብቅ ብላለች፤ያንብቡአት።

ዶ/ር ሀብታሙ ከድር (Ph.D.)
የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
የኮሚዩኒኬሽንና የሥነ ጽሑፍ መምሪያ ኃላፊ

ወንድሜ ፀጋአብን ከአሥር ዓመታት በፊት በሕይወት መጽሔት ላይ ያስተላልፋቸው በነበረው ጠንካራ ጽሑፎቹ አውቀዋለሁ። ዛሬም ይህን በራእይ ሽክማችን ላይ ያተኮረ ጠንካራ ሥራ አቅርቦልናል። በበርካታ መረጃዎች የታጨቀ፣ የምርምር ውጤቶች የቀረቡበት፣ በጠንካራ አገላለጾች የተገነባ፣ የብዙ ምሁራን አስተያየት የተካተተበት፣ የሥነ ጽሑፍ ውበትን ከይዘቱ ጥንካሬ ጋር አጣምሮ የቀረበ መጽሐፍ ነው። በሀገራችን በዚህ መልክ የተዘጋጁ ጥቂት መጽሐፍት ናቸው። እያንዳንዳችን ውስጣችንን እንድንፈትሽ በብዙ ይረዳናል። እኔም ተጠቅሜበታለሁ። የበቃ ሥራ ነው።

ደረጄ አበበ
የወንጌል ብርሃን ቤተ ክርስቲያን ኮሚዩኒኬሽን ክፍል ኃላፊ
የካቦድ መጽሔት አዘጋጅ።

ባለራእይ አፍራሽ አብዮተኛ፣ ራእይ ለቤተ ክርስቲያን አደጋ ተደርጎ በአንዳንድ መሪዎች በሚቆጠርበት ወንጌላዊያን አማኞች ማኅበረሰብ መካከል ሆኖ ራእይን የሚያበራ፣ ባለራእይን የሚያበረታታ፤ ራእይ ሰጪውን የሚያጎላ እንደዚህ ያለ መጽሐፍ ታትሞ እንደሆን ለእኔ የወ/ዊ ፀጋአብ በቀለ «ባለራእይነት» ብቻ ነው። መጽሐፉ በበርካታ እውነቶች የተሞላ ከመሆኑም በተጨማሪ ከአቀራረቡ ሳቢነት የተነሣ ያነበብኩት በትልቅ ጉጉት ነው። ተጠቅሜበታለሁ። ይህ መጽሐፍ ደራሲው ለአዲሱ ትውልድ ያበረከተ ውድ ስጦታ ነው። አንብቡት።

ዶ/ር ተሾመ አየለ ሮማ (Ph.D.)
የምሥራች ለሕዝብ ሁሉ ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን
ልዩ ስልጠና ማዕከል ኃላፊ

«ባለራእይነት» መጽሐፍ ክርዕሱ ባለፈ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን መሠረት ያደረገ፣ በመንገዱ ተፈትነው በፍሬአቸው ትውልድን በጽድቅ ኖረው የከነኑ ሰዎችን ታሪክ በዋቢነት ያካተተና እንዲሁም ጸሐፊውን በቅርብ እንደማውቀው ሀሳባዊ ወይም አዕምሮአዊ መረጃ ብቻ ሳይሆን በተግባር የተፈተነ ባለራእይነቱን በማካፈል በእያንዳንዱ መቋጫ ላይ ዘመን ተሻጋሪ መርሆዎችን ያስጨብጣል:: በአጠቃላይ መጽሐፉ አቋምን ፈታሽ፣ ሕይወትን ሞጋች፣ አቅጣጫን አመልካችና እግዚአብሔርን የሁሉ ምንጭነቱን በማሳየት ትውልድ ባለራእይ እንዲሆን የሚጣራ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: በመሆኑም ይህ ለዘመኗ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ስጦታ ነው ብዬ አምናለሁ:: ስለዚህ መጽሐፉን ሁሉም ቢያነብ ያተርፋል::

መብራቴ መሰለ (መጋቢ) /B.Th/
የሐዋሳ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

«ባለራእይነትን» ሳነበው ይሞግታል፣ ያበረታታል፣ ይገስጻል፣ የልብ ጫካዎች ላይ እያበራ ያለፈውን፣ አሁን ያለንበትንና መጪውን የሕይወት ጉዞ በባለራእይነት ዓይን እንድንቃኝ ያስገድደናል:: ከታዛብነት ወደ ታሪክ ሠሪነት እንድንሸጋገር መንገድ ያሳያል:: ሕሊናውን ላልሸጠ ሰው አካሄድንና ዕጣ ፈንታን መማሪያ ቤተ መጻሕፍት ነው::»

ደረጀ ሙላት (ዘማሪ) የተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ

ፀሐፊ፣ አስተማሪ፣ መሪና ጥሩ ተናጋሪ ፀጋአብ የባለራእይነትን እውነት ይተነትናል፣ ባለራእይ ነውና ያለ ራእይም እንደማይሆን ገብቶታልና የልቡን መቃተት ጻፈው - አስተማረው:: እኔን በብዙ ረድቶኛል::ያንብቡት! ያልተጭበረበረ ራእይ ይኖርዎት ዘንድ ይረዳዎታልና::

ሙሉጌታ ደምሴ (M.A)
ሰባኪ፣ አስተማሪና አሰልጣኝ





በአብያተ ክርስቲያናት በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ያሉ አገልጋዮችን ብቻ ሳይሆን ከግለሰብ አንሥቶ በፖለቲካና በማኅበራዊ አገልግሎት አመራር ላይ ላሉትም ሁሉ የመሪነትን አቅም የሚያሳድግ የዳበረ ግብዓት በዚህ መጽሐፍ አይቻለሁ:: ለአዲሱ ትውልድ ወደ ትክክለኛ ግብ የሚያደርስ፣ ለማያዊ ራእይ ለንቆ እንዲነሣ የጥሪ ደወል የሚያስተጋባ፣ መለኮታዊ እምነትና ድፍረት በአንባቢው ልብ የሚጭር መሣሪያ ሆኖ አግኝቸዋለሁ::

ዳቃ ጅሎ (M.A)
የቀድሞ አርባ ምንጭ ተግባረ ዕድ ት/ቤት ዳይሬክተር

ራእይ «በሰው እጅ ሲያዩት ያምር ሲይዙት ያደናግር» ዓይነት ነገር ነው:: ሆኖም ግን ይጨበጣል፣ ይለመዳል፣ ይኮናል:: እናም ይኼ መጽሐፍ ራእይን ያስጨብጣል፣ ያስለምዳል፣ ያስኮናል:: ስለዚህም ግለሰብና ሕዝብ፣ መሪና ተመሪ፣ ቤተ ክርስቲያን ብሎም ሀገር «መረን» እንዳይሆኑ ያግዛል::

እሸትአየሁ ክንፉ /M.A, CPM/
የሐዋሳ ዩንቨርስቲ መምህር

ይህን «ባለራእይነት» የሚል በዓይነቱ ልዩ የሆነ መጽሐፍ ደጋግሜ ያነበብኩት በትልቅ ጉጉትና ልባዊ ፍቅር ነው:: መጽሐፉን ሳነብ የተለያየ ዓይነት ስሜት ጭሮብኛል ንደት፣ ቁጣ፣ ሣቅ፣ ቁጭት፣ ለቅሶ፣ ተስፋ ... ሲሆን አሁን ካለሁበት የአገልግሎት ሕይወት ተዛማጅ፣ አቀራረቡ ሁሌንተናዊ፣ መልዕክቱ ወቅታዊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: ማንም ሰው በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በፖለቲካ አቋም፣ በኑሮና በትምህርት ደረጃና በሙያ ልዩነት ሳይገደብ ይህን መጽሐፍ ቢያነብ ለሁለንተናዊ የሕይወት ለውጥ ዘመን ዘለል ምክር ያገኝበታል:: እባካችሁ መላልሳችሁ አንብቡ::

ታከለ ሲግሶ
የቀድሞ ምዕራብ አርሲ ዞን ወ.አ.ክ.ን ሰብሳቢ
በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ወንጌልን በመስበክና በማስተማር ላይ ሚገኝ::

## ማውጫ

*መግቢያ*

*ምስጋና*

**ክፍል አንድ ፡- የመንፈሳዊ ራእይ ምንነት?**

1. ራእይ ምንድነው? - - - - - - - - - - - - - - - 11
2. የራእይ ጥቅሞች - - - - - - - - - - - - - - - - 29
3. ራእይን እንዴት እንቀበላለን? - - - - - - - - - - -42
4. ራእያችን ከእኛ በፊት ነበር! - - - - - - - - - 61
5. ራእይ ወይስ ልምድ? - - - - - - - - - - - - - -72
6. የራእይ ገዳዮች - - - - - - - - - - - - - - - 82
7. የራእይና የባለራእይ ባሕሪያት - - - - - - - - - 106

**ክፍል ሁለት፡- ዓለምን የለወጡ ባለራእዮች**

8. ዓለምን ያዳነ ባለራእይ - - - - - - - - - - - - 128
9. ሀገርን የታደገ ታናሹ ባለራእይ - - - - - - 153

**ክፍል ሦስት፡- ዘመናችን ባለራእዮች**

10. ልቤን በአፍሪካ ቀበሩ - - - - - - - - - - - - - - -167
11. አውሮፓን እያነጋገረ ያለ አፍሪካዊ - - - - -180
12. አፍሪካን እያነጋገረ ያለ አውሮፓዊ - - - - -192
13. እኔም ራእይ አለኝ - - - - - - - - - - - - - - 208

ማጠቃለያ - - - - - - - - - - - - - - - - - - - 219

ዋቢ መጽሐፍት - - - - - - - - - - - - - - - - 222





## መግቢያ

### *«አንተ ወጣት ቁጭ በል! »*

*«አንተ ወጣት ቁጭ በል! እግዚአብሔር በወንጌል ያልተደረሰውን ዓለም ለመድረስ ቢፈልግ እኔንና አንተን አያማክርም::»* ያሉት ዶክተር ጆን ሲ. ራይላንድ በኢንግላንድ እ.ኤ.አ በ1780ዎቹ የአንድ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ መጋቢ ነበር:: መጋቢው ይህን ከባድ የተግሳጽ መዶሻ ያነሣው በአገልግሎቱ ትልቅነትና ባመጣው አዎንታዊ ተጽዕኖ «የዘመናዊው ሚስዮን አባት» የሚል ቅጽል ስም ለተሰጠው በዊልያም ኬር ራእይ ላይ ነበር:: ዊልያም ኬር መጋቢው በጉባኤ ፊት የሰነዘረበት አደገኛ ተግሳጽና ተቃውሞ ቃል አልሰበረውም፣ አላሸበረውም፣ተስፋ አላስቆረጠውም፣ አላስቆመውም::

አንድ ሰው እንዳለው «ተቃውሞ አንዳንዶችን ሲሰብራቸው ሌሎችን ሪከርድ እንዲሰብሩ ያደርጋቸዋል::» ኬር የተቃውሞን ጉልበት በራእይ ኃይል ሰብሮ በማለፍ ለትውልድ ሁሉ ምሳሌ የሚሆን አንጸባራቂ ሥራ ሠርቶ አልፎአል:: ትልቅ ራእይ ካለህ ለትልቅ ተቃውሞ ተዘጋጅ! ተቃውሞው ከሰይጣን ብቻ ሳይሆን ኢየሱስን ወንድሞቹ «አላመኑበትም» የገዛ ወገኖቹ «አልተቀበሉትም»፣ ዳዊትን ታላቅ ወንድሙ በራእዩ መንገድ ላይ አይቶት «ትዕቢተኛ»፣ ዮሴፍን ወንድሞቹ «ስለ ሕልሙ ይልቁኑ ጠሉት» አባቱም «ገሰጸው» እንደሚለው፣ ጳውሎስ ራእይውን ይዞ መጀመሪያ ወደ ኢየሩሳሌም የበጉ ሐዋርያቶች ወዳሉበት ቤተ ክርስቲያን በመጣ ጊዜ ለማመን እንደተቸገሩ አንተንም «ይረዳኛል» የምትለው የቅርብ ሰው ራእይህን ስትነግረው ላይረዳህ ይችላል:: ዋናው ጉዳይ ግን *«አልፈህ ለመሄድ አቅም አለህ ወይ?»* የሚለው ነው::

ከጌታ የተቀበልኩት የአገልግሎት አቅጣጫ በተለይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለተግባራዊ አገልግሎት ማስታጠቅ አንዱ ነው:: ለዚህም አገልግሎት ጸጋው ረድቶኝ ያዘጋጀሁት የመማሪያ ጽሑፎች በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እጅ የሚገኝ ሲሆን ከእነዚያ ውስጥ «ባለራእይ መሪ» በሚል ባለፋት 5 ዓመታት

በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከ7000 የሚበልጡ በቤተ ክርስቲያን፣ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በመሪነት በማገልገል ላይ ያሉ መሪዎች ስልጠናውን ወስደዋል:: በስልጠናው ላይ የተካፈሉና ባሉበት ቦታም ትምህርቱን በማስተማር ላይ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ትምህርት በብዙ እንደተጠቀሙበት በቃልና በጽሑፍም ሁሌ ይገልጹልኛል:: በመጽሐፍ መልክ ለሁሉ ቢቀርብ የብዙዎችን አመለካከት በመለወጥ ረገድ ትልቅ እገዛ እንደሚኖረው ተደጋጋሚ አስተያየት ሰጥተውኛል:: በመጨረሻም መልዕክቱ የትውልዱ መሆኑን ስላመንኩ በመጽሐፍ መልክ ቀርቧል:: *«ባለራእይነት»* በሚል ርዕስ የተዘጋጀው የመጀመሪያ መጽሐፌ ሊወለዱ ላሉት ለብዙ መጽሐፎች በኩር ነው:: ለእግዚአብሔር ክብር፣ ዓለም አቀፋዊ ራእይ ሰንቀው የተለመደውን ድንበር ጥሰው የሚያስጥሱ ከምድራችን እንዲነሡ ባለኝ ልዩ ሸክምና ጸሎት ለትውልዱ በትህትና የቀረበ ነው::

ባለራእይነት በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ሁለት ተከታታይ መጽሐፎች ጌታ ረድቶኝ በአንድ ላይ ተጠናቀዋል:: የመጀመሪያው መጽሐፍ የመንፈሳዊ ራእይ ጽንሰ ሐሳብ በመተንተንና ምሳሌ ሊሆኑልን በሚችሉት ባለራእዮች የሕይወት ተሞክሮ ላይ ልዩ ትኩረት በማደረግ ያውጠነጥናል:: ሁለተኛው መጽሐፍ የኢትዮጵያ ክርስትና ከየት ወዴየት? በማለት ያለፈውን፣ ያለውንና የሚመጣውን ዘመን ለማስቃኘት ይጥራል፤ ባለራእይነት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምን እንደሚመስል ያስቃኛል፤ እንደ ዕድሜያችንና እንደ ታሪካችን ዓለም አቀፋዊ ራእይ ያላቸው ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያልተነሱበትን ምክንያቶች ይተነትናል፣ የአመለካከትና የአሠራር ለውጥ እንዲመጣ ይሞግታል፣ የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ምን እንደምትመስል ፍንጭ ይሰጣል፣ ዕድልና አደጋዎችን በማመልከት ለትውልዱ ምርጫውን ይተዋል:: ይህ የመጀመሪያው መጽሐፍ በሦስት ክፍል የተከፈለ አሥራ ሦስት ምዕራፎች አሉት::





ክፍል አንድ በውስጡ ሰባት ምዕራፎች ይዟል:: እነርሱም የመለኮታዊ ራእይ ምንነት፣ የራእይ ጥቅሞች፣ ራእይን እንዴት እንደምንቀበል፣ አሁን እየተመራንና እየኖርን ያለው በልምድ ወይስ በራእይ? ብሎ በመጠየቅ፣ የራእይን ገዳዮች በስፋት ከዳሰሰ በኋላ በሰባተኛው ምዕራፍ ወሳኝ የሆኑ የራእይና የባለራእይ ባሕሪያትን ይዳስሳል:: ክፍል ሁለት ዓለምን የለወጡ ባለራእይዎች በሚል ዋና ርዕስ ሥር ሁለት ምዕራፎች ይገኛሉ:: በዚህ ክፍል ያሉ ሁለቱም ምዕራፎች ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን ምሳሌ ሊሆኑልን የሚችሉ አንዳንድ ባለራእዮች ከሰማይ ምን ዓይነት ራእይ እንደተቀበሉና በምን ውስጥ አልፈው ራእያቸውን እንደተገበሩ ለትምህርታችን በሠፊው ቀርቦአል:: ባለራእይነት ከስም ያለፈ ምን ዓይነት የሕይወት፣ የባሕሪይና የአመለካከት አቋም እንደሚጠይቅ ለመዳሰስ ተሞክሮአል::

ክፍል ሦስት ዘመነኞቹ /contemporary/ ባለራእዮች በሚለው ሀሳብ ሥር አራት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ልቤን በአፍሪካ ቅበሩ ያለው ባለራእይ፣ በዘመናችን ጋዜጠኝነትን ለማጥናት ወደ ራሽያ ሄዶ አውሮፓን እያነጋገረ ያለው ታላቅ የዘመናችን አፍሪካዊ ባለራእይ፣በአሥር ዓመት 60 ሚሊዮን ሰዎች ወደ ጌታ ስለ ሰበሰበው ባለራእይ፣ ስለገጠማቸው ታላላቅ ተግዳሮቶች፣ ስላስመዘገቡት ታላላቅ ድሎችና በዓለም ላይ እያመጡ ስላለው አዎንታዊ ተጽዕኖዎች ለትምህርታችን በዝርዝር ቀርቦአል:: የዚህ ክፍል መጨረሻ ምዕራፍ «እኔም ራእይ አለኝ» በምል ርዕስ ሥር ስለ ሌሎች በማውራት ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ ለመሆን ካለኝ ልባዊ ፍላጎት በትንሹ የአገልግሎት ሕይወቴ ያየሁትን የራእይን ጉልበትና የእግዚአብሔርን ታማኝነት ለአንባቢዎቼ አቅርብያለሁ::

**መልካም ንባብ**

***ፀጋአብ በቀለ (ወ/ዊ)***
*የጎስፒል ፎር አንርችድ ኔሽንስ ሚኒስትሪ*
*መሥራችና ዳይሬክተር*
*ሀዋሳ 2004 ዓ.ም*

# ምስጋና

በዘላለማዊ ዕቅዱና ፈቃዱ በራሱ ጊዜ ወደ ምድር ለውስን ዘመንና ዓላማ ያመጣኝን የነፍሴ መገኛ፣ መዳኛና መሪ አምላክ ከልቤ አመሰግነዋለሁ::

የትዕግሥት፣ ጽናትና ዝቅ ብሎ ማገልገልን በመሆን ሁሌ የምታስተምረኝ በጣም የምወዳትና የማከብራት ባለቤቴን ቲያ ዳቃ የምንሳሳለቸው ልጆቻችን ትሁት ፀጋአብ፣ ሩት ፀጋአብ፣ ምናሴ ፀጋአብና ልዕልት ፀጋአብ ያለ እነርሱ ጸሎትና ፍቅር ማገልገልም ሆነ ይህን መጽሐፍ መጻፍ ለብቻዬ አይታሰብም:: ጌታ ይባርካችሁ:: እናቴ ዓለሚቱ ወ/ገብርኤል በብዙ ድህነት፣ ብቸኝነትና ያለመቻል ተስፋ ሳትቆርጪ እኔን ለማሳደግ የከፈልሽውን ዋጋ መመለስ ባልችልም «በጌታ ነገ ሰው ልትሆን ትችላለህና በርታ» የሚል የምክር ቃልሽ ዛሬም በልቤ ሕያው ነው:: ትጋትና ለአሉታዊ ሁኔታዎች እጅ ያለ መስጠትን ካንቺ ተምሪያለሁ:: ዕድሜሽ ይለምልም::

የዚህ መጽሐፍ ረቂቅ አረም የበዛበት እርሻ ይመስል ነበር:: እንደ ትጉህ ገበሬ የሰላ ብዕራቸውን አንግበው አሰልችውንና አስቸጋሪውን የማረም ሥራ ለመሥራት ራሳቸውን የሰጡ ወገኖች ብዙዎች ናቸው:: ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህል እሸትአየሁ ክንፉ፣ ዳቃ ጅሎ፣ መጋቢ መርዓዊ ሥላሴ ንጉሤ፣ ዶ/ር ፋስል ናሆም፣ ለሊሳ ዳንኤል፣ ወንጌላዊ ወንድሙ ማቴዎስ፣ ዘማሪ ደረጀ ሙላት፣ ሙሉጌታ ደምሴ ፣ ደረጀ አበበ፣ ታከለ ስግሶ፣ መጋቢ መብራቴ መስለ፣ ዶ/ር ተሾመ አየለ፣ ዶ/ር ሀብታሙ ከድር ከእናንተ ብዙ ተምሪያለሁ:: በአንባቢያን ስም ላመሰግናችቸሁ እወዳለሁ:: እግዚአብሔር ይባርካችሁ::

በጌታ ሥራ የተጠመደው አሜሪካ ያለው መንፈሳዊ ልጄ አሊ ኤልያስና እይታው ትልቅ የሆነ ታናሽ ወንድሜ ዳራራ ጢሞቴዎስ ከእኔ ይልቅ ከጌታ ስለተቀበልኩት አገልግሎት ያላቸውን መሰጠትና ትጋት ስመለከት ሁሌ ስለ እነርሱ ጌታን ለማመስገን እገደዳለሁ:: በወሳኝ መረጃ የታጨቁ ዳጎስ ያሉ መጽሐፎችን አቀብለውኛል:: ሊናገረው ከሚችለው በላይ ልቤን በብዙ አሳርፈዋል:: ከልብ አመሰግናችኋለሁ::





«ይህ መልዕክት በአስቸኳይ ለትውልዱ መድረስ አለበት» በማለት ለዚህ መጽሐፍ ሕትመት በገንዘባቸሁ ከእኔ ጋር የቆማችሁ ቅዱሳን ጌታ ለዘላለም ይባርካችሁ:: ያለ እናንተ እገዛ ይህ ትልቅ ውጤት እውን አይሆንም:: በዚህ አጋጣሚ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በምክር፣ በጸሎትና በገንዘባችሁ ላለፉት ሰባት ዓመታት የእግዚአብሔርን መንግሥት ከእኛ ጋር በማስፋፋት ላይ ያላችሁ ቅዱሳን የወንጌል አጋሮቻችን ጌታ ይባርካችሁ:: ይህ መጽሐፍ የፀሎታችሁ፣ የምክራችሁና የልግስናችሁ ውጤት ነው:: እንኳን ደስ አላችሁ:: በአርክ ክርስቲያን ሰርቪስ ባሳለፍኩት ጥቂት ጊዜ ብዙ ለሕይወቴና ለዚህ መጽሐፍ ግብአት የሆኑ ቁም ነገሮችን ገብይቻለሁ:: ጌታ ይባርካቸው::

የእርሚ ባይብል ኮሌጅ ተማሪዎችና «የለውጥ መሪ ሥልጠና» ተካፋዮች ለሕይወቴ ትልቅ ትምህርት ቤት ሆናችሁኛል:: በዚህ መጽሐፍ የእናንተ ቀጥተኛ እጅ አለበት:: በተጨማሪ ከጌታ ስለ ተቀበልኩ አገልግሎት የምትማልዱና ከእናንተ ጋር ወንጌል ይዤ እንድወጣ ዕድል የሰጣችሁኝን የጎስፒል ፎር አንርችድ ኔሽንስ ሚኒስትሪ ሠራተኞች፣ የምልጃ ጸሎት ግብረኃይልና የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች ሁሌ ስለ እናንተ ሳስብ ድካሜን እረሳለሁ:: ሁላችሁንም ከልብ እያመሰገንኳችሁ፣ ጌታ ይባርካችሁ ለማለት እወዳለሁ::

# ክፍል አንድ

## የራእይ ምንነት?

*«ለብዙዎቻችን አስቸጋሪ የሆነው ሊሰወርብን የማይችለውን ትልቅ ራእይ ማየት ሳይሆን ጥቃቅን ከመሆናቸው የተነሣ ለማየት አዳጋች የሆኑ ነገሮችን ለማየት መንጠራራታችን ነው።»*

*ማይክል ጆን*

# 1 ራእይ ምንድነው?

*«መለኮታዊ ራእይ ነገሮችን እንዳሉ ማየት ሳይሆን እግዚአብሔር እንደሚያይ ነገሮችን የማየት አቅም ነው።»*

እ.ኤ.አ በ1833 በዋሽንግተን ዲሲ አዳዲስ የአዕምሮ ሥራ ውጤት ባለቤትነት /patent/ ምዝገባ ቢሮ ሠራተኛ የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ ስጽፍ «በሰው ልጆች አዕምሮ ሊፈጠሩ የሚችሉ አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎች ሁሉ ስለተፈጠሩ ከዚህ በኋላ ይህ ቢሮ ምንም አይነት ሥራ ስለማይኖረው በጊዜ ሌላ ሥራ ለመፈለግ እንድችል እንድታሰናብቱኝ አመለክታለሁ።» ሲል እርሱ ዴብዳቤውን በጻፈበት ጊዜ በቢሮው ከ5000 በታች የፈጠራ ሥራዎች ብቻ የተመዘገቡ ሲሆን እርሱ ይህን ደብዳቤ ከጻፈ ከስድት ዓመት በኋላ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት 600,000 ዛሬ ከ6,000,000 / ከስድሰት ሚሊዩን/ በላይ እንደተመዘገቡና በየዓመቱ ከ600,000 በላይ የፈጠራ ሥራዎች በዓለም አቀፍ አዕምሮአዊ ንብረት ቢሮ /WIPO/ ለምዝገባ እንደሚቀርቡ መረጃዎች ይጠቁማሉ።[1] ከላይ የተመለከትነው ግለሰብ የራእይ እጦት ወደ ተሳሳተ ድምዳመና እርምጃ እንዳመራው እንመለከታለን። ሩዝቬልት «መጭው ዘመን በሕልማቸው ውበት ለሚያምኑ ሰዎች ነው» እንዳሉት ዓለም የባለራእዮች ናት። በዓለማችን ራእይ ለግለሰብ፣ ለሀገር፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለንግድ፣ ለመንግሥታት፣ ለተለያዩ ድርጅቶችና ተቋማት ፍሬያማነት፣ ምጥቀትና ዕድገት መሐሰቅነቱ ታምኖበት፣ በስፋት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መነገርና መጻፍ የተጀመረው እ.ኤ.አ ከ1980ዎቹ ወዲህ እንደሆነ መዛግብቶች ያመለክታሉ።[2]

[1] http://www.wipo.int/export/sites/www/ipstats/en/statistics/patents/pdf/wipo_pub_943
[2] *Barna Gorge, the power of vision, published by Regal, USA, 1992.p.6*

*ያሉትን እውነት  የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊም ይጋራል::*  ያለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን «የመረጃ ዘመን» /Information era/age/ ተብሎ ይታወቃል:: ኢንቴርነት፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ፋክስ፣ ቴሌፋክስ፣ ፌስ ቡክ፣ ቲውተር፣ ዩቲዩቢ፣ ቴሌ ኮንፈራንስ በአገልግሎት ላይ መዋል ዓለም እንደ አንድ መንደር /Global village/ እንድትቆጠር አድርጓታል:: ዛሬ በማንኛውም የትምህርት መስክ በአፍሪካ ጫካ ውስጥ ሆነን ከአሜሪካ ወይም ከአውሮፓ ዮንቨርስቲዎች በኮምፒዩተር /online/ ላይ በመሥራት ከሰርትፍኬት እስከ ፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ መውሰድ መቻላችን ዘመናችን ምን ያህል የእውቀት መረጃ ፍሰት እንዳለ ያመለክታል:: ጄምስ ጋሊስ በመጽሐፋቸው እ.ኤ.አ ከ2000 ወዲህ ብቻ በዓለም ላይ ስለመጣው የዕውቀት ብልጫ እንዲህ ይገልጻሉ:-

*«እ.ኤ.አ ከ2000 ወዲህ የዓለማችን ዕውቀት በየ18 ወራት እጥፍ እያደገ እንደሆነ ያውቃሉ? ከዚያ በፊት በነበሩ ዘመናት ግን በአምስት አመት እንዴ ያድግ እንደነበር ይህን ስምተዋል? ከቀደሙት 5,000 ዓመታት ይልቅ ባለፉት 30 ዓመታት ብቻ በዓለም የተገለጠው ዕውቀት ይበልጣል:: በዓለም ላይ ያሉ ሳይንቲስቶች በየቀኑ 7,000 ያለቀ የአዳዲስ  ግኝቶች ጥናታዊ ጽሑፎችን ያቀርባሉ:: በአሜሪካ ብቻ ከ100,000 መጽሐፍ በላይ በየዓመቱ ይታተማል::»*[5]

*ዩኒስኮ /UNESCO/ በአንዳንድ ሀገሮች በአንድ ዓመት የታተሙ አዳዲስ መጽሐፎች ብዛት እንደሚከተለው አቅርቦ ነበር:: አሜሪካ 288,355 (2009)፣ እንግሊዝ 20,600 (2005)፣ ቆጵሮስ 930 (1996)፣ አፍጋንስታን 2,795  ኬንያ 300 (1994) ኢትዮጵያ 240 (1991) በማለት 110 ሀሮችን ዝርዝሮዋል::*[6]  ይህ የዕውቀት ጉርፍ ዓለምን እንዴት በማጥለቅለቅ ላይ እንደሚገኝ ያመለክታል::

[5] *James Giles, The God factors ignite your potential, Pneuma Life publishing, USA, 1995 p. 37*
[6] *http://en.wikipedia.org/wiki/Books_published_per_country_per_year*





ይህ ሁሉ መረጃ ፍሰት እያለ ዓለማችን የሚመጥናት ራእይ ባለቤት ስላልሆነች በጦርነት፣ በረሃብ፣ በፓለቲካና በኢኮኖሚ ቀውስ፣ በጥላቻ፣ በበሽታ፣ በመልካም አመራር እጦት፣ በቸነፈር፣ በኒኩሌር ስጋት፣ በአሸባሪነት፣ በሃይማኖት ጽንፈኝነት፣ በአየር ብክለትና በስነ ምህዳር ቀውስ፣ በዘረኝነት ጫና ሥር ወድቃ በመጠጥ ስካር ናላው እንደ ዞረ ሰው በመንገዳገድ ላይ ትገኛለች:: የመረጃ ክምችት ለብዙ ነገር ትልቅ ሀብትነቱ ባይካድም ራእይን ቢያግዝ እንጂ በራሱ ግን ራእይ አይደለም:: ራእይም አይሆንም:: እንዴት ሥራ በመፍጠርና በቀላሉ አንቱ የተባለ ቱጃር መሆን እንደሚቻል ተንትነው እንደ ዶሮ ብልት በቁጥር የሚያስቀምጡ ሊቆች የሚያስተምሩትን መሆን ያልቻሉት ዕውቀት ስሌላቸው ሳይሆን ራእይ ስለሌላቸው ነው:: ሁላችንም የሚናውቀውን ብንሆን ኖሮ አሁን ባለንበት ቦታ ባልሆንን ዓለማችንም ይህን ባልመሰለች ነበር:: ሰው የሚሆነው የእይታውን ያህል እንጂ የመረጃውን ያህል አይደለም:: ብዙ የዕውቀት መረጃ ተሸክመው አንዳች የተለየ ነገር ለራሳቸውና ለትውልዱም ሳይሠሩ ዝም ብለው ኖረው ያለፉ ነበሩ:: ይህ ነው የተባለ ዕውቀት ሳይኖራቸው ደግሞ አንድ ራእይን ከጌታ ተቀብለው በማድረግ ለዘመን ሁሉ ተምሳሌት የሆኑና ጌታን አስከብረው ያለፉ ብዙ ሰዎችን ዓለማችን አስተናግዳለች:: ሰዎች በዕውቀት ባሕር ውስጥ እየሰመጡ ስመጡ ገና ያልደረሱበት የዕውቀት ውቅያኖስ ትልቅነት ፊንትው ብሎ ስለምታያቸው ያሉበት የዕውቀት ባሕር ለመዋኘት የማይቻለበት ኩሬ አድረጎ የመቁጠር አባዘ ይጠናወታቸዋል::

ብዙ ማድረግ በሚችለው የተከማቸ ዕውቀታቸው እምነት ከማጣትና ከፍርሃት የተነሳ በመረጃ ሃብታም የተግባር ድሃ ሆነው ይሞታሉ:: ብልህ ሰው በእጁ ከለሉ ዘጠኝ ነገሮች ይልቅ በእጁ ያለ አንዱን ከሺ በላይ እንደ ሆነ ቆጥሮ ይጠቀምበታል:: የሚበልጥ ዕውቀት መፈለጉ መልካም ሲሆን ባወቁት ያለመጠቀም ደግሞ የመደንዘዝ ምልክት ነው:: ብዙ አወቆ ምንም ካለማደረግ ይልቅ የምናውቀውን አንዱን አድርገን መገኘት የትልቅነት ምልክት ነው:: ዶክተር ኪኒዝ ዊንበር የተባለ ጸሐፊ *«በአዕምሮ ከተቆለለው የዕውቀት መረጃ ብዛት ተራማጅ ኢንሳይክለሮፐዲያ ተብሎ ቅጽል ስም ወጥቶለት ምንም ለዓለም*

*ካላበረከተው ምሁር ይልቅ ዝግምተኛ ተብሎ በራሱ የተለየ አንድ ፈጠራ ሀሳብ የተገለጠ ተራ ሰው፤ ለዓለም ትልቅ ባለውለታና አዋቂ ነው::»* እንዳለው የዕውቀት

ብዛት ለሚበልጥ ሥራና ለላቀ ውጤት ካላበቃን ዋጋ የለውም:: የምንወርሰውና የሚወርሰን መረጃችን ሳይሆን እይታችን ነው:: ዋናው ነገር ምን ያህል ታውቃለህ? ሳይሆን በዕውቀትህ ምን ሠራህ? ውጤታማነታችን የሚለካው በአዕምሮአችን ውስጥ በተከማቸው የዕውቀት ብዛት ሳይሆን ለጌታ ክብር ለሰዎች ልጆች ጥቅም በሚንሠራው አንድ ውጤታማ ሥራ እንደሆነ አንዘንጋ:: በዘመናችን የብዙዎች ትግል ለራእያቸው ግብአት የሚሆን ዕውቀትና ክህሎት መፈለግ ሳይሆን «ዋናው ወረቀት ነው» በሚለው አደገኛና ራስ ተኮር ፈልጥ ለሥራ ሳይሆን ለደሞዝ ለውጥና ለስም የወረቀቶች ድታ የዕውቀትና የተግባር ድሆች ሆነዋል:: ራእይ መር ሕይወት ስኖረን አቋማችን ከዚህ ይለያል::

## *የተለያዩ መዝገበ ቃላት ራእይን እንዴት ይፈታሉ?*

### *ስትሮግ ኮንኮርዳንስ*

እንደ ስትሮንግ ኮንኮርዳንስ ራእይ «ካሀዋዞን» chazown (khaw-zone) ከሚለው የእብራይጥ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም *«አርቆ ማየት፣ ተሰውሮ የነበረ ነገር መግለጥ፣ ህልም ማለት ነው::»*[7] ይላል::

### *ሚሪያም ዌብስተር ዲክሽነሪ*

ራእይ የሚለውን ቃል ሲፈታው *«መለኮታዊ ጽንሰ ሀሳብ፣ ሊሆን ያለ የሩቅ እይታ፣ ያልተለመደና ያልተጨበጠ በሕልምና በራእይ ግን የታየ የመጪው ስዕል ይለዋል::»*[8] ይህም ዛሬ ያልሆነ ነገር ግን በእይታችን የተጠናቀቀ በግዑዙ ዓለም ልናመጣው የምንነሳበት የመለኮት የመጪው ጊዜ አጀንዳ ማለት እንችላለን::

[7] *Libronix Digital Library System* *Strong's Concordance* *number 2377*

[8] *Libronix Digital Library System -Merriam-Webster's Collegiate Dictionary (Eleventh Edition*





### *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*

*«ራእይ በእንቅልፍ ወይም በተመሰጠ ጊዜ የሚታይ የህሊናዊ ትርኢት፣ህልም»*[9] እንደሆነ አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በጥሬ ትርጉሙ ሲገልጸው ይህም ራእይ ማለት ዛሬ ላይ ቆመን በዓይነ ህልናችን የሚታየን እንደሆነ እንመለከታለን::

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ የራእይ ትርጉም

በመጽሐፍ ቅዱስ ራእይ ማለት መለኮታዊ ሀሳብ ለሰው የሚገለጥበት አንዱ መንገድ ማለት እንችላለን:: በሌላ አገላለጽ ራእይ ከአንድ መለኮታዊ አካል ለአንድ ምድራዊ አካል በትእይንት መልክ መለኮታዊ መልዕክት የሚመጣበት አንዱ መንገድ ነው:: በብሉይ ኪዳን ራእይ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ "raa and haza" ከሚሉ ሁለት ግሥሶች የመጣ ሲሆን ትርጉማቸውም ማየት ማለት ነው:: በአዲስ ኪዳንም ራእይ የሚለውን ቃል ለመግለጥ በአገልግሎት ላይ የዋለው የግርክ ዋናው ግሥ "*horao*" [oJravw] የሚል ሲሆን ትርጉሙም ማየት፣ መመልከት መረዳት የሚል ነው:: በሁለቱም ኪዳኖች ራእይ ማለት አንድ መለኮታዊ መልዕክት ከእግዚአብሔር የምንሰማበት ሳይሆን በማየት የሚንቀበልበትን ሂደት የሚገልጥ እንደሆነ እንመለከታለን::[10] ሳይኮሎጂስቶች የሰው ልጅ ባየው ነገር የሚያዝ፣ የሚነዳና የሚመራ "eye-minded" ተደርጎ የተፈጠረ ፍጡር ነው ይላሉ::

## *የተለያዩ ጸሐፊዎች ራእይን እንዴት ይገልጻሉ?*

ጌታቸው በለጠ በመጽሐፉ ራእይን ሲገልጽ *«በአዕምሮ የተረገዘና ልሂቅ ባህርያት የሚንፀባረቅበት ፋይዳ ያለው የነገ መዳረሻ»*[11] *ሲሉት ዶክተር ዓለሙ ቢፍቱ «በአገልግሎትና በራእይ ማደግ» በሚለው መጽሐፉ ስለ ራእይ ምንነት ሲገልጽ «ራእይ ከመንፈሳዊ አሠራር አንጻር፣ በሰማይ የሚከናወነውን መለኮታዊ እቅድና*

[9] *የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ 1993 ዓ.ም ገጽ 101*
[10] Elwell, Walter A. "Entry for 'Vision(s)'". "Evangelical Dictionary of Theology". . 1997.
[11] Ibid, p. 49

*ተግባር በምድር ላይ እንዴት እንደሚፈጸምና እንደሚደረግ የሚገለጽበትና የሚተረጎምበት አምላካዊ መመሪያ ነው::»*[12] ብሎዋል:: መጋቢ ቢሊይ ሀይበልስ ስለ ራእይ ምንነት ሲገልጽ *«መለኮታዊ ራእይ መቀጣጠልን በሰዎች ውስጥ የሚፈጥር የመጪው ፎቶ ነው::»*[13] ብሎዋል::

አንድ የቤተክርስቲያን መሪ ራእይ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ሲመልስ *«የማይታየውን በማየት በገሀዱ ዓለም እንዲታይ ማድረግ ነው»* ሲል ሌላኛውም *«ራእይ ማለት አሁንና መጭውን አገናኝ ድልድይ ነው»* ብሎዋል:: ጆርጅ ባሪና ደግሞ *«የአገልግሎት ራእይ ማለት እግዚአብሔር በጠራው ባሪያው ውስጥ የሚያስቀምጠው ብልጫ ያለው የመጪው ስዕል ሲሆን መሠረት የሚያደርገውም አገልጋዩ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለራሱና ስላለበት ሁኔታ ባለው ትክክለኛ ግንዛቤ ላይ ይሆናል::»*[14] ሲል በርት ናነስ የተባለ ክርስቲያን ጸሐፊ ደግሞ *«ራእይ ለድርጅትህ የምትነድፈው ሊጨበጥ የሚችል፣ ተአማኒነት ያለውና ማራኪ የሆነ የወደፊት ክንውን ነው::»*[15] ብሎዋል:: ዶክተር ማይልስ ሞኖሮ «መጽሐፍ ቅደሳዊ ራእይ ማለት ጀማሬ ላይ ቆሞ ፍጻሜን የማየት አቅም ነው»[16] በማለት ጽፈዋል:: ከላይ እንደተመለከትነው የተለያዩ ክርስቲያን ጸሐፊዎች መንፈሳዊ ራእይን በተለያየ መንገድ በመግለጥ ራእይ ባለፈውና አሁን ባለው ሳይሆን በመጭው ላይ እንደሚያተኩር ስምምነት ያላቸው ይመስላሉ::

ራእይ ምድነው? ለሚለው ጥያቄ ከላይ የተመለከትናቸው ጽንሰ ሀሳቦች እንዳሉ ሆነው የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊም የራሱን የራእይን ምንነት እንዲህ ለማስቀመጥ ይሞክራል:: *መለኮታዊ ራእይ ከእግዚአብሔር የሚንቀበለው፣ የመፈጠራችን*

[12] *ዓለሙ ቢፍቱ፣ በአገልግሎት ራእይ ማደግ ገጽ 7*
[13] Hybels Bill, Courageous Leadership,*Zondervan, Grand Rapids, Michigon USA, 2009, p.36*
[14] *Ibid, p. 37*

[15] *Burt Nanus, **Visionary Leadership**, San Francisco Jossey-Bass.USA. 1992.*

[16] *Myles Munroe, In pursuit of purpose, Destiny Image publishing, Inc. 1992. p.83*





*ዓላማ ገላጭ፣ የትውልዱ ጥያቄ መልስ አዘል፣ በመጪው ላይ የሚያተኩርና በሰው ልብ የሚበቅል መለኮታዊ ዘር ነው:: ራእይ ዕደሜያችንን የሚያካልል፣ ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ የሚያተርፈንና በልባችን ውስጥ የሚንተከተክ አንድ ገኸ መለኮታዊ ሀሳብ ነው:: ራእይ በዛሬው አሉታዊ ነገሮች ተስፋ ሳንቆርጥ እንድንገዝ ተነሳሽነትን በውስጣችን የሚፈጥር አዎንታዊና ታላቅ በልብ ዓይኖች የሚታየን የመጪው ብሩህ ምስል ነው::*

## የአንድ ራእይ ሁለት ገጽታዎች

### ገጽታ አንድ

አንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንዳሉት ሁሉ እንዲሁም ማንኛም እውነተኛና መለኮታዊ ራእይ ሁለት ገጽታዎች ይኖሩታል:: የራእይ የመጀመሪያ ገጽታ የሚባለው አሁን እንደ ግለሰብ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያንና እንደ ሀገር ያለንበት አፋጣኝ መፍትሔ የሚሻ አንገብጋቢ ጉዳይን ይመለከታል:: ራእይ አዲስ ነገር የምንፈጥርበት ወይም አሮጌውን የምናድስበት ታላቅ ኃይል ነው:: አዲስ ነገር ለመፍጠርና አሮጌውን ለማደስ በማይፈለግበት ምድር ባለራእይ ሆኖ መገለጥ ላልተጠየቁት ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንደ መነሣት ይቆጠራል::

ሙሴ በምድረ በዳው በጎችን ሲጠብቅ ታላቅ ራእይ *«ቁጥቋጦ በእሳት ሲነድድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ::» (ዘፀ. 3: 2)* የሚለው ሀሳብ የራእይው የመጀመሪያ ገጽታ ነበር:: ይህም በባርነት፣ በጭቆና፣ በሞት አዋጅ፣ ተከበው በመከራ ምጣድ ላይ ለአራት ክፍለ ዘመናት እየተጠበሱ መከራው በፍጹም ሊያጠፋቸው ስላልቻለው የእሥራኤል ሕዝብ ያሉበትን ዘግናኝ ሁኔታን ያመለክታል::

ባለራእይ ያለውን ችግር በትክክል የመረዳት ብቻ ሳይሆን በችግር ውስጥ ባሉት ሰዎች እግር ራሱን በመተካት የእነርሱን ረሃብ፣ ሕመም፣ ልባዊ ጩኸትና ሸክም በትክክል የሚሰማው ብቻ ሳይሆን ለመለወጥ የሚነሳ የመፍትኄ አዋጅ ነጋሪ ነው:: የራእይ የመጀመሪያ ገጽታ ካልታወቀ የራእይ ሁለተኛ ገጽታ አይታወቅም::

### ገጽታ ሁለት

*የአንድ ራእይ ሁለተኛው ገጽታ «ከዚህች አገር ወተትና ማር ወደምታፈሰው አገር ወደ ሰፊይቱና ወደ መልካሚቱ አገር ወደ ከነዓናዊያን... አወጣችሁ ዘንድ ወረድሁ።» (ዘፀ. 3:8) ሙሴ «ከዚህች ሀገር» ሲል የእቶን በረት ከተመሰለችው ግብፅ ወተትና ማር ወደምታፈልቀው ከነዓን የመምራት ራእይን ሲቀበል እናያለን።*

ሙሴ በአንደኛው የራእይ ገጽታ ላይ ቆሞ ሁለተኛ ገጽታን አየ። አንደኛ የራእይ ገጽታ የራእዩ መነሻ ሲሆን ሁለተኛው የራእዩ ገጽታ ደግሞ የራእዩ መድረሻን ያመለክታል። ሁለቱም የራእይ ገጽታዎች አንድ ዓይነት መልክ ሊኖራቸው በፍጹም አይችሉም። የእግዚአብሔር ራእይ በመከራ ጀምሮ በመከራ አያበቃም፣ በማጣት ጀምሮ በማጣት አይጨርስም፣ በጨለማ ጀምሮ በጨለማ አይደመድምም። እግዚአብሔር ሕዝቡ በሙሴ በኩል አሁን ያለበትን ብቻ ሳይሆን ነገ ሊሆንለት ያለውን አስደናቂ የበረከትና የሙላት ራእይ ሲያስጨብጠው እንመለከታለን። በመጀመሪያው የራእይ ገጽታ መራብ፣ መከራ፣ ማጣት፣ ጨለማ ሲሆን ሁለተኛው የራእይ ገጽታ ግን ወተትና ማር ወደምታፈሰው ሀገር ማስገባት ነበር። የሙሴ መጀመሪያ የራእይ ገጽታ ግብፅ ሲሆን የራእይው ሁለተኛ ገጽታ ከነዓን ነው። ባለበት ቦታ ጀምሮ ባለበት ቦታ የሚያበቃ ራእይ ትክክለኛ ራእይ አይደለም። በአንድ ገጽታ ራእይ ባለንበት ለመሽከርከር ካልሆነ የትም መድረስም ሆነ ማድረስ አይታሰብም። የባለራእይ ዓይኖች ችግርና መፍትሔውንም አንድ ላይ የመመልከት አቅም አላቸው።

## መለኮታዊ ራእይ

### ሀ. የመጪው ሥዕል ነው

በመጽሐፍ ቅዱሳችን 26 ጊዜ ስሙ የተጠቀሰው፣ ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳንም በምሳሌነት የተገለጠ፣ የአዕዋፍ ንጉሥ የሚል ቅጽል ስም የተሰጠውና አሜሪካን ጨምሮ የብዙ ሀገሮችና ድርጅቶች የመለያ አርማ ሆኖ እያገለገለ ያለው ወፍ ንስር





ይባላል። እንደ የሥነ- አዕዋፍ ሳይንስ ምሁራን ጥናት ንስርን ከሌሎች የወፍ ዘር ልዩ ካደርጉት ነገሮች መካከል የዓይኑ ትልቅነት አንዱ ሲሆን መጠኑም ከሰው ዓይን ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ከሰው ዓይን አራት እጥፍ በላይ ማየት እንደሚችልና ከ1000 የጫማ ከፍታ ላይ እየበረረ በመሬት በርቀት ላይ ያሉትን ጥቃቅን ነገሮች ሳይቀር አቅርቦና አተልቆ ማየቱ፣ ንስር ከንስር ጋር እንጂ ከድንብጥ፣ ከአሞራና ከሌሎች አዕዋፍ ጋር አይበርም ምክንያቱም እርሱ በሚበርበት ከፍታ ላይ መብረር ስለማይችሉ፣ አውሎ ንፋስን በፍጥነት ለመብረር መጠቀሙ፣ አንደገና ኃይሉን የማደስ የተፈጥሮአዊ ችሎታ ባለቤት መሆኑ ልዩ እንዳደረገው ይናገራሉ።[17] ባለራእይም በዛሬ አሉታዊ ነገሮች ሳይደናበር የነገን ብሩህ ገጽታ አይቶ ማሳየቱ፣ በእምነት ወዳየው መራመዱ፣ ተግዳሮቶችን ለዕድገት ግብአትነት መጠቀሙና በጌታ ዕለት ዕለት መታደሱ ከንስር ጋር ያመሳስለዋል።

መንፈሳዊ ራእይ የመጪው ትልቅ አዎንታዊ ሥዕል ነው። መለኮታዊ ራእይ ከዕውቀታችን፣ ከልምዳችንና ከታሪካችን ቀነጫጭበን ያሳደግነው የመጪው የተሻለ ትልቅ የምኞት ተራራ ሳይሆን በሕይወታችን ሊሆን ያለ የእግዚአብሔር የጊዜው ገዢ ሀሳብ ነው። መንፈሳዊ ራእይ በአይነ ልቦናችን አይተን በገሀዱ ዓለም ለመውለድ የምናምጥበት አዲስና ልዩ የሕይወት ምዕራፍ ነው። የመጪው ትልቅ ስዕል ሲባል ቤተ ክርስቲያናዊ፣ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ይዘት ያለው መለኮታዊ አጀንዳ ማለት ነው።

መለኮታዊ ራእይ የተጨበጠ አጀንዳ እንጂ ዝም ብለን እየተጓዝን በድንገት ወይንም በአጋጣሚ የምንደርስበት ተራ ዕድልም ሆነ የተለመደ ድልም አይደለም። በመሆኑም ባለራእይ በትልቁ የመጪው ሥዕል እንጂ በትልቅ የመጪው ዕድል አያምንም። ባለራእይ የመልካም ዕድል ፈጣሪ እንጂ ጠባቂ አይደለምና። ይህ የመጪው ግልጽ ስዕል ውስጣዊና ግላዊ እንጂ ከሌላ ሰው ሰምተን ስለ መጪው እንደ ገደል ማሚቶ የምናስተጋባው ሀሳብም አይደለም። ዓይነ ልቦናችን በግልጽ ጌታ ያሳየንን በገሃዱ ዓለም እንዲገለጥ ጨክነን ሰዋዊ ሚናችንን እየተጫወትን ሌሎችም ፍንትው ብሎ እንዲታያቸው ስናደርግ በራእይው ኃይል ብዙዎችን

[17] *http://en.wikipedia.org/wiki/Eagle*

እንማርካለን:: ባለራእይ ተጽኖ ፈጣሪ ነው የሚባለው ለዚህ ነው:: በውዴታ አብረውን የቆሙትም በራእዩው የፍቅር ግዴታ ለተግባራዊነቱ ከእኛ ጋር በቆራጥነት ይሰለፋሉ:: በእኛ ውስጥ በግልጽ በዓይነ ልቦናችን ዓይተን በሌሎችም ውስጥ እንዲታይ የማድረግ አቅምና ትዕግስት ከሌለን ራእያችን *«ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ»* እንደተባለው ምሳሌ ያለውጤት ይሆንብናል::

## ለ. የለውጥ ጥሪ ነው

ራእይ የለውጥ የጥሪ ደወል ነው:: ኮሎኔል መርሻ ወዳጆ ከአዲስ ራእይ አንጻር የለውጥን አስፈላጊነት ሲጠቅሱ *«ነባር የአሠራር ልምዶች አዲሱን ራእይ ለማስተናገድ እንዲችሉ በአግባቡ ለውጥ ሊደርግባቸው ይገባል::»*[18]

ያሉት ራእይና ለውጥ የማይለያዩ ስለሆነ ነው:: ራእይ ከነበርንበትና አሁን ካለንበት ለትልቅ ነገር የመንጠራራት ሕይወትና አካሄድ ስለሆነ ባለራእይ «እንደለመድነው» «እንደሚታወቀው» «እንደ ባሕላችን» በማለት ወደ ኋላ ለሚጉትቱት አሮጌ አባባሎች ብዙ ቦታ አይኖረውም:: ራእይ ነገሮች እጅ እጅ ሲሉንና ከጭንቅ እንደ መውጫ በር የምንጠቀምበት ብቻ አይደለም:: ራእይ ከተሻለ ወደሚበልጠውና አሁን ካለንበት ምቹ ሁኔታዎች ወደ ላቀው የመለኮት ፈቃድና ቀጣይ አጀንዳ የመሸጋገሪያ ብቸኛ ድልድይ ነው:: በአንድ ቤተ ክርስቲያን ነገሮች በጥሩ ሁኔታ እየተካሄዱ ባሉበት እንኳ ራእይ ለላቀው ውጤት ሲባል ለውጥን የግድ ይላል:: ሰዎች ደግሞ በባሕርያችን የለውጥ ውጤቱ እንጂ ሂደቱ ብዙ ስለሚያናውጠን ለጥቅማችን ራእይ የሚጠይቀውን የለውጥ ጉዞ ለመሄድ መታገስ ያቅተናል:: ሁሉም ለውጥ ዕድገት ባይሆንም ያለ ለውጥ ግን ዕድገት እንደማይኖር አንዘንጋ:: ራእይን ወደን ለውጥን መጥላት ፈውስን ወድደን ፈውስ አምጪ መራራ መድኃኒት ለመዋጥ እንደመጥላት ይሆናል:: ራእይና ለውጥ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ስለሆኑ ማለያየት አይታሰብም:: ራእይ የለውጥ አባት ነው::

---

[18] *መረሻ ወዳጆ፣ መሪነት ገጽ*





ራእይ ከሌለ አቅጣጫ የለም፣ አቅጣጫ ከሌለ መሄድ የለም፣መሄድ ከሌለ መድረስ የለም፣ መድረስ ከሌለ ማድረግ የለም፣ ማድረግ ከሌለ ለውጥ የለም፣ ለውጥ ከሌለ ዕድገት የለም፣ ዕድገት ከሌለ ሕይወት የለም:: በመሆኑም በመለኮታዊ ራእይ ለመመራት ከፈቀድን ለውጥ ግዴታ እንጂ ውዴታ አይደለም:: *«መኖር መለወጥ ነው! ፍጹምነት ደግሞ አሁንም አሁንም መለወጥ ነው»* ያለው ጆን ሄነሪ ነው::

## ሐ. ምንጩ እግዚአብሔር ነው::

ሙሴ የእሥራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ባርነት ነፃ የማውጣት ራእይ፣ ነህምያ የፈረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር የመገንባት ራእይና ሐዋርያው ጳውሎስ አሕዛብን በወንጌል የመድረስን ራእይ ከእግዚአብሔር እንደተቀበሉ ሁሉ ዛሬም የእውነተኛና መለኮታዊ ራእይ ምንጭና ሰጪ አንድ ብቻ ሲሆን እርሱም እግዚአብሔር ነው::

መለኮታዊ ራእይን ኮፒ ማድረግ፣ መዋስ፣ መቅዳትና መስረቅ አይቻልም:: የሰዎችን ሀሳብ መቅዳት ይቻል ይሆናል ነገር ግን የባለራእይነትን ልብና መንፈስ መቅዳት በፍጹም አይቻልም:: *«እግዚአብሔር ሁሉ ያለው ሲሆን ፎቶ ኮፒ ማሽን የለውም ምክንያቱም የእርሱ ሥራ ሁሉ ኦርጂናል ናቸውና»* ብለው ወንጌላዊ ሬሂናርድ ቦንኬ አንዴ ሲናገሩ በጆሮዬ ሰምቼ ነበር::

የአገልግሎት ራእይ እግዚአብሔር በአንተ በኩል ተገልጦ ብዙዎችን የሚያሳትፍ መንግስቱን በምድር ላይ ለማስፋት የዘላለማዊ ዕቅዱ አካልና ነፀብራቅ ነው:: መለኮታዊ ራእይ በሰዎች የመጠቀና የጠለቀ የአስተሳሰብ አቅም፣ የምክንያታዊነት ችሎታ፣ የትምህርትና የልምድ ብዛት፣ ከስማችውና ከማንነታቸው፣ በኅብረተሰቡ ከተሰጣቸው ከበሬታና ሥልጣን፣ ከወንበራቸውና ከዝናቸው አልፎም ከገንዘባቸው የተነሣ የሚገኝ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው:: ራእይውን ከተቀበልን በኃላ ጌታ በሰጠን እውቀትና ልምድ፣ ራእይን ማካፈል፣ ሰዎችን ማስተባበር፣ ማቀድ፣ ዕቅድን መከታተል ሰዋዊ ድርሻችንን ቢያመለክቱም ራእይውን ከሰማይ ካልተቀበልን ለብቻቸው በአንድ እጅ ለማጨብጨብ እንደ መታገል ነው::

መለኮታዊ ራእይ የሽማግሌዎች ኮሚቴ፣ የቦርድና የጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ውጤት ሳይሆን ከሰማይ በምድር ላይ በአንድ ሰው በኩል ከእግዚአብሔር ለብዙሐን የሚመጣ መለኮታዊ የጊዜው አጀንዳ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን በጥፋት ውሃ ሊቀጣና ዘርን በምድር ላይ ለማስቀረት የመርከብን ራእይ የሰጠው ለአንድ ሰው ለኖኅ ነበር። መርከብን የሠሩ ሰዎች ግን ከኖህ ጋር ነበሩ። መሲህ የሚመጣበት መንገድ እንዲሆኑ የኪዳን ሕዝብ የአባትንት ራእይ የተሰጠው ለአብርሃም ሲሆን ለራእይው ፍጻሜ እስከ ኢየሱስ ሚሊዮኖች ተሳትፈዋል።

እሥራኤልን ከግብፅ ባርነት ሊያወጣ የነፃ አውጭነት ራእይ የተሰጠው ለሙሴ ሲሆን ከእርሱ ጋር ወንድሙ አሮን፣ እህቱ ማርያም፣ እግዚአብሔርና ሰባ ሽማግሌዎች እንዲሁም መላው የእስራኤል ማህበር ተሳታፊ ነበሩ። ዓለምን ሊያድን የቤዛነትን ራእይ ኢየሱስ በብቸኝነት ቢወጣውም ለአዋጅ ነጋሪነት 12 ሐዋርያቶችና አሁን እስካለችው ቤተ ክርስቲያን ያሉት ቅዱሳን ሁሉ የራሳቸው ቦታና ሚና ነበራቸው፤ አላቸውም። መለኮታዊ ራእይ የሚመጣው በአንድ ሰው በኩል ነው ስንል ከእግዚአብሔር በአንድ ሰው በኩል የሁሉም ይሆን ዘንድ የሚመጣ ሁሉን አቀፍ መለኮታዊ አጀንዳ ማለታችን ነው። አንድ ሰው የመለኮታዊ ራእይ መንገድ እንጂ ምንጭና ባለቤት ሊሆን አይችልም። የመንፈሳዊ ራእይ ምንጭና ባሌበት አንድ ሲሆን እርሱም እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ዶክተር ዓለሙ ቢፍቱ ራእይ የግለሰብ እንዳልሆነ ሲገልጽ *«ራእይ የአንድ ግለሰብ አይደለም። ራእይ ሲሰጥ እግዚአብሔርም ዓላማዬ ብሎ የሚያነጣጥረው በግለሰብ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንግሥትና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ነው።»*[19] *ብሎዋል። ራእይ የግለሰብ ያለመሆኑ ግን በግለሰብ በኩል አይመጣም ማለት እንዳይደለ መታወቅ አለበት።*

## መ. የእምነት መንገድ ነው

የማይቻል ነገር የሚቻለው ለሚያምን ሰው ብቻ ነው። ባለራእይም የማይቻለውን እንደሚቻል መናገሩ የራሱን ሳይሆን የጠሪውን ልክና አቅም ስላወቀ ነው። መቻል

[19] *Ibid., p7*





አለመቻላችን የሚለካው በዕድሜያችን፣ በዕውቀታችን፣ በገንዘባችንና በጡንቻችን ሳይሆን በእምነታችን ልክ ነው። *ቃሉም ለሚያምን ሁሉ ይቻላል* አለ እንጂ ሁሉን ለሚያውቅ ወይም ገንዘብ ላለው ሁሉ ይቻላል አላለም። ራእይ ከእኛ በላይ ትልቅ የጊዜው አጀንዳ ሲሆን ይህን ከግቡ ለማድረስ ያለ እምነት በጭራሽ አይቻልም።

ጌታ በሥጋ አይን ሲታዩ ምስኪኖችን፣ ብዙም ያልተማሩ፣ ሰፊ ዕውቀትና ዕውቅና ያልነበራቸውን፣ የሚላቸውን ለመረዳት እንኳ የዘገዩ፣ ድንጉጦች ሰብስቦ ለሦስት ዓመት ካስተማራቸው በኋላ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ» ብሎ አዘዛቸው። ከታላቁ ተልዕኮ ጋር ወፈር ያለ ገንዘብ በባንክ አከማችቶ ቼክ አልሰጣቸውም። ድርጅታዊ መዋቅርና የደመወዝ እስኬልም አልተከለላቸውም። ነገር ግን ሁልጊዜ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን ቃል የገባላቸው ሲሆን እነርሱም በእምነት ወጥተው ዓለምን በወንጌል ገለባብጠዋል። *«እነርሱም ወጥተው በየሥፍራው ሰበኩ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር።» (ማር. 16: 20)* እንደሚል እግዚአብሔር ስለተናገረንና ስለ ሰማን ብቻ ሳይሆን እንደተገለጠልን ለመሥራት በእምነት ስንወጣ እርሱም ከእኛ ጋር ለመሥራት ይወጣል። ታዘንና ታምነን ካልወጣን ከእኛ ጋር ልሠራ አይወጣም። ሰምቶ አደሮችና አድናቂዎች በበዙበት ሳይሆን ሰምቶ አድራጊዎች ባሉበት ምድር እግዚአብሔር ይሠራል። እምነት የባለራእይ የጉዞው ሰንደቅ ዓላማ ነው። ሲ.ኤች ማክንቶሽ የተባለ ሰው ስለ እምነት ሲናገር፡-

> *«ይህ አይቻልም» የሚል የተቃውሞ ሀሳብ ሲነሣ እምነት ግን ይቻላል ይላል። እምነት እግዚአብሔርን ወደ ሁኔታዎች ለሥራ ያንቀሳቅሰዋል፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሚያቅተው ምንም ነገር እንደሌለና እግዚአብሔርን በማይቻሉ ነገሮች ላይ እንደሚስቅ ያውቃል። በእምነት ዳኝነት መሠረት የማንኛውም ጥያቄ ብቸኛ መልስ እግዚአብሔር ነው። የማንኛውም ችግር ብቸኛ መፍትሔ እርሱ ነው። እምነት ሁሉንም ነገር ወደ እግዚአብሔር ይመራል። እግዚአብሔር ለሁሉ በቂ እንደሆነ ስለሚያውቅ ስድሰት መቶ ሺ ዶላር ይሁን ስድስት ሚሊዮን ስለቁጥሩ ብዛት አይገደውም። የሚያስፈልገውን ግብዓት ሁሉ ከእርሱ ያገኛል። አለማመን ይህና ያ እንዴት ሊሆን ይችላል?» ይላል፣ «በእንዴቶች» የተሞላ ነው። ነገር ግን*

*እምነት ለአሥር ሺህ «እንዴቶች» አንድ ትልቅ መልስ አለው:: ያም መልስ እግዚአብሔር ነው::»*[20]

የባለራእዩ ትልቁ ሀብት ለራእይው ስኬት እግዚአብሔርን ማመንና በእግዚአብሔር መታመን ብቻ ነው:: ባለራእይ በብዙዎች ዘንድ ለማመን በጭራሽ በማይታሰብበትና አይቻልም በተባለበት ነገር ላይ «ይቻላል» ብሎ እግዚአብሔርን የሚያምን ሰው ነው:: እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚችል ማንበብና መናገር ቀላል ሲሆን ይቻላል ብሎ መራመድ እምነትን ይጠይቃል:: ባለራእይ የተለየ ሰው ሳይሆን እግዚአብሔርን ለአንድ ትልቅ ነገር ያመነ፣ የተሰጠና ቆራጥ እርምጃ ያለው ተራ ሰው ነው:: በተለይ በሀገራችን በተመሳሳይ ነገሮች የተከበብንበት ዋናው ምክንያት አንድን ነገር ለማድረግ ስንነሣ አይቻልም፣ ህብረቱም ሆነ ኮሚቴው ይህን አይቀበልም፣ አልተለመደም፣ በእኛ ሀገር ይህ አይሠራም የሚለው አመለካከት ገዝፎ ስለወጣ ነው:: በተለመደ ነገር የታጠረ አዕምሮ የተለየ ነገር ለመሥራት በፍጹም አይችልም:: ስለዚህም ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ እይታ ያላቸው ባለራእይዎች በብዛት እንደ ዕድሜያችንና እንደ ታሪካችን እንዳይነሡ እንቅፋት ሆኖብናል:: አይቻልም! የሚለው ቃል በእኛ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠር የሚችለው ከሌሎች ልብ ወጥቶ በእነርሱ አንደበት ሲነገርን ሳይሆን ከልባችን ወጥቶ በአንደበታችን መነገር ሲጀምር ብቻ ነው:: ባለራእይ አይቻልም የተባለውን አስቀድሞ በእይታው ችሎ ስለተነሣ ሰዎች አይቻልም ሲሉት አልፎ ይሄዳል እንጂ አይደናበርም:: ሁሉን በሚችለው አምላክ ውስጥ ሆኖ በእምነት ሁሉን ላየ ሰው የማይቻል አንዳችም የለም::

ባለራእይ የማይቻል በሚመስል ሁኔታ ውስጥ ይቻላልን ያወጅል:: በዙሪያው ያሉት ሰዎች ስለደገፉትና ስለተቃወሙት ግን አይደለም:: ሁሉን በሚችለው አምላክ ዓይን ሁሉን አይቶ ስለተነሣና «ይቻላል» የሚል የውስጡ ጥንካሬ ከተቃወሞው በላይ ስለገዘፈበት ነው:: ዓለም በአንድ ድምፅ ራእያችንን ደግፎ ውስጣችን በእኛ ላይ ካመፀ የትም አንደርስም::

[20] *Ibid, p.37*





ነገር ግን ውስጣችን ወደ ፊት መሄዳችንን አምኖበት ዓለም ቢቃወመን እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ በእኛ ይፈጽማል:: በ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀርመናዊው የቤተ ክርስቲያን አዳሽ የተባለው ማርቲን ሉተር ቤተ ክርስቲያንን የማደስ ታላቅ ራእይን አንግቦ ስጓዝ በብዙ ጦርነት፣ ጥላቻ፣ ስም የማጥፋት ዘመቻና የግድያ ዛቻ ውስጥ አልፎ ነበር:: አንዴ ፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኛው «ሉተር ዓለም ሁሉ አንተን እየተቃወመ ሰላለህ ዓለምን መቃወም ትችላለህ ወይ?» ብሎ ስጠይቀው ሉተር ስመልስ ክቡር ዳኛ ሆይ «እኔ ብቻዬን አይደለሁም:: ዓለም ሁሉ በእኔ ላይ ብነሣ እኔም ዓለማትን በፈጠረው አምላክ ጋር ቆመ በውሸት ጉዳና ላይ ያለችውን ዓለም እፋረዳለሁ::»

እንዳለው ሉተር ዓለምን የረታው ከጌታ ቃልና ከመንፈሱ ባገኘው አቅምና በጠራው መንፈሳዊ ራእይ ጉልበት ነበር::

## መርሆዎች

- *መለኮታዊ ራእይ በዛሬው አሉታዊ ነገሮች ተስፋ ሳንቆረጥ እንድንጓዝ ተነሳሽነትን በውስጣችን የሚፈጥር አዎንታዊና ታላቅ በልብ ዓይኖች የሚታየን የመጪው ሥዕል ነው::*
- ባለራእይ የተለየ ሰው ሳይሆን እግዚአብሔርን ለአንድ ትልቅ ነገር ያመነ፣ የተሰጠና ቆራጥ የእምነት እርምጃ ያለው ተራ ሰው ነው::
- *መቻል አለመቻላችን የሚለካው በዕውቀታችን፣ በገንዘባችንና በጡንቻችን ትልቅነት ሳይሆን በእምነታችን ልክ ነው::*
- አንድ ሰው የመለኮታዊ ራእይ መንገድ እንጂ ምንጭና ባለቤትም ሊሆን አይችልም::
- የባለራእይ ዓይኖች ችግርና መፍትሔው አንድ ላይ የመመልከት አቅም አላቸው::
- *ራእይና ለውጥ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ስለሆኑ ማለያየት አይታሰብም:: ራእይ የለውጥ አባት ነው:: ራእይ ባለበት ለውጥ አለ:: ለውጥ ባለበት ራእይ አለ::*

- ባለራእይ በትልቁ የመጪው ስዕል እንጂ በትልቅ የመጪው ዕድል አያምንም። ባለራእይ የመልካም ዕድል ፈጣሪ እንጂ የመልካም ዕድል ጠባቂ አይደለምና።
- ሁለት ገጽታ የሌለው ራእይ ግቡን ሊመታ አይችልም።





# 2 የራእይ ጥቅሞች

*«ራእዩ የተወሰደበት አገልጋይ ማለት ልቡ ከውስጡ ተቆርጦ እንደ ወጣበት ሰው ነው። ራእይ አገልጋይ ወደ አየለት ግብ የሚያስኬደው ሞተር ነው። ተግባርን በውስጡ የሚፈጥርና ተከታዮችን የሚያቀጣጥል እሳት ነው። ዘመን በዘመን ሲተካ ያለመናወጥ በጽናት መስዋእት እየሆነ ጌታን በታማኝነት እንዲያገለግል ያደርገዋል።» ቢል ሀበልስ*

ለአንድ ቤተ ክርስቲያን መለኮታዊ ራእይ የዕድገት ቁልፍ ነው። የአንድ መንፈሳዊ መሪ ስኬት ወንበሩ፣ ቢሮው፣ የምንሰጠው ስያሜ፣ የሚከፈለው ገንዘብ፣ የተከታዩቹ ፍቅር አይደለም። ሁሉም በቦታቸው አስፈላጊነታቸው ባያጠያይቅም ራእይ ባይኖረው ግን በራሳቸው ምንም አይፈይዱም። ለዚህም ነው ታላቁ የእሥራኤል ንጉሥ የነበረው ሰሎሞን ሲናገር «ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል።» (ምሳ. 29: 18) ያለው። «መረን» የሚለውን ቃል የአማርኛው መዝገበ ቃላት ሲፈታው፡- «ስድ፣ ልቅ ይለዋል።»[21] ሕዝቡ መረን እንዳይሆን መሪ ራእይን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ሕዝቡን በራእይ ጉልበት ሊመራ ይገባል።

ያለ ራእይ መጓዝ አቅጣጫ ማጣት፣ መቅበዝበዝ አደጋ እንዳለው ሁሉ በራእይ ጉልበት መጓዝ ጥቅሙ ምን ይሆን? የሚል ጥያቄ በውስጣችን መነሣቱ አይቀሬ ነው። በቀደመው ክፍል የራእይን ምንነት በሰፊው እንደተመለከትን ሁሉ በዚህ ክፍል ደግሞ መለኮታዊ ራእይ መር ሕይወት መምራት ለግለሰብ፣ ለቤተሰብ፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለድርጅትና ለመንግሥት የሚሰጠውን ጥቅም እንመለከታለን።

[21] Ibid, p.140

## ጥቅም 1 አቅጣጫና ዓላማ

አንድ መንፈሳዊ መሪ ለሚመራችው ሰዎች አቅጣጫና ዓላማን ማሳየት ካልቻለ እውነተኛ መሪ ሊሆን አይችልም። መለኮታዊ ራእይ መድረሻችንን ብቻ ሳይሆን ለምን ወደዚያ ለመሄድ እንዳስፈለገን ማወቅ ለተከታዮቻችን ግልጽና የተጨበጠ አቅጣጫና ዓላማ ይሰጣቸዋል። ሰዎች አቅጣጫና ዓላማቸውን ሲረዱ የመሰጠታቸው መጠን በጣም የላቀ፣ ለራእይው ስኬት በሚጫውቱት ትንሽና ትልቅ ሚና ደስተኞችና ታማኞች ይሆናሉ። መንፈሳዊ መሪ ተከታዮቹን ውጤታማ እንዲሆኑ ሲያደርግ መለኮታዊ ራእይ ደግሞ ተከታዮቹ በከፍተኛ ተነሳሽነት ለራእይው ስኬት እንዲነሣሡ ያደርጋል። የተሳካለት መሪ ለተከታዮቹ ዓላማውን በመንገር ብቻ ሳይሆን የውጤቱን አንጊነትና እንዴት እዚያ መድረስ እንደሚቻል ያሳያል፣ ያስረዳል። አቅጣጫና ዓላማ ከራእይ ማሕፀን ይወለዳሉ። በአንድ ቤተ ክርስቲያንና አገልግሎት እውነተኛ ራእይ ካለ በዚያች ያሉት ቅዱሳን አሁን የት እንዳሉና መድረሻቸው የት እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ። በደረሱበት ሥፍራ ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል በተሞላ ልብ፣ በእምነት እርምጃቸውና ልዩ ጫና በመፍጠር አቅማቸው ይታወቃሉ።

ከሁሉም የሚያሳዝነው ጥቂት እንደ ትልቅ የጊዜው መገለጥ የሚቆጠሩ መልዕክቶቻችን ተግዳሮቶቻችንን በመላ እንድናመልጣቸው የሚመክሩን ወይንም ድርሻችንን ሳንወጣ እጆቻችንን አጣጥፈን ቁጭ ብለን የእግዚአብሔርን ተአምራት ጠባቂዎች አድርገውናል። ዓላማና አቅጣጫ የጠፋበት ሰው የቦረና ኦሮሞዎች እንደሚሉት «ሞኝ በጠፋበት ሀገር እንደ ቤቱ ይቆጥረዋል።» እንደ ማለት ይሆናል።

## ጥቅም 2 ግልጽነት

ግልጽነት ከሌለ፣ መተማማን የለም፣ መተማመን ከሌለ መቀባበል የለም፣ መቀባበል ከሌለ ወዳጅነት የለም፣ ወዳጅነት ከሌለ አንድነት የለም፣ አንድነት ከሌለ ዕድገት የለም ፣ ዕድገት ከሌለ ራእይ የለም፣ ራእይ ከሌለ ውጤታማ አመራር የለም። ራእይ በሌላት ቤተ ክርስቲያን ያሉ ሰዎች በድግግሞሽ የታከቱ ናቸው።





በቤተ ክርስቲያናቸውም አዲስ አሠራርና የተለየ ሀሳብ ላይ ለመነጋገር ሁልጊዜ መሪዎቻቸው አይፈቅዱላቸውም። ሁሌ እንዲያደምጡ እንጂ አንዳንዴ እንኳ እንዲደመጡ ዕድል አይሰጡአቸውም። ስለዚህ ውስጣቸው እየጮኸ አንደበታቸውን ከመሪዎቻቸው ፍርሃት የተነሣ ለጊዜው ተለጉመው ይመላለሳሉ። በፍርሃት የተሸበበው አንደበት አንዴ ስከፈት ውጤቱ ለመሪው ሆነ ለተመሪው መልካም አይሆንም! ለመንጋው መበተን ምክንያት ሊሆን ይችላል። የግልጽነት እጦት ጦስ ቤተ ክርስቲያንን እያመሳት ነው።

የሕዝቡን የልብ ትርታ ለማድመጥ ያልታደሉ መሪዎች የሕዝባቸውን ውጫዊ ዝምታ የመንፈሳዊነት ምልክት አድርገው ይቆጥራሉ። ግልጽነት በሌለበት ቤተ ክርስቲያንና የአገልግሎት መርሐግብርን ብቻ መፈፀምና ማስፈፀም በነገሠበት ቦታ ተከታዮች አሮጌውን ሀሳብ ኮፒ እንዲያደርጉ እንጂ አዲስና የጊዜውን ሀሳብ መውሰድም ሆነ ማሳደግ እንደ አለመታዘዝ ይቆጠርባቸዋል። ሁልጊዜ እግዚአብሔር ለመሪዎቻቸው እንጂ ለእነርሱ እንደሚናገር ለማመን ይቸገራሉ። «እንደተገለጠልህ ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ» (ዕብ.8፡ 5) የተባለው ቃል *«ከዚህ በፊት እንደተደረገው ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ»* በሚል ያልተጻፈ ሕግ ተተክቶ ይኸውም እያንዳንዱን አገልግሎትና በአካባቢው የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፣ ይመራል። በግልጽ መለኮታዊ ራእይ በምትመራው ቤተ ክርስቲያን እውነቱ የዚህ ተቃራኒ ነው።

ራእይ መር አመራር ባለበት ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳን አዳዲስ ሀሳቦችና አተያዮች ሁሉ ወዲያው ተቀባይነትን ያገኛሉ ባይባልም ያለ አዳዲስ የጊዜው ቃልና አሠራር ወደ ፊት መጓዝ ስለማይታሰብ አባላት ከዘለማድ አተያይ

እንድላቀቁ ጠንካራ ትምህርት ሁሌ ይሰጣቸዋል። የተለመደውን ሥራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትነቱን ባለቀቀ፣ ትውልድና ዘመኑን ባገናዘበ መልኩ በአዲስና በላቀ መንገድ ለመሥራት ሁሉም ይተጋሉ። አዳዲስ አቀራረቦች፣ ፈጠራዊ ሂደቶችና ልዩ ልዩ አቅምን የሚያሳድጉ ግብአቶች ተቀባይነት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ራእይን ሁልጊዜ ትኩስና ሕያው የሚያደርጉ ቅመሞች ተደርገው ይቆጠራሉ።

ራእይ መር በሆነች ቤተ ክርስቲያን ባለው ግልጽነትና ነጻነት ሰዎች እጅግ በጣም ደስተኞች ከመሆናቸው የተነሣ በእያንዳንዱ እርምጃ የድርሻቸውን ሲወጡ በግዴታ ሳይሆን በባለቤትነት መንፈስ ነው። መለኮታዊ ራእይ መር በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ምንም እንኳ የራሳቸው ድካም፣ ጉድለት፣ ያለመቻል ቢኖርባቸውም ለራእይው ስኬት አንድ ነገር ማድረግ እንደሚችሉ ያምናሉ። በድፍረትም ይናገራሉ፤ ያደርጋሉም። ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያን «የብርቱዎች» ብቻ ሳትሆን የእነርሱም እንደሆነችና ቦታም እንዳላቸው ይረዳሉ። ይህ ራእይ በአንድ ቤተ ክርስቲያንና አገልገሎት የሚያመጣው አስደናቂ የግልጽነት ውጤት ያመለክታል።

## ጥቅም 3 መነሻና መድረሻን ማሳወቅ

መድረሻውን የማያውቅ መነሻውንም አያውቅም። «መሄዳችንን እንጂ የት እየሄድን እንዳለን አናውቅም» የሚሉ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ብዙዎች ናቸው። መድረሻቸውን ለይተው በማወቅ ጉዞ ያልጀመሩ ቢደርሱም አያውቁትም። መነሻው ላይ ከመጠን በላይ የቆየ ሰው መነሻውን እንደ መድረሻው የመቁጠር አደጋ ውስጥ መግባቱ አይቀሬ ነው። መድረሻን ሳያውቁ መጓዝ ጊዜን፣ ገንዘብን፣ አቅምን፣ ጉልበትን፣ ዕድሜን ወዘተ በከንቱ ማባከን ነው። ለብዙዎቻችን ክርስትና ማለት ጌታን መቀበል፣ መጠመቅ፣ የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን፣ የክትትልና የአገልግሎት ትምህርት መማር፣ ቅዱስ ቁርባን መውሰድ፣ የአገልግሎት ትምህርት መማር፣ በልሳን መናገር፣ በአንዱ የአገልግሎት ዘርፍ መታቀፍና በእሁድ አምልኮ ላይ ሁሌ መገኘት ማለት ሆኗል። እነዚህ ሁሉ አስፈላጊነታቸው ባያጠያይቅም በጌታ የመሆን ምስጢር ግን ከዚህም ያልፋል።

ክርስትና ሳይወለዱ አርጅቶ መሞት ሳይሆን ተወልዶ፣ በጌታ አድጎ ፍሬን በማፍራት የዓለምን ፊት የመሸፈን አስደናቂና ራእይ መር የሕይወት ምዕራፍ ነው። ይህን ዓይነቱን ሕይወት ለመለማመድ ቁልፉ የቤተ ክርስቲያን አባልነት ብቻ ሳይሆን የጌታ ልጅነትን አውቆ ራእይን ከእርሱ በመቀበል መነሻና መድረሻ ባለው መንገድ ላይ መገለጥ ነው።





በቤተ ክርስቲያን ያሉ ብዙ ሰዎች ምንም ሳይሮጡ አሸንፈው ሽልማትን በመጠበቅ ላይ የሚገኙ «ባለድሎች» ይመስላሉ። የመለኮታዊ ራእይ አንዱ ጥቅም እያንዳንዱን ቀን በአግባቡ እንድንጠቀምና ወደ ተያዘልን ግብ እንዲንሮጥ አቅምና ጉልበት መሆኑ ነው። መለኮታዊ ራእይ መነሻና መድረሻ ያለው የአገልግሎት ሕይወት እንዲኖረን ያደርገናል። ግልጽ የአገልግሎት ራእይ ባለቤቶች ስንሆን ከየት ተነሥተን የት እንዳለን፣ ወደምንሄድበት ለመድረስ ምን ያህል እንደቀረን፣ ለጉዞአችን ምን ዓይነት ግብአቶች እንደሚያስፈልጉን፣ ከየት እንደምናገኛቸው፣ መቼ እንደምንደርስና ስንደርስ ምን እንደምንሆን በሚናባችን ስናይ የጉዞውን ሕመምና አስቸጋሪ ውጣ ውረድ እንረሳለን። በሕይወት ከየት ተነሥተን ወዴየት መሄድ እንዳለብንና ያሰብነው ጋ መቼ መድረስ እንዳለብን ለማወቅ ከፈለግን ራእይ መር ሕይወት ሊኖረን ይገባናል።

## ጥቅም 4 ቀጣይነት

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አንዱና ትልቁ ጥያቄ የቀጣይነት ጥያቄ ነው። የአንድ አገልግሎት ቀጣይነት የሚወስነው በራሱ በአገልግሎቱ ሳይሆን አገልገሎቱ በተጀመረበት ራእይ ይሆናል። ብዙ ጊዜ የአገልግሎቱ ጀማሪዎች ራስ ተኮር ሲሆኑ፣ የሌሎችን ተሳትፎና ሚና ዝቅ አድርገው ሲቀርጹ፣ ቀጣዩን ትውልድ ያቀፈና ያለፈ የመጠቀ እይታ ድሆች ሲሆኑ ለራስ ኖረው ለራስ የመሞት አደጋ ውስጥ ይወድቃሉ። እውነተኛና የተሳካለት መሪ ስኬቱና ውድቀቱም ጎልቶ የሚወጣው እርሱ በመራበትና ባገለገለበት ዘመን ሳይሆን ከመሪነቱ ቦታ ከተነሣ በኃላ ነው። ለዚህም ትልቅ ምሳሌ የሚሆንልን በዘመኑ የገነነና ዝናው በዓለም ሁሉ የናኘ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ከመሪነት ወንበሩ ከተነሣ በኃላ ገዝፎ የወጣው ለሕዝቡ ያደረገው ሳይሆን በሕዝቡ ላይ ያደረገው፣ ለሕዝቡ የሠራው ሳይሆን በሕዝቡ ላይ የሠራውን ጭካኔ ሕዝቡ በአደባባይ ሲያወግዝና የረዳት ያለህ! እያለ ለተተኪው መሪ ብሶቱን ለልጁ ሲያቀርብ *«አባትህ ቀንበር አከብዶብን ነበር አሁንም: አንተ: ጽኑውን የአባትህን አገዛዝ በላያችንም የጫነውን የከበደውን ቀንበር አቃልልልን»*(1ነገ:12:4) ሲል እንመለከታለን ::

ራእያችን ቀጣይነት እንዲኖረው ከተፈለገ ትኩረቱ በእኛና በዘመናችን ላይ ሳይሆን በዘመናት ሁሉ ገዢ በሆነው ጌታና በመጪው ትውልድ ላይ ሊሆን ይገባል።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥፍራቸውን በተለያየ ምክንያት ሲለቁ በእነርሱ የተጀመረው አገልግሎት የቀጣይነት አደጋ የሚገጥመው ከዚህ የተነሣ ነው። ባለራእይ ለራስ ኖሮ ለራስ ለመሞት የሚታገል ታጋይ ሳይሆን በእርሱ መስዋዕትነት የራእይ ችቦ እያቀበለ ለትውልድ ሁሉ ሞቶም በሥራው የሚናገር አገልጋይ ነው።

አንድ ጊዜ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ በብዙ የተናኘለት ዋቢ አገልግሎት የነበራቸው በሕይወት እያሉ በአራትና አምስት ዓመት ሳያድጉ ያረጁ አገልጋዮችና አገልግሎቶች በቤተ ክርስቲያን ጥቂቶች አይደሉም። ለዚህም አንዱ ምክንያት በጊዜያዊ ሙቀትና የአገልግሎት ግብዣ ንፋስ ብርታት ከመሮጣቸው በፊት ቁጭ ብለው ምን ያህል እንደሚሮጡ፣ የሚሮጡለትን የተለየ ግብና ስጦታ ሳይለዩ፣ ከየት ተነሥተው የት ለመድረስ ግልጽ ዕቅድ፣ መነሻና መድረሻው በሁሉም የታወቀ ራእይ ስለሌላቸው ይመስለኛል።

እነዚህን የትላንቱ መንፈሳዊ ሩጫ ኃያላን ዛሬ የመንፈሳዊ ሩጫ ሃያስያን ቀጣይነት የከለከላቸውና ባለፈው ወርቃማ ዘመን የአገልግሎታቸው ሰንደቅ ዓላማ ሥር ቁጭ ብለው እንዲያወሩ ያስገደዳቸው የመለኮታዊ ራእይ እጦት ነው። በድንቅና በታምራት እንዲሁም በትንቢት የታጀበ አገልግሎት ራእይን ሊያግዝ ቢችልም በራሱ ራእይ ሊሆኑ ግን አይችሉም። ይህ ሁሉ ኖሮአቸው በማለዳው ከሩጫው ሜዳ የውጡ አገልጋዮች ቁጥራቸው ቀላል አይደለምና። ብዙዎች የኪስ አጀንዳቸውን ያጣበበው ተጠርተውበት የሚያገለግሉበት የኮንፍራንስ፣ የማነቃቂያ፣ የክሩሴድ ፕሮግራም እንጂ በእነዚህ አገልግሎት ባይጠሩ በተሰጠኝ ራእይ ይህን አደረጋለሁ የሚል የተጨበጠ ነገር የላቸውም። ባለራእይ በተከፈተው በር ብቻ ሳይሆን የተዘጋውን በር በመለኮታዊ ራእይ ኃይል ከፍቶ የማገልግል አቅም አለው። ለመሆኑ ወጥቶ ለማገልግል ሁሌ ደብዳቤና የስልክን ጥሪ መጠበቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይሆን? በዘመናችን የመንፈስ ቅዱስ ምሪት በስልክና በደብዳቤ ተለውጦ ይሆን? አገልግሎት ከቤተ ክርስቲያን የሚመጣ የኮንፍራንስና የማነቃቂያ ደብዳቤና ስልክ ብቻ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ባልተተከለባቸው ሕዝቦችና አካባቢዎች ማን በደብዳቤ ይጥራን? ማን ስልክ ደውሎ ለኮንፍራንስ ይጥራን?





ራእይ ለሚጠሩን ብቻ ሳይሆን ለማይጠሩንም ተደራሽና ደራሽ ያደረገናል። ይህም የአገልግሎታችን ቀጣይነት አንዱ ማስረጃ ነው። ጌታ ይርዳን።

## ጥቅም 5: ቅደም ተከተል

እያንዳንዱ ሰው የራሱ ውስንነት አለው። የጊዜ ውስንነት፣ የአቅም ውስንነት፣ የዕውቀት ውስንነት፣ የኃይል ውስንነትና የገንዘብ ውስንነት፣ የዕድሜ ውስንነት። በዚህ ሕይወት ሁሉን በአንዴ ያለው ሰው የለም። ራእያችን እያንዳንዳችን ባለን ውስንነት መሠረት ለየትኛው ሥራችን ልዩ ትኩረትና ጊዜ መስጠት እንዳለብንና የትኛውን ጉዳይ እግረ መንገዳችንን መሥራት እንዳለብን ለሥራችን ቅደም ተከተል ይሰጠናል። ዓለምን በወንጌል ለመድረስ ባለራእይ ከሰፈር ይጀምራል። በታላላቅ ነገሮች ላይ ለማዘዝ በትንንሽ ነገሮች ላይ በመታዘዝ ያስመስክራል። ላይን እይቶ እግረ መንገዱን በታች ማለፍ አይፈራም። ባለራእይ አገልግሎትን ከመድረክ ወደ ቤቱ ሳይሆን ከቤቱ ወደ መድረክ ያሳድገዋል።

የምናደርጋቸው ምርጫዎችና ውሳኔዎች ወደ ራእያችን ያቀርቡናል ወይም ከራእያችን ያርቁናል። በሕይወታችን ግልጽ ራእይ ሲኖር መንገድ በመሰለ ሁሉ ላይ መሄድ ሳይሆን በሚገባን መንገድ ላይ ብቻ እንድንሄድ ያደርገናል።

## ጥቅም 6: ትልቅ እይታ

እይታችንን በሚናውቀውና በለመድነው የሀሳብ ሜዳ ስንገድበው በመጪው ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ መፍጠር አንችልም። ይህም በክረምት ብርድ አጭር ብርድልብስ እንደ ለበሰ ሰው ሳንነቃና ሳንተኛ እንድንኖር ያስገድደናል። እግዚአብሔር ላንተ ያለውን ትልቁን ራእይ ማየትና መረዳት ስትጀምር ከትንሹ እይታህ በላይ ከመሆኑ የተነሣ ከተለመደው ሀሳብህ ጋር ጦርነት ውስጥ መግባቱ የግድ ነው። የባለራእይ ትልቁ ድል ዓለምን ሳይሆን ራስን ማሸነፍ ነው። ከብዙ ትግልና ግጭት በኋላ የእግዚአብሔር ራእይ እኛ ለራሳችን ካለን ግምት በላይ የመጠቀና የጠለቀ መሆኑን ስንገነዘብ በውዴታ ለመማረክ እጅ እንሰጣለን። ለመለኮታዊ ራእይ እጅ እንደሰጠን ስለ መጪው የምናይበትና የምንጫወትበት የሀሳብ ሜዳችንም በተቀበልነው ራእይ ልክ ይለጠጣል። ያልሰፋ ልብ ሰፊ ሀሳብ

መሸከም አይችልም:: ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተለመደውን አንድ ዓይነት አሠራር ስለሚከተሉ ቶሎ ይዝላሉ:: በትንሽ እይታም ይሰቃያሉ:: እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለው ራእይ ግን እነርሱንና ልምዳቸውን የሚመስል ትንሽ ሳይሆን እራሱን የሚመስል ትልቅ ነው:: እግዚአብሔር ራእይን ሲሰጠን በትንሹ እይታችን ውስጥ ሆነን ራሳችንን እንድናይ ሳይሆን በትልቁ የዘላለም ራእይ ውስጥ ገብተን ዓለምን እንድናይ ፈልጐ ነው:: ትልቁ እግዚአብሔር ለልጆቹ ትንሽ ራእይ የለውም:: የእግዚአብሔር ራእይ ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ በአንድና በሁለት ዓመት ሠርተን የምንጨርሰው ሳይሆን ትውልድን የሚጠቀልል አንዳንዴ በእኛ የሕይወት ዘመን እንኳ ዳር ለማድረስ የማንችለው ሊሆን ይችላል::

ሙሴ ያየውንና የተቀበለውን ራእይ ኢያሱ እንዳስጨረሰ፣ ዳዊት የእግዚአብሔር ቤት የመሥራት ራእይን ተቀበሎ ልጁ ሰሎሞን እንደጨረሰ አንተም ተቀብለህ ሌሎች ሊጨርሱት ይችላሉ:: ዋናው ማን ተቀበለ? ማን ጨረሰ? ሳይሆን ትልቁ የእግዚአበሔር ራእይ መገለጡ፣ እግዚአብሔር እስካየለት ድንበር ሁሉ ማካለሉና እኛም ባለድርሻዎች የመሆን ዕድል ማግኘታችን ነው:: አንዳንዴ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራእይ ብለው ለቤተ ክርስቲያን የሚያካፍሉት ሀሳብ በመሪነት ወንበር ላይ ለሁለትና ሦስት ዓመት አገልግሎት ቆይታቸው መጠን ለክተው እንደሚሰፉት የራሳቸው ጥብቆ ለሌላው ጠባብ ስለሚሆን ለተከታዩ መሪና ሕዝብ አይመጥንም:: ትልቅና ግልጽ የእግዚአብሔርን ራእይ ተቀብለን ለሰዎች ማካፈል ስንጀምር ትልቅ መደነቅ፣ ውስጣዊ ተሐድሶና መነሣሣት በውስጣቸው ከመፈጠሩም አልፎ ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ምክራቸውን፣ ሕይወታቸውን ለራእይው ስኬት በግብአትነት ያለ ገደብ የሚያቀርቡ ይሆናሉ:: ራእያችን ከየት እንደሆነ ለማወቅ የራእያችንን መጠንና ትኩረት ማጤኑ በቂ ነው:: ራእያችን እኛን የሚመስል ትንሽ ከሆነ ከራሳችን ሲሆን ከእግዚአብሔር ከሆነ ደግሞ ትልቅ ነው:: ትልቅ ራእይ ሁሉ ከእግዚአብሔር ባይሆንም ከእግዚአብሔር የሆነ ራእይ አንዱ መለያው ግን ትልቅነቱ ነው:: ትልቁ እግዚአብሔር ወደ ትንሹ ሰው ትልቅ ራእይን ይዞ በመምጣት ከትንንሽ ሀሳቦቹ አለያይቶት ለትልቅ ሥራው መሣሪያ ያደርገዋል:: መለኮታዊ ራእይ ሰጭውን እንጂ ተቀባዩን አይመስልም::





## ጥቅም 7: ለውጥን መቀበል

መለኮታዊ ራእይ ለውጥን ቢንፈራውም እንድንቀበለው ግን ኃይል ይሆነናል:: መለኮታዊ ራእይ በገነነበት አንድ ጥሩ አሠራርም ሆነ ሀሳብ በተሻለው ለመለወጥ ብዙ አያታግልም:: አንድ ጊዜ ያነበብኩት ታሪክ ሁሌም አይረሳኝም::

*«በ1940ዎቹ የዓለማችንን የእጅ ሰዓት ገበያ ድርሻ 70% ተቆጣጥሮ የነበረው የስዊዝ ሰዓት ሲሆን በዓለም ሁሉ በውበት፣ በጥራትና በጥንካሬ አቻ ያልተገኘለት እንደነበር ይነገርለታል:: አንድ ቀን በዋጋ፣ በዲዛይን፣ በውበት፣ በዓይነት፣ በጥንካሬና በተፈላጊነቱም ቀዳሚ ሊሆን የሚችል አዲስ የሰዓት ዲዛይን አንድ ሰው ሠርቶ ወደ ዝነኛው የስዊዝ የሰዓት ፋብሪካ መጣ:: የፋብሪካውን ዋና አስተዳዳሪዎች ከሰበሰባቸው በኃላ እንዲህ አላቸው:: ፋብሪካችሁ በዓለም ሁሉ ስላለው ዕውቅናና ዝና ትልቅ አክብሮት አለኝ ከዛሬ ጀምሮ እስካሁን ትሠሩ የነበረው ሰዓት ሊተካ የሚችል የተሻለ ዲዛይን ይዤ መጥቻለሁ:: በቀጣዩ ዓለም ሁሉ የሚጠቀምበትን አዲስ ሰዓት ባላችሁ ስምና ዕውቅና ከእኔ በመግዛት እንድታሰራጩ በማለት አሳያቸው:: መሪዎቹም በእጃቸው የነበረውን የትላንቱን አዲስ የሁልጊዜ አዲስ አድርገው ስለቆጠሩ የአዲሱን ዲዛይን ጉዳይ መስማት እንኳ እንደ ስድብ ቆጠሩ:: በጣም ተናደው አንድ ዓለም ሁሉ ያደነቀውን ፋብሪካ አንድ ተራ ሰው እንዴት በድፍረት እንዲህ ይላል? በማለት ለልሀቀት የመጣላቸውን ለውጥ እንቢ አሉ:: እርሱም አልፎ ሄዶ ያን ዲዛይን አንድ ላልታወቀ የሰዓት ፋብሪካ ሸጠው:: ፋብሪካውም በሁለት ዓመት ውስጥ በአዲሱ ዲዛይን በዓለም ላይ ቀዳሚ ለመሆን ችሎዋል:: መጀመሪያ ዕድሉ የተሰጠው ፋብሪካ በትላንቱ አዲስ በዛሬው አሮጌ ሀሳብ ተከራርቶ የመጣለትን የጊዜውን አዲስ የለውጥ ሀሳብ ባለማስተናገዱ ከ5 ዓመት በኋላ 50% ሠራተኞቹን ለመቀነስ ተገዶ ከ10 ዓመት በኋላ ሙሉ በሙሉ ተዘግቶዋል ይላል::»*

ለውጥን እንቢ ብለን ባለራእይ መሆን በፍጹም አይታሰብም:: የእውነተኛ ራእይ አንዱ ምልክት ለውጥን ማምጣት ሲሆን አንዱ የራእይ ጥቅም ደግሞ ለውጥን የሚፈቅድ ሕይወት ባሌበት እኛን ማድረጉ ነው:: ብዙ ሰዎች ለውጥን እንደ ጦር

ስለሚፈሩ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ሳይራመዱና ትውልድንም ሳያራምዱ በትላንትና አዲስ በዛሬ አሮጌ አስተሳሰብና አሠራር ለራሳቸው ኋላ ቀርተው ትውልዱንም ወደ ኋላ ይጎትታሉ። መለኮታዊ ራእይ ባየለበት ቤተ ክርስቲያን ጊዜያዊ የለውጥ ፍርሃት ቢኖርም በመጸለይ የራእዩን ከተረዱ ወዲያው ለለውጡ ራሳቸውን ክፍት ያደረጋሉ።

ፍርሃትና ጥርጣሬያቸውን በመተው በለውጡ በመታገዝ በአንድ ልብ ራእይን ከግቡ ለማድረስ ይሰለፋሉ። እንዲህ ማለት ግን ተቃዋሚዎች እስከመጨረሻ አይኖሩም ማለት ግን አይደለም። ተከታዮች መሪያቸው ከእግዚአብሔር ተቀብሎ የሚያስተላልፈው ራእይ ሲገባቸው ለውጥን ይፈቅዳሉ። በመሪያቸው ላይ ባላቸው አመነታና ፍቅር እርሱ ለሚያቀርበው የለውጥ ጥሪ ቀኝ እጃቸውን ለመስጠት አይቸገሩም። ለውጥን እንድንቀበል ማድረግ የመለኮታዊ ራእይ አንዱ ጥቅም ነው።

## ጥቅም 8: ፍሬያማነት

ፍሬያማ እንድንሆን ተወስኖብናል። «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት» (ዘፍ. 1: 28) «እኔ ሕይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁ መጣሁ።» (ዮሐ. 10: 10) «..ፍሬ ልታፈሩ ... ሾምኋችሁ» (ዮሐ.15: 17) ተማሪ በትምህርቱ፣ ገበሬ በግብርናው፣ ነጋዴ በንግዱ፣ ባለትዳሮች በትዳራቸው እንዲሁም ሰዎች ሁሉ ፍሬያማነትን በብርቱ ይፈልጋሉ። የቤተ ክርስቲያን ፍሬያማነት የፍላጎት ብቻ ሳይሆን የመለኮታዊ ራእይ ውጤት ነው።

ለአንድ ቤተ ክርስቲያን የመለኮታዊ ራእይ ትልቁና ዋና ጥቅም ፍሬያማነትን በአገልግሎቷ ማጎናጸፍ ነው። የቤተ ክርስቲያን ስኬት የሚለካው በፕሮግራሞች፣ በአገልጋዮች፣ በአባላትና በገንዘብ ብዛት ሳይሆን በጠራውና ግልጽ በሆነው መለኮታዊ ራእይና ውጤት ይሆናል። ከላይ የዘረዘርናቸው በራሳቸው ክፉ ባይሆኑም የስኬት ምልክት ግን ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱም እነዚያ ሁሉ ኖሮአቸው ያልተሳካላቸው አብያተ ክርስቲያናትና አገልግሎቶች ብዙዎች ናቸውና።





አንድ አገልግሎት ስኬት የሚለካው ከተሰጠው ራእይ አኳያ እንጂ እኛ ስኬት ነው ብለን በሚንዘረዝራቸው ላይሆን ይችላል። እግዚአብሔር አንድ ሰው ሰባኪ እንዲሆን ጠርቶና ራእይ ሰጥቶት እያለ እርሱ የተሳካለት ነጋዴ ሆኖ አገልግሎቱን ቢጨረስ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያለው አይመስለኝም። ፍሬያማነት በራእያችን ውስጥ ተሰውሮአል።

## ጥቅም 9 ድፍረት

*«ዓለም በደፋር ጎጥአንና በፈሪ ጻድቃን የተሞላች ናት»* የሚለውን አባባል ባለራእይ ይስማዋል እንጂ አያምንም። አይቀበልም። ባለራእይ የሆኑ ሰዎች መለኮታዊ ራእይን አንግበው በእምነት ሲጓዙ፣ ከየት ተነሥተው የት እየሄዱና መቼ እንደሚደርሱ ያውቃሉ። ለምን እንደሚሄዱ መልስ ሲኖራቸው ተቃውሞን የመጋፈጥ፣ አስፈላጊ ዋጋን ሁሉ የመክፈልና በቃሉ ላይ የተመሠረተ ድፍሬት ባለቤቶች ይሆናሉ። መለኮታዊ ራእይ በነገሠበት ቤተ ክርስቲያን ያሉት ቅዱሳን በራእይ ለራእይ ከመኖራቸው የተነሣ በጌታ ቤት አገልግሎት ትልቅ እምነትና ድፍረት አላቸው። ከራሳቸው በላይ የሆነውን ማንኛውንም ተግዳሮት ለመግጠም አያቅማሙም፤ አቋራጭ መንገድንም አይቀይሱም። እግዚአብሔር ለታላቅ ነገር እንደጠራቸው ጠንካራና ውስጣዊ እርግጠኝነት ስላላቸው በተሰለፉበት በእያንዳንዱ ሥራዎቻቸውም የሚያስመዘግቡት ውጤት ከራሳቸው በላይ ትልቅ ነው። ለዓለም ለውጥና ለቤተ ክርስቲያን በረከት አንዳች ልዩነትን ሊፈጥር የሚችል ሚና መጫወት በመቻላቸውም ሁልጊዜ ደስተኞች ናቸው። ከተቀበሉት ታላቅ ራእይ ተነሳ የቤተ ክርስቲያን፣ የሀገርና የዓለም ተስፋ እንደሆኑ አፍ ሞልተው ያውጃሉ። «እንግዲህ ታላቅ ብድራት ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ» (ዕብ. 10: 35)

## መርሆዎች

- እግዚአብሔር ራእይን ሲሰጠን በትንሹ እይታችን ውስጥ ሆነን ራሳችንን እንድናይ ሳይሆን በትልቁ ራእይው ውስጥ ገብተን ዓለምን እንድናይ ነው::
- መለኮታዊ ራእይ ከትንንሽ እይታዎቻችን ጋር ያፋታናል::
- ባለራእይ ለራስ ኖሮ ለራስ ለመሞት የሚታገል ታጋይ ሳይሆን በእርሱ መስዋዕትነት የራእይ ችቦ እያቀበለ ለትውልድ ሁሉ የሚናገር ሰው ነው::
- የቤተ ክርስቲያን ፍሬያማነት  የሚለካው በፕሮግራሞች፣ በአገልጋዮች፣ በአባላትና በገንዘብ ብዛት ሳይሆን በጠራና ግልጽ በሆነው መለኮታዊ ራእይ ነው::
- መለኮታዊ ራእይ የመለኮታዊ ድፍረት ምንጭ ነው::
- አቅጣጫና ዓላማ ከራእይ ማሕፀን ይወለዳሉ፡
- መለኮታዊ ራእይ ለሥራችን ቅደም ተከተል ይሰጠናል:: መለኮታዊ ራእይ መነሻና መድረሻ ያለው የአገልግሎት ሕይወት እንዲኖረን ያደርገናል::
- ራእይ በነገሠበት ሥፍራ ለውጥ ቢፈራም አይጠላም::
- መድረሻውን የማያውቅ መነሻውንም አያውቅም::
- ራእይ መነሻ ላይ ቆሞ መድረሻን የማየት አቅም ሲሆን መለኮታዊ ራእይ ባለበት ቦታ የመድረሻ ጥያቄ ቦታ የለውም::





## <u>አይመጣም በምኞት</u>

*የዕውቀት ማህደር መሆን ብር ወርቅ መመዘን*
*በዘር ወይ በጎሳ በስልጣንም መግነን*
*ይኸ ሁሉ አይገዛው አይከረጅ ከሰው*
*እንደ እጀ ጠባብ ለፍተህ አትለብሰው*
*ደምህ ውስጥ ካልገባ ከላይ ከመለኮት*
*ባለራእይ መሆን አይመጣም በምኞት::*

ደረጀ መላቱ

# 3 ራእይን እንዴት እንቀበላለን?

*«አንዳንዴ ዓይን ማየት የማይችለውን ልብ ያያል::»*

*ጃክሰን ብራወን*

መለኮታዊ ራእይን እንዴት እንቀበላለን? የሚለው ጥያቄ የብዙ ሰዎች ጥያቄ ይመስለኛል:: ጆን ስቶት የእንግሊዝ ስመ ጥሪ የሥነ መለኮት ምሁር ሰዎች ራእይን መቼ እንደሚቀበሉ ስገልጽ *«አሁን እየሆነ ባለውና በሚንሠራው ሥራ ቅዱስ ያለመርካት የተነሳ የሚበልጠውን ውለጣችን ስፈልግ ራእይን እንቀባለን::»* ብሎዋል::

በዚህ ምዕራፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክና በሕይወት ካሉት ሰዎች እንዴት የመፈጠራቸውን ራእይ እንደተቀበሉ እንመለከታለን:: መለኮታዊ የአገልግሎት ራእይን የሚንቀበልበት መንገዱ ልዩ ልዩ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ መንፈሳዊ ራእይ አስቀድሞ በልባችን ካለው ሸክም ይወለዳል:: ለምሳሌ:- አንድ ሰው የማገልገል ሸክም አለው ማለት የጠራና የጠለለ የአገልግሎት ራእይ አለው ማለት አይደለም:: በልቡ ካለው ሸክም ግን መነሻና መድረሻ ያለው ግልጽ ራእይ ሊወለድ ይችላል:: ራእያችን በልባችን ሸክም ቢሆንም የልባችን ሸክም ሁሉ ራእይ መሆን ግን አይችልም:: ራእያችንን ለማወቅ በልባችን ጌታ ያስቀመጠውን ሸክም አስቀድመን ማወቅ የግድ ነው:: ለአንድ ነገር ሸክም ከሌለን ስለዚያ ነገር ራእይ ሊኖረን አይችልም::

እግዚአብሔር ድንገተኛና እኛ ለማድረግ የማንፈቅደውን ነገር ራእይ አድርጎ አይሰጠንም:: መለኮታዊ ራእይ ብዙውን ጊዜ በልባችን ከተቀመጠው ሸክም ጋር የተሳሰረ ነው::





የጥቁሮች መብት ተከራካሪ የነበረው ማርቲን ሉተር ኪንግ እ.ኤ.አ በኦገስት 28 1963 *«ሕልም አለኝ»*[22] በሚል ርዕስ ሥር ታሪካዊ ንግግር በማድርግ አሜሪካን ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የነቀነቀ እንቅስቃሴን ከመምራቱ በፊት *«ሰው በሰው ለምን ይጠላል? የቀለም መለያየታችን ለምን አንዱን የበላይ አንዱ የበታች ያደርጋል?»* የሚሉ ጥያቄዎችና ትልቅ ሸክም በውስጡ ነበር:: ከዚህ ሸክም የተወለደው ራእይ የዓለማችን ቀዳሚ የሰብዓዊ መብት ተሟጋችና በዓለም ሁሉ ካመጣው ተጽዕኖ የተነሳ ከተለያዩ ዩንቨርስቲዎች 50 የክብር ዲግሪዎች አስገኝቶለታል:: በዓለማችን ላይ በዕድሜ ወጣት ሆኖ እ.ኤ.አ በ1964 የኖቤል የሰላም ሽልማት ተሸላሚ አድርጎታል:: የዛሬይቷ አሜሪካ በዲሞክራሲ ላይ እንድትገነባና ነጭና ጥቁሩ በሕግ ፊት በእኩልነት የሚኖሩባት ሀገር እንድትሆን ትልቅ ሚና ተጫወቶአል:: ለራእይ ባለው ቆራጥ አቋሙ ገና በ39 ዓመቱ እ.ኤ.አ አፕሪል 1968 በሰው እጅ ቢገደልም ሥራው ለትውልድ ሁሉ እስከ ዛሬም ይናገራል::[23] ሰዎች የባለራእይን ሥጋውን ቢገድሉም ሥራውን መግድል አይችሉም::

## የነህምያ እንደገና የመገንባት ራእይ

ነህምያ ኢየሩሳሌምን ቅጥር ከፍርስራሽ መካከል በ52 ቀናት እንደገና የመገንባትና የተጠቃውን ሕዝብ ከትልቅ ስድብና አንገት መድፋት የታደገ ታላቅ ባለራእይ መሪ ነበር:: ስለ ነህምያ ሲነሳ ሁልጊዜ ራእይን ተቀብሎ ትልልቅ ነገር መሥራቱን እንጂ ከራእዩ በፊት ስለሕዝቡ ልዩ ሸክም እንደነበረው ሲነገር አይሰማም:: ነህምያ ለራሱ በጣም በተመቻቸና የፈለገውን ለማግኘት በማይቸገርበት በአርጤክስ ቤተ መንግሥት የንጉሡ የጠጅ አሳላፊ ሆኖ ይኖር ነበር:: ልቡ ከግላዊ ምቾትና ደስታ ባለፈ ሁሌ ስለ ሕዝቡና ስለ ኢየሩሳሌም ከተማ ትልቅ ሸክም እንደነበረው ቃሉ እንዲህ ይላል:- «እኔም የዳኑትን ከምርኮም የተረፉትን የአይሁድን ነገር የኢየሩሳሌምንም ነገር ጠየቅኋቸው::» (ነህ 1: 3):: ነህምያ የነበረበት ፈንጠዚያ፣ ድሎትና ሙላት *«ለእኔ ይድላኝ እንጂ!»* በማለት በስድብና በጉስቁልና ምጣድ ላይ እየተጠበሰ ለነበረው ሕዝቡ ሸክመ ቢስ አላደረገውም:: ነህምያ ሕዝቡ ለነበረበት

22 *Hansen, D, D. (2003). The Dream: Martin Luther King, Jr., and the Speech that Inspired a Nation. New York, NY: Harper Collins. p. 177.*

23 *http://en.wikipedia.org/wiki/Martin_Luther_King,_Jr.*

ፈታኝ ሁኔታ ከንፈር ከመምጠጥ ያለፈ በምዕራፍ አንድ ላይ ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስና ስለ ሕዝቡ ጉስቁልና ልቡ ተሰብሮ በእግዚአብሔር ፊት በንስሃ ወደቀ:: እንደገና የኢየሩሳሌምን ቅጥር የመገንባት፣ የሕዝቡን አንገት ቀና ለማድረግና የእግዚአብሔርን ክብር ለማስመለስ «አይቼም ተነሣሁ» (ነህ: 4: 10) በማለት ራእይን ይዞ እንደ ተነሣ ይገልጻል::

ነህምያ በአይቻልም ውስጥ ይቻላልን፣ በጨለማ ውስጥ ብርሃንን፣ በፍርስራሽ ውስጥ ግንባታን፣ ሀገሩንና ሕዝቡን ለዘመናት በተጫነው ሸንፈት፣ ጉስቁልና ላይ በራእይ ኃይል በመነሣትና በራሱ በመወራረድ የተገለጠ ሰው ነበር:: በንጉሡ ፊት ቀርቦ ቁርጥ ውሳኔውን ሲገልጽ *«እሠራው ዘንድ ወደ ይሁዳ ወደ አባቶቼ መቃብር ከተማ ስደደኝ አልሁት::» (ነህ. 2: 6)*:: ይላል:: በዚህም ነህምያ ሸክሙ ወደ ራእይ ተለውጦ ዝም ብሎ ከማዘን ወደ ጨካኝ የእምነት እርምጃ እንዳስገባው ማየት የራእይና እርምጃ አንድነትንና ልዩነት ያመለክተናል:: ነህምያ የራሱን ምቾት መስዋዕት በማድረግ በራእይ ያየውን በገሀድ ዓለም ለማሳየት በእምነት እንደወጣ ሁሉ ዛሬም ከእውነተኛ ባለራእይዎች ይህ ይጠበቃል:: ባለራእይ ላየው ራእይ በነፍሱ ተወራርዶ በመንፈሳዊ አውደ ግንባር ላይ ይገኛል እንጂ በሌሎች ሞት ለመንገሥ በምቾት ጥላ ሥር ሆኖ አይጠብቅም:: እርምጃ የሌለው ራእይ ውሃ ከሌለው ባዶ ደመና ጋር ይመሳሰላል::

## ለሥራ የማያስጨክን እንባ

ብዙዎቻችን ሀገራችንና ሕዝባችን ያለበትን ድህነትና ኋላ ቀርነት ስንመለከት ሙሉ ቀን ሳይሆን ሙሉ ዓመት የማውራትና የማልቀስ ሸክምና አቅም ያለን መሆናችን በራሱ በቂ አይደለም:: ሸክሙ ራእይን ፀንሶ ራእዩም አዲስ የመፍትሔና የእምነት እርምጃን ካልወለደ በስተቀር እንባ ብቻውን ለውጥና ታሀድሶ በምድራችን አያመጣም:: ሸክማችን ራእይን ወልዶ በተግባር ሜዳ ካልገለጠልን ስለ ለውጥ ለማውራት እንጂ ለውጥን ለማምጣት ብቁዎች አያደርገንም:: ዛሬ ብዙ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ለምን እንደዚህ እንደሆነች የጠለቀና የመጠቀ ጥናትና ምርምር እንዲሁም ትንታኔ ለመስጠት መቻላቸው፣ ስልጠናዎችና ምክክሮች መደረጋቸው





አንድ ትልቅ ነገር ነው:: የጥናቱ ውጤት እንደገና የመሥራትና የመገንባት ራእይን አስጨብጦን ወደ ተፋፋመው መንፈሳዊ የጨበጣ ውጊያ ለመግባት ካላስቻለን በስተቀር ለውጥን ለመስበክና ለመዘመር እንጂ ለውጥን ለማየት አንችልም:: ነህምያ ከሸክም ራእይ ተወልዶ ወደ ተግባር ሜዳ ካሻገረው በኋላ እንዴት ይሠራ እንደነበር እንዲህ ይገልጻል *«ለጥብቁ የቅጥሩን ሥራ ሠራሁ::»* (ነህ. 5: 16)

ነህምያ የነገሮችን ቅደም ተከተል ያወቀ ብቻ ሳይሆን በተግባር ሜዳም ትግልን ከአንጸባራቂ ድል ጋር ያሳየን ታላቅ ባለራእይ መሪ ነበር:: ነህምያ ብርቱ የጸሎት ሰው ብቻ አልነበረም:: መረጃን በማሰባሰብ የሚያምን፣ በእውነት፣ በእምነትና በጥበብ እንጂ በስሜት የማይነዳ፣ የማያመቻምች ታላቅ ዲፕሎማት እንደ ነበር ታሪኩ በግልጽ ያሳየናል:: በተጨማሪም ነህምያ ሠርቶ የሚያሠራ ብርቱ ሠራተኛ ፣ ከራሱ በላይ የሚኖርለትን ዓላማ ያገኘ፣ የጸሎትና የእርምጃን ጊዜ ለይቶ የሚያውቅ፣ መልካም ቀንና ሁኔታን የማይጠብቅ ነገር ግን በተሰጠው ራእይ ጉልበት በክፉ ቀን መልካምን ቀን ለመፍጠር የቆረጠና በራእይው መንገድ ለራሱ ሞቶ ሀገርን ለማኖር የተሰጠ ታላቅ ባለራእይ መሪ ነበር::

ባለራእይ በጸሎት ጊዜ እርምጃ አይወስድም:: በእርምጃም ጊዜ ለጸሎት አይንበረከክም:: ባለራእይ መቼ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንዳለበትና ለመሥራት መቼ መውጣት እንዳለበት ቦታውን፣ ማንነቱን፣ የተሰጠውንና ስጭውንም በጥንቃቄ ለይቶ ያወቀ ሰው ነው:: በሀገራችን ባለችው ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ባለራእይ ነን የምንል ብዙዎች ቅድምያ ለሚገባው ቅድምያ የመስጠት ችግር ጎልቶ ይታይብናል::

በተግባር ጊዜ ለጸሎት ምሽግ እንገባለን በጸሎት ጊዜ እርምጃ ለመውሰድ እንጣደፋለን:: ድግግሞሽና በአንድ ቦታ መሽከርከር በቅደም ተከተል ቀውስ ውስጥ እንዳለን አመልካች ነው::

## የዕንባቆም ሸክም

ብዙውን ጊዜ ሰዎች በዕንባቆም 2:2 ላይ ስለተገለጠው «ራእዩን ጻፍ በጽላትም ግለጸው» ስለሚለው ቃል ሲናገሩ ይህ ራእይ ከዕንባቆም 1:1 ትልቅ ሸክምና ክርክር እንደተወለደ ይዘነጉታል:: ከዚህ የሚንማረው ትልቁ መርህ ማንኛውም እውነተኛ ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ራእይ በልባችን ከነበረው ሸክም ጋር ተያያዥ መሆኑን ነው::

> *«ነቢዩ ዕንባቆም ያየው ሸክም ይህ ነው:: አቤቱ እኔ ስጮኽ የማትሰማው እስከ መቼ ነው? ስለ ግፍ ወደ አንተ እጮኻለሁ አንተም አታድንም:: በደልንስ ስለምን አሳየኸኝ? ጠማማነትንስ ስለ ምን ትመለከታለህ? ጥፋትና ግፍ በፊቴ ነው ጠብና ክርክር ይነሣሉ:: ስለዚህ ሕግ ላልቶአል ፍርድም ድል ነሥቶ አይወጣም ኃጢአተኛ ጻድቅን ይከብባልና ስለዚህ ፍርድ ጠማማ ሆኖ ይወጣል:: »* (ዕን. 1: 1 - 4)

ነቢዩ ዕንባቆም ትልቅ ሸክም ለሕዝቡና ለምድሩ ስለነበረው ከሚያየውና ከሚሰማው እመጽና ኃጢአት የተነሣ ውስጡ ስለደማ ከሕዝቡ ጋር እንዲህ እያለ ሰቆቃውን ያሰማ ነበር «እስከ መቼ?» «ኃጢአት በሕዝብህ ሕይወት እስከ መቼ ይነግሣል?» በማለት በእግዚአብሔር ፊት ይቃትት ነበር::

ይህ ጠንካራ ሸክምና ጬኸት ራእይ እንዲወለድ ምክንያት ሆኖአል:: ራእይና ሸክም የተጣመሩ ቢሆንም ሸክም ከራእይ ይቀድማል:: እግዚአብሔር የማይዛመድ ሸክምና ራእይ አይሰጠንም:: በመጀመሪያ ሸክምን በሕይወታችን ካስቀመጠ በኋላ ያ ሸክም ሥጋ ለብሶ በሕያውነት ራእይ ሆኖ በገሀዱ ዓለም ይወለዳል::

ሸክም በልባችን ውስጥ እግዚአብሔር የሚያስቀምጠው ጥቅል ሀሳብ ሲሆን ራእይ ደግሞ ስለዚያ ሸክም እንድንሠራበት የሚሰጠን እግዚአብሔር በሕይወታችን የገለጠው አንድ ገዢ አጀንዳ ነው:: እግዚአብሔር ልናደርገው የማንወደውን ወይንም እንድናደርገው ያላስታጠቀንን እንድናደርገው አይልከንም::





በመጀመሪያ እንድናደርገው ስለሚፈልገው ነገር አስቀድሞ ያስታጥቀናል:: እግዚአብሔር ራእይዩን እንድንፈጽም ከመላኩ በፊት በውስጣችን ካስቀመጠው ሸክም ራእይን የምንፈጽምበትን ክህሎትና ጉልበት ይሰጠናል::

እግዚአብሔር የጊታርና የመስንቆን ልዩነት የማያውቅ ሰው ድንገት ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ጊታር እንዲጫወት ልዩ ራእይ ሰጥቶት ወዲያው መድረክ ላይ አያወጣውም;: አንድ በእርግጠኝነት ለመናገር የምፈልገው ነገር እግዚአብሔር ሰውየው የማይወደውንና ፍጹም የማያውቀውን ነገር እንዲያደርግ ድንገት ጠርቶት ወዲያውም አይልከውም:: አንድን ነገር ለማድረግ ሸክም ከሌለህ፣ ምንም አይነት ምኞቱም ሆነ መሰጠቱ ከሌለህ፣ ምንም አይነት ችሎታም ሆነ ፍላጎት ከሌለህ፣ ዕውቀቱም ሆነ የማድረግ ሙቀቱ ከሌለህ እግዚአብሔር እንድታደርገው አይልክህም::

በሀገራችን የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ የሚማሩት በውስጣቸው ባለው ዝንባሌ ላይ ተመርኩዘው ሳይሆን ገንዘብ ሊያስገኝላቸው የሚችለውን ትምህርት ቅድሚያ በመስጠት ሲሆን ያንንም የሚያኙት ከመቶ አሥር የማይሞሉቱ ናቸው:: ዘጠናውም እጅ በማይፈልጉት ባዶ ቦታዎች የመደልደል እንጂ ውስጣቸውን የሚያደምጥላቸው አካልም ሆነ አካሄድ እስካሁን ያለ አይመስልም::

ከዚህም የተነሣ ብዙዎች ራሳቸውን ያላገኙ ተመራቂዎች፣ ባልፈለጉት መንገድ እንዲሄዱ የተገደዱ ደሞዝተኞች አድርገው ራሳቸውን ይቆጥራሉ:: ተመርቀው ከወጡ በኋላ ሥራቸውን ለመኖር ከመሥራት ያለፈ ፈጠራን አክለውበት ትልቅ ነገር ለማድረግ ውስጣዊ ተነሳሽነት ስለሚጎላቸው ከአቅም በታች በመጫወት ዕድሜያቸውን ለመጨረስ ይገደዳሉ:: ራእይ ካለ ግን ይህን ሁሉ አልፎ መሄድ ይቻላል:: ሰው በልቡ የሌለውን ማድረግ ቀላሉም ከባድ ሸክም ሲሆንበት በልቡ ያለውን ከባዱን ቀላል የሚያደርግ በፍቅርና በመስጠት መሥራቱ ነው:: የአንድ ሰው ብልጽግና፣ ደስታ፣ ስኬቱ፣ ድሉ፣ ኃይሉ፣ ከፍታውና ቅባቱ የተቀበረው በልቡ ውስጥ ባለው ሸክሙ ውስጥ ነው::

በቤተ ክርስቲያንም ብዙ አገልጋዮች ከጥሪያቸው ጋር የሚተላለፉት እግዚአብሔር በጊዜው ካሸከማቸውና ከውስጣዊ ፍላጎታቸው ጋር በማይሄድ አቅጣጫ ለመኖር ብለው ከተያዘላቸው ትልቅ መለኮታዊ ሀሳብ ጋር ስተላለፉ ይታያሉ። ሁሉ ነገር የሚጀመረው ከሸክም ነው። ለምን እንደተፈጠርክ የፈጠረህን ሳትጠይቅና ውስጥህን ሳታጤን ምን መሥራት እንዳለብህ ሰዎችን ሆነ ገበያውን አታማክር። ገበያው ከአንተ ስለሚፈልገው እንጂ ውስጥህን አጢኖ እግዚአብሔር ካንተ ምን እንደሚፈልግ የመንገርም ሆነ የመምከር አቅም የለውም።

እግዚአብሔርም ሸክምን በአንተ ውስጥ ሲያስቀምጥ የገበያውን ሁኔታና አንተንም አይቶህ ሳይሆን የተፈጠርክለትን ዘላለማዊ አጀንዳ አይቶ ስለሆነ እርሱ የሚያይልህ ሁሌ ትክክለኛውና የሚበልጥ ነው። ነገ ትልቅ ራእይ የሚወጣው ዛሬ በውስጥህ ካለው ሸክም ነው። ራእይህን ለማወቅ እግዚአብሔር በውስጥህ ያስቀመጠውን ሸክም ማወቅ ይቀድማል።

## ህንድን በወንጌል የመድረስ ራእይን የሰነቀ ጫማ ሠፊ

*መጋቢ ዶክተር ጆን ራይላንድ እ.ኤ.አ በ1783 የ22 ዓመት ወጣት ዊልያም ካሬን* በውሃ ባጠመቀበት ቀን በአውደ ዕለት ማስታወሻው ላይ *«ዛሬ አንድ ድሃ ጫማ ሰፊ ወጣት የውሃ ጥምቀት ወስዶዋል»*[24] ብሎ አስፍሮ ነበር። ወጣቱ ጫማ ሰፊ ዊልያም ኬሪ ድህነቱ ሳያግደው እንዲህ ብሎ ተነሣ *«ትልቅ ነገርን ከእግዚአብሔር ጠብቅ ትልቅ ነገርንም ለእግዚአብሔር ለማድረግ ተነሥ»*[25]። ዊልያም ኬር እንዳለው ኖሮ ያለፈው በድህነት በተከበበች ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ለህንድ የመትረፍ ራእይ ይዞ በመነሣት ነበር። ኬሪ አስደማሚ ስኬት ከማስመዝገቡ በፊት በትንሹ የጫማ መሥፊያ ቤቱ ግርግዳ ላይ ትልቅ የዓለም ካርታ በማንጠልጠል በውስጡ ካለው ሸክም የተነሣ ለዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት በትጋት ይጸልይ እንደነበር ታሪኩ ይናገራል። እግዚአብሔር ታላቅ የሚስዮናዊነት ራእይ ሰጥቶት ወደ ህንድ ሳይልከው በፊት ትልቅ ዓለም አቀፋዊ የወንጌል ሸክም ሰጠው። ይህ ሸክም

[24] *http://www.wholesomewords.org/missions/biocarey.html*

[25] *http://thinkexist.com/quotation/expect-great-things-from-god-attempt- great-things/411686.html*





*ራእይን ወልዶ እግዚአብሔር በዚህ ተራ ሰው ሕይወት ያደረገው ታላላቅ ሥራዎች ለትውልድ ሁሉ ተምሳሌት ከመሆን አልፎ ለኬርም «የዘመናዊ ሚስዮናዊነት አባት»*[26] የሚል ቅጽል ስም አስገኝቶለታል። ዊልያም ኬር በልቡ ከነበረው የአገልግሎት ሸክም ህንድን በወንጌል የመድረስ ትልቅ ራእይ ተወልዶ፣ አድጎና አፍርቶ ለዓለም በረከትና ተምሳሌት ሆኖአል።

እግዚአብሔር ከልጅነትህ ጀምሮ በውስጥህ ያስቀመጠው ልዩ ሸክም ምንድነው? ከሁሉም ውስጥህ የሚረካውና የመንፈሱን ውስጣዊ ምስክርነት የምታገኘው ምን ስትሠራ ነው? እግዚአብሔር ለስሙ ክብር ለሰዎች ልጆች መዳንና በረከት የሚሆን ምን የተለየ ራእይ በውስጥህ አስቀምጦአል? በመንፈሱና በቃሉ ውስጥ ሆነህ ስጦታህን፣ ችሎታህንና የቅዱሳንን ምስክርነት አንድ ላይ ስታመጣ በውስጥህ በግልጽ የሚታይህ አንድ ነገር ምንድነው?

ዊልያም ኬር ህንድን በወንጌል የመድረስ መለኮታዊ ራእይ ሊቀበል በግሉ በምን አይነት አሳዛኝና ፈታኝ ዓለም ውስጥ ይኖር እንደነበር ሮስ ፓተርሰን *በመጽሐፉ* እንዲህ ጽፎዋል :-

> *«ኬር የተወለደው እ.ኤ.አ 1761 በድህነት ከሚማቅቁ ቤተሰብ ሲሆን በዚያ ዘመን የረባ ትምህርት ለማግኘትም ዕድል ካላገኙት እንግሊዛዊያን መካከል አንዱ ነበር። ኬር ምንም አይነት ገቢም ስላልነበረው የሆዱን ጥያቄ ለመመለስ ጫማ የመሥፋት ሥራ ቢጀምርም እንዳሰበው አልሆነለትም። የሰፈር ትምህርት ቤት በመክፈት ገቢውን ለማሳደግ ያደረገው ሁለተኛ ሙከራም ትርፉ ኪሳራ ስለሆነበት በዚያም መቀጠል አልቻለም። ኬር የብቸኝነት ኑሮውንም ለማሸነፍና ረዳት ፍለጋ ሚስት ቢያገባም በትዳሩም ደስተኛ አልነበረም። ካልተመቸችው ሚስቱም የዓይኑ ማረፍያና የፍቅር ምንጭ የሆነችለት ሴት ልጁንም ሞት ሲነጥቀው ኬሪ ልቡ የተሰበረና ቀን የጨለመበት ተስፋ ቢስ መስሉ ነበር። ለአገልግሎት ካለው ልዩ ሸክምና ጥሪ የአንዲት ትንሽ ቤተክርስቲያን መጋቢ ቢያደርጉትም ስበከቱ የተዘበራረቀና የማይመስጥ ከመሆኑ የተነሣ በመጋቢነት የመቀጠሉም ተስፋ በአጭሩ*

[26] *http://mosesonmissions.wordpress.com/2008/11/27/william-carey-father-of- modern-missions/*

*ተቀጨ:: እንግዲህ በዚህ አይነት የኪሳራና የተስፋ መቁረጥ ሸለቆ ውስጥ ይማቅቅ ለነበረው ምስኪን ሰው ታላቁ እግዚአብሔር ወደ መፈጠሩ ታላቅ የራእይ ተራራ አውጥቶት ለነበረበት ትውልድና ከእርሱም በኋላ በራእይ ለሚነሡት ሁሉ በምሳሌነቱ ያበራ ዘንድ ፋና ወጊ አድርጎታል::»*[27]

ከዚህ የምንማረው ትልቁ ነገር የዛሬ ማጣት፣ በችግር መከበብ፣ የሁኔታዎች እንደምንፈልጋቸውና እንደምናስባቸው ያለመሆን ትልቅ ነገር እንዳንሠራ ሊከለክሉን እንደማይችሉ ነው:: ባለራእይ ካለበት ነገር ይልቅ በላይ ያለውን ያያል፣ ያሳያል፣ ያምናል ይታመናል:: አንድ ሰው ትልቅ ራእይን ተቀብሎ እንዳይነሳ በዙርያው ካሉት አጣብቂኝና አሳዛኝ ሁኔታ ይልቅ በውስጡ ያለ አሉታዊ አመለካከት አንድ እርምጃ እንዳይንቀሳቀስ ሊያደርገው ይችላል:: ባለራእይ በሁኔታ አያምንም:: ራሳችንንና ሁኔታችንን እግዚአብሔር እንደሚያየው ማየትና እግዚአብሔር ስለእኛና ስለሁኔታችን የሚለውን ማለት ካልቻልን የትም አንደርስም::

ከሁኔታ በላይ በራእያችን ካላመንን ለትውልድ የሚተርፍ ታላቅ ነገር በዘመናችን ለማድረግ ቀርቶ ለራሳችንም በወጉ ሳንበቃ በጥላና በጨዛ የተመሰለውን ጥቂቱን ዕድሜያችንን በዋዛ ለማጠናቀቅ እንገደዳለን:: በምድር ሆነህ በሰማይ ስላንተ ያለውን የመፈጠርህን መለኮታዊ ዓላማ አይተህና አውቀህ ከተነሣህ ሰይጣን፣ ያለህበት ሁኔታና ሰዎች ሊያዘገዩህ ቢችሉም ሊያስቀሩህ ግን በፍጹም አይችሉም:: ካንተ በላይ ጉልበት ኖሮት አንተን ሊያስቀር የሚችል ጉልበት በዓለም ላይ የለም:: እግዚአብሔር ባንተ ብርቱ እንደሆነ አትዘንጋ::

## የማይክሮሶፍት ባለራእይ

ቢል ጌት ከ56 ቢሊዮን ዶላር በላይ በመሰብሰብ የዓለማችን ሁለተኛ ደረጃ የያዘ ቱጃር እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ቢልጌት ገና 13 ዓመት ልጅ እያለ የኮምፒዩቴር ፕሮግራም ንድፍ እንደ ጀመረ ታሪኩ ያወሳል:: ቢልገት ገና በልጅነቱ

[27] *Ross Paterson, What in the world is GOD WAITING FOR? p.89*





ለከሳይድ በሚባል የግል ትምህርት ቤት ስማር ያልተፈቀደለትን የኮምፒዩተር ክፍል ከመነካካቱ የተነሣ ባመጣው ብልሽት ወደ ኮምፒዩቴር እንዳይጠጋ ተከልክሎ እንደነበር ይነገራል::[28] ቢልጌት ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ለመሆን ዕድል ቢያገኝም በማለዳ በልቡ ከተቀመጠው ሸክም የተነሣ አቅም ሳያንሰው በማለዳ በራእዩ መንገድ ለመገለጥ የሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርስቲ ትምህርቱን አቋርጦ ለመውጣት ተገዶአል::[29] የዩኒቨርስቲ ትምህርቱን አቋርጦ እንዲወጣ ያደረገው የቢልጌት ራእይ ምን እንደነበር የሞባይል ሶፍትዌር ኢንጅነሪ Ravi Kumar Paluri በአንድ ድህረ ገጽ ሲገልጹ የቢልጌት ራእይ *«በእያንዳንዱ ጠረጴዛ ላይ ኮምፕዩቴር በእያንዳንዱ ኮምፒዩቴር ውስጥ የማክሮሶፍት ሶፍትዌር ማየት ነው::»*[30] በማለት አስፍሮአል:: በመጨረሻም ይኼ ጠንካራና ውስጣዊ አዲስ ነገር የመፍጠር ሸክም በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮችን የሚዝቅበት ልዩ የሀብት ዋሻ የሆነለትን የማይክሮሶፍት ራእይ ባለቤት አድርጎታል:: ቢል ጌት በዚህ ራእይ ሁልጊዜ ለዓለማችን አዳዲስ ማይክሮ ሶፍትዌሮችን እየፈጠረ በገፍ በማቅረብ ላይ ይገኛል:: ባጠቃላይ የዓለማችን ታላላቅ የፈጠራ ሰዎች በልባቸው ካለው ሸክም በተወለደ አንድ ራእይ ላይ ተገልጠው መውጣታቸው ሁላቸውን ያመሳስላቸዋል::[31]

## የመለኮታዊ ራእይ ልዩነት

የመለኮታዊ ራእይን ልዩ የሚያደርገው የዕውቀታችን፣ የተሰጦአችንና የልምዳችን ውጤት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ብቻ መቀበላችን ነው:: መለኮታዊ ራእይን በስብሰባ፣ በኮሚቴ ውሳኔ፣ በውስጣችን ባለው አቅምና ተሰጥኦ፣ በእጅ ብልጫ ብቻ መውሰድ አይታሰብም:: አንድ የቤተ ክርስቲያን ራእይ የግለሰብና የኮሚቴ የስብሰባ ውጤት ከሆነ መለኮታዊ መሆኑ አብቅቶለታል:: መንፈሳዊ ራእይ በእግዚአብሔር

[28] *http://www.notablebiographies.com/Fi-Gi/Gates-Bill.html*
[29] *http://en.wikipedia.org/wiki/List_of_college_dropout_billionaires*
[30] *http://www.buzzle.com/editorials ' Bill vision -"A computer on every desk and Microsoft software on every computer". Bill is a visionary person and works very hard to achieve his vision. His belief in high intelligence and hard work has put him where he is today.*

[31] *http://en.wikipedia.org/wiki/Bill_Gates*

ቃል መርህ የተቃኘ፣ የጊዜውን የእግዚአብሔርን አጀንዳ ገላጭ፣ ሰውና እግዚአብሔር ተኮር ነው። በሰዎች ተሰጥኦና ውስጣዊ አቅም ብቻ ላይ ተመሥርቶ የሚገለጥ ራእይ ቀዳሚ ትኩረቱ ሰው ነው። ይህም ለዓለማችን በጣም አስፈላጊ ነው። ልዩ ልዩ አቅምና ተሰጥኦን ለሰዎች የሰጠ ጌታ ራሱ ቢሆንም ሰዎች ሙት መንፈሳቸው በቃሉ ሕያው ሆኖ ከጊዜው የእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር ካልተያያዘ በስተቀር በውስጣቸው ባለው ነጠላ አቅም ላይ ብቻ በመመርኮዝ መለኮታዊ ባለራእይ መሆን አይችሉም። እግዚአብሔር በፈለገ ሁኔታና ምንነት የመጠቀም ሙሉ መብትና ሥልጣን እንዳለው ሆኖ። መለኮታዊ ራእይ ከእግዚአብሔር ለስሙ ክብር፣ በምድር ላይ በሰው በኩል የሚተገበር የዘላለም አሻራ ያለበት፣ ሰዎችን ወደ ሙሉ በረከት የሚያደርስ ኃይል ነው። የመንፈሳዊ ራእይ ዋናና ቀዳሚ ዓላማው ፍጥረትን በክርስቶስ ኢየሱስ በመጠቅለል ሥራ ውስጥ አንድ ጉልህ ሚናን በመጫወት እግዚአብሔርን ማክበርና ለሰዎች በረከትና ዕድገት እንዲሆን ሰበብ መሆን ነው።

መለኮታዊ ራእይ የዘላለም ብድራት አለው። የመለኮታዊ ራእይና የሌላው ራእይ ልዩነቱ በራእዩ ዓይነት ላይ ሳይሆን የባለራእዩ ከክርስቶስ ጋር ያለው ግንኙነት ላይ ይሆናል። ሰው ሁሉ በባለራእዩ እግዚአብሔር ስለተፈጠረ በተወሰነ መልኩ ባለራእይ የመሆን አቅም ይዞ ይወለዳል። ልዩነታችን መንፈሳዊ ራእይ የምንቀበለው በውስጣችን ባለው አቅም ሳይሆን ከጌታ መሆኑና የሚንጠቀመውም ለጌታ ክብርና ለሰዎች ልጆች በረከት መሆኑ ነው። መለኮታዊ ራእይ ክርስቶስን መግለጥና የሰውን ልጆች ወደ ክብር የማስመለስ ተልዕኮ ስላለው ሰማያዊና ምድራዊ ባሕሪይ ይታይበታል። ስለ ኢንተርፕሩነርሽፕ የሚያስተምሩ ምሁራን በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ *«ከ3000»* የሚበልጥ ልዩ ልዩ ፈጠራ ባለቤትነት አቅም እንዳለ ይናገራሉ። አሳዛኙ ነገር ይህ ሁሉ ውስጣችን ኖሮ አንድ እንኳ የለንም ብለን በድህነት መኖራችን ነው። በእያንዳንዱ ሰው ያለው አቅም የሰው ልጅ ራሱን፣ አከባቢውን፣ ሀገሩን፣ አህጉሩንና ዓለምን መለወጥ እንዲችል ከእግዚአብሔር የተሰጡ ናቸው። ይህ አቅም በውስጣችን ስላለ ብቻ ግን አይወጣም። እምነትና ፈልገን፣ በራእይ ኃይል፣ በመጠቀ አሠራር ልንወልደው ይገባል።





በውስጣችን እግዚአብሔር ያስቀመጠውን የታመቀ አቅም በራእይ ኃይል ካልተገለጥንበት ሁሉ እያለን እንዳች የሌለን ምስኪኖች ሆነን የመኖር አደጋ ውስጥ እንገባለን።

ቶማስ ኤድስን ይህን ምስጢር ስላወቀ ዓለምን በታላላቅ ግኝቶች አጥለቅልቆአል። ጆን ማክስዌል ቶማስ ኤድስን በውስጡ ያለውን አቅም እንዴት ለመጠቀም በዓላማ እንደኖረ ሲገልጹ *«ቶማስ ኤድሰን የብዙ ግኝቶች ባለቤት /inventor/ ሲሆን በየስድስት ወሩ አንድ ትልቅ አዲስ ግኝት በየ10 ቀኑ ደግሞ አንድ ትንሽ ግኝት ለዓለም ለማበርከት ለራሱ በያዘው ዓላማ መሠረት እርሱ ሲሞት በአሜሪካ መንግሥት በስሙ የተመዘገቡ 1,093 ያልተመዘገቡ ደግሞ ከ2000 በላይ ግኝቶች ባለቤት ሆኖ ነበር።»*[32] ብለዋል። አንዳንዶች ኤድሰን ይህን ያደረገው በጣም የተማረና የመጠቀ ሰው እንደሆነ አድርገው ይቆጥሩ ይሆናል እርሱ ግን የተሰጠውን አቅም አሟጦ የመጠቀም ራእይና ትጋት እንጂ የተለየና ልዩ ትምህርት እንዳልነበረው ታሪኩ ያወሳል። ይህ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ እንዲገለጥ አስቀድሞ ያዘጋጀው ታላቅ ውስጣዊ እምቅ ሀብት መኖሩን አመልካች ነው። ዶክተር ወሮታው በዛብህ በመጽሐፋቸው ስለሀገራችን የእይታና የተሰጥኦ ሀብት እንዲህ አቅርበዋል፦

*«ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ወደ 80 ሚሊዮን የሚጠጋ፣ በአብዛኛው ወጣት የሆነ ሕዝብ አላት። ይህ ማለት 80 ሚሊዮን የሚያስቡ አዕምሮዎች፣ 160 ሚሊዮን ከሩቅ የሚያዩ ዐይኖች፣ 160 ሚሊዮን ቁም ነገሮችና ጥበብን የሚያደምጡ ጆሮዎች፣ 160 ሚሊዮን ወደ ትክክለኛ ቦታና ሥራ ሊሄዱ የሚገባቸው እግሮች፣ 160 ሚሊዮን ሊሠሩና ሊያበለጽጉ የሚችሉ እጆችና 240,000,000,000 ኢትዮጵያን ከዳር እስከ ዳር ሊያበለጽጉና ታላቅ ሀገር ሊያደርጉ የሚገባቸው ተሰጦዎች አሏት። ይህ ሁሉ የሰው ሀብትና ተሰጥኦዎች ይዛ ዛሬ ባለነው ዜጎቿም ሳትመካ ኋላቀር የምትባል ሀገር ነች።»*[33]

---

[32] Maxwell C. John, ***DARE TO DREM … THEN DO IT,*** Thomas Nelson, Inc., Nashville, USA. 2006.

[33] *ወሮታው በዛብህ፣ በኢንተርፐረነርሽፕ መበልፀግ ምርጫም መብትም ግዴታም ነው፣ 2006 ገጽ*

## ለአንድ የተለየ ዓላማ ወደ ዓለም መጥተሃል ::

ሰኞ ጥቀምት 20 2004 ዓ.ም በዓለማችን የሕዝብ ብዛት 7 ቢሊዮን የሆነበት ታሪካዊ ቀን ሲሆን ከ7 ቢሊዮን ሰዎች መሐል ስንተኛ ሰው ሆነህ ወደ ዓለም እንደመጣህ ቁጥርህን ማወቅ ትፈልጋለህ ወይ? የሚል ጥያቄ በአንድ ማህበራዊ ድህረ ገጽ ቀርቦ ነበር:: ከ7 ቢሊዮን ሰዎች የራሴን ቁጥር ለማወቅ በUNFPA በተዘጋጀው ልዩ ቀመር የተወለድኩበትን ቀን ወርና ዓ.ም በቅጽ ላይ ስሞላ በዓለም ላይ ስወለድ 3, 661, 289, 465ኛ /ሶስት ቢሊዮን ስድስት መቶ ስልሳ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ ስልሳ አምስተኛ/ ሰው እንደሆንኩ ተነግሮኛል::

ሂሳቡን እንዴት እንደሠሩ ባላውቅም:: ይህም በአንድ የተለየ ቁጥር ወደ ዓለም መምጣታችን ብቻ ሳይሆን ከመምጣታችን ጀርባ አንድ መለኮታዊ አጀንዳ እንዳለና ፀጉራችን ሳይቀር በጌታ ፊት በቁጥር እንደሚታወቅ መጽሐፍ ቅዱሳችን በግልጽ ይናገራል:: ለምን ወደዚህች ምድር እንደመጣህና በአንተ ብቻ ሊተገበር የታቀደ መለኮታዊ ራእይ ለይተህ ከቃሉና ከመንፈሱ እስከታገኝ ድረስ ትጋ እንጂ እንደ ብዙዎች በመሳይ ሥራ ላይ ወርቃማውን ጊዜ እንዳታባክን ተጠንቀቅ::

አንድ ሰው እግዚአብሔር በሕይወቱ ያስቀመጠው ራእይ ምን እንደሆነ ለማወቅ የመጀመሪያው እርምጃ እግዚአብሔር ለአንድ ትልቅ ነገር እንደፈጠረው አምኖ ከእርሱ ለመቀበል በፊቱ ተግቶ መጸለይ መሆን አለበት:: በተለይ ያልተገለጠውን የእግዚአብሔር ፈቃድ በተገለጠው፣ በእጅ የሌለውን በእጅ ባለው፣ ያልደረስንበትን ትልቅ ነገር ከደረስንበት ትንሽ በኩል ለማወቅ ራስን ለመንፈሱና ለቃሉ መስጠት ብልህነት ነው:: ብዙ ሰዎች መለኮታዊ ራእይ መቀበል ያልቻሉበት ምክንያት እግዚአብሔር በእነርሱ የሚሠራውን ስላላሳያቸው ወይም ስለሌለው ሳይሆን ለራሳቸው በወሰኑት መንገድ እግዚአብሔርን ስለሚጠብቁ ነው:: እርሱ ደግሞ በወደደውና በመረጠው መንገድና ጊዜ እንጂ በራሳችን ውሳኔ ወደ እኛ አይመጣም::





አይሁዶች ለአራት ሺ ዓመታት ይጠብቁት ከነበረው መሲህ ጋር እንዲተላለፉ ያደረጋቸው ችግር ይህ ነበር:: እኛም ከተያዘልን መለኮታዊ አንድና ገዢ አጀንዳ ጋር እንዳንተላለፍ::

## ራእይውን ጻፍ

### *ራእይውን ጻፍ በጽላትም ላይ ግለጸው (ዕን 2:2 - 3)*

ሮበርት ውድርፍ የኮካ ኮላ ካምፓኒ ፕሬዝዳንት በነበሩበት ዘመን እ.ኤ.አ /1923 – 1955/ የድርጅቱን ራእይ ሲገልጹ *«የሰው ዘር ባለበት ሥፍራ ሁሉ የኮካ ኮላ ምርቶችን በበቂ ሁኔታ ማቅረብ ነው» ብለው ነበረ:: በዚህ ራእይ መሠረት ዛሬ የኮካኮላ ካምፓኒ 400 የተለያዩ አይነት መጠጦችን በ200 ሀገሮች በየዓመቱ 1.5 ቢሊዩን ጠርሙስ መጠጦችን እንደሚሸጥ የካምፓኒው መረጃ ይጠቁማል:: ይህ* ራእይ ግቡን ከመምታቱም አልፎ አንዳንዶች ሲናገሩ:- *«ዛሬ በዓለማችን ኢየሱስ ከሚለው ስም ይልቅ ኮካ ኮላ የሚለውን ስም የሰሙ ይበልጣሉ::» ይላሉ:: ይህም የተጻፈ፣ ለሌሎች የተገለጠና የተሠራበትን ራእይ ምን ያህል ኃያል እንደሆነ ያመለክታል::*

ዕንባቆም ምዕራፍ 2:2 ራእይውን በጽላት ላይ ግለጸው /ጻፈው/ በዛሬው አገላለጽ በማስታወቂያው ወይም በቢሊቦርድ ላይ ለሁሉም እንዲታይ ግለጥ እንደ ማለት ነው:: መለኮታዊ ራእይን ከእግዚአብሔር ከተቀበልን በኋላ ራእያችንን በቀላሉ ለሌሎች ማካፈል እንድንችልና ሌሎችም በቀላሉ ማስታወስ እንዲችሉ አድርገን መጻፍ ይገባናል::

«ራእይህን ጻፍ» ማለት ዘመናትን አሻግረን ባለንበት ጥሪና ሥራ አቅጣጫ አርቀን ስኬታችንን ማየት የምንችልበት መንገድ ነው:: የተጻፈ ነገር በቀላሉ አይረሳም፣ ለማስታወስም ሆነ ለሌሎችም ለማስተላለፍ ቀላል ይሆንልናል:: ከዛሬ አሥርና ሃያ አመታት በኋላ ባለንበት ሙያ፣ አገልግሎት ጥሪና ሥራ አቅጣጫ ሳንደርስበት መድረሻችንን ከወዲሁ አይተን ለመነሣት እንዲረዳን የተጻፈ ራእይ የሚጫወተው ሚና ቀላል አይደለም::

ለእኛ መጻፍ የከበደን ራእይ ለሌሎች ለመረዳት አይቀልም፡፡ ስለዚህ ራእይችንን በቀላሉ ለሌሎች በማካፈል ከራእይው ኋላ ለማሰለፍ ራእያችንን መጻፍ የግድ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ራእይ አለን ይበሉ እንጂ ራእይህን ጽፈህ አሳይ ሲባሉ በአጭር ቃል ለማስቀመጥ ግራ ይገባቸዋል፡፡ አንዳንዶች ሳምንታዊ፣ ወርሃዊና ዓመታዊ ፕሮግራሞቻቸውን እንደ ራእይ ሲያሳዩ ሌሎች ደግም ሞቅ ሲላቸው በጊዜያዊ የስሜታቸው ግለት ላይ ሆነው አንዴ ብለው ሁለተኛ ጊዜ በቃል ለመድገም የማይችሉትን ሀሳብ ራእያችን ነው ብለው ለመግለጽ ይሞክራሉ፡፡

ይህን መጽሐፍ ስጽፍ ከመቶ የሚበልጡ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን የተጻፈ ራእይ ካላቸው ለማረጋገጥ ባደረኩት ዳሰሳ በልባቸው ከያዙት ጥቅል ሀሳብ ካልሆነ በስተቀር ግልጽ ራእያችን ይህ ነው ብለው በጽሑፍ ለማሳየትና በትክክል ለመግለጽ የቻሉ 2% ብቻ ሲሆኑ 98% ራእይ አለን ብለው በድፍረት ከመናገር ያለፈ ራእይን በጽሑፍ የመጻፍ አስፈላጊነትና ጥቅም እንኳን በፍጹም የተረዱም አይመስሉም፡፡

## ያልተገለጠ ራእይ ከሌለ ራእይ አይሻልም

ብዙዎች «ራእይ አለኝ» ከማለት ያለፈ የተገለጠና የታወቀ ራእይ የላቸውም፡፡ እንደዚያ ያሉ ሰዎች ራእያቸውን ለሌሎች አካፍለው ባያውቁም ራእያቸው አንድ ቀን ከግቡ ደርሶ እንደሚያዩ ብርቱ እምነት እንዳላቸው መናገራቸው በጣም ያስገርማል፡፡ አንድ ያለተወለደ ጽንስ እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በማሕፀን ማደግ መቻሉ ለሁሉም የታወቀ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን በማሕፀን ከዘጠኝ ወራት በላይ ብዙ ከቆየ ሕያውነትን እንደሚያጣ ሁሉ በልባችን የተቀመጠው ራእይ በጊዜው ካልተወለደ በውስጣችን ሊሞት ይችላል፡፡ ብዙዎች ከመጠን በላይ በውስጣቸው ከመቆየቱ የተነሳ የሞተ ራእይን ተሸክመው ይኳዛሉ፡፡

ከዘመን ዘመን ራእይ አለኝ ብለው የሚናገሩ ራእያቸውን በገሃዱ ዓለም ማሳየት ያልቻሉ ሰዎች ራእይ ከሌላቸው የሚሻሉት «ራእይ አለኝ» በማለታቸው ብቻ ነው፡፡ ያልተገለጠ ራእይ ደግሞ ከሌለ ራእይ አይሻልም ያልኩት ለዚህ ነው፡፡





ራእያችን በጽሑፍ ካልተቀመጠ ወደ አንድ ነገር ሊወስደን በሚችለው መንገድ ላይ ለመራመድና የሌሎችን እገዛም ለማግኘት በፍጹም አንችልም፡፡ ያልተፀነሰ ራእይ አይወለድም፣ ያልተወለደ ራእይ አያድግም፣ ያላደገ ራእይ በምድር ላይ አይሰፋም፡፡

## ራእይህን በብዕር ዕቅድህን በእርሳስ

በወረቀት ላይ በብዕር የተጻፈን ጽሑፍ ወረቀቱ እስካልተቀደደ ድረስ ለማጥፋት አስቸጋሪ ሲሆን በእርሳስ ለተጻፈ ጽሑፍ ደግሞ እንደገና ለማስተካከል የራሱ ማጥፊያ «ላጲስ» ተሠርቶለታል፡፡ የአገልግሎት ራእይ ልብ ወለድ ወይንም ከሰው የሚሰጠን ስጦታ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የምንቀበለው የመፈጠራችን ዓላማ ገላጭ ነው፡፡ መለኮታዊ ራእይ እያደገ ይሰፋል እንጂ ፍጹም አይለወጥም፡፡ ስለዚህ በመለኮታዊ የአገልግሎት ራእይ ይዘት ላይ ምንም ለውጥ ማድረግ ስለማይቻል ራእይ በብዕር መጻፍ አለበት፡፡ እንዲህ ማለት ለምሳሌ አንድ የንግድ ራእይ በግላዊ ትርፍ ላይ ተመርኩዞ የሚቀርጸው ባለቤቱ ስለሆነ እንደ አስፈላጊነቱ በባለራእዩ /የንግዱ ባለቤት/ ሊቀያየር ይችላል፡፡

የአገልግሎት ራእይ ግን ከእግዚአብሔር በሰው በኩል ለክብሩ በምድር ላይ የሚሠራ ታላቅ ሥራ ነው፡፡ ልናጠፋውና ልናስተካክለው ስለማንችል በብዕር መጻፍ አለበት ስንል ቋሚነቱን ለማመልከት ነው፡፡ ዕቅድ ከራእይ የሚወለድ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ቅደም ተከተሉን ከጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ፣ ከግብአቶች ውስንነትና ማነስ፣ አከባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ጫናዎች የተነሣ፣ እንደገና ሊከለስ፣ ሊስተካከልና ሊለወጥ ይችላል፡፡ ዕቅድን በእርሳስ እንጽፋለን ማለት እንደ አስፈላጊነቱ መለዋወጥ መቻላችንን ለማመልከት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ራእያችንን በትክክል ሳንገነዘበው ከጌታ ያልተሰጠንን የአገልግሎት ራእይ ይዘን ብዙ ከተጓዝን በኋላ ጌታ ትክክለኛ ራእያችንን በገለጸልን ጊዜ ራእያችንን የማስተካከል፣ የመለውጥና እንደገና የመቅረጽ አጋጣሚዎች መኖራቸው ባይካድም በዚህ ሂደት የተለወጠው ራእይው ሳይሆን እኛ ወደ ትክክለኛው የእግዚአብሔር አጀንዳ መለወጣችንን ያመለክታል፡፡ ራእይ ይለውጠናል እንጂ መለኮታዊ ራእይን መለወጥ በፍጹም አንችልም፡፡

## መቀመጥ እግዚአብሔርን መጠበቅ አይደለም::

ጌታን መጠበቅ የማያውቅ ከጌታ ጋር መሥራትም አያውቅም:: ጌታን መጠበቅ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱሳችን አበክሮ ይናገራል:: ብዙዎች «እግዚአብሔርን እንጠብቃለን» በሚል የስንፍና ጥላ ሥር ቁጭ ብለው ጌታ ቁርጥ ውሳኔና አቅጣጫን ያመልክተኝ ብለው በወርቃማ ጊዜያቸው ላይ ሲጫወቱ ይታያሉ:: ስለ አንድ ነገር ትንቢትም ደጋግመው ሰምተዋል፣ ጊዜ ወስደው ጸልየው አስጸልየዋልም፣ ሕልምም አይተዋል፣ ከቃሉም ማረጋገጫ አግኝተዋል ነገር ግን «ጌታን እንጠብቃለን» በማለት ዛሬም ገዞ አልጀመሩም:: እንደነዚህ አይነት ሰዎች ምንም ሳይሠሩ ዘመናቸው በከንቱ ያልቃል:: የሚኖሩትም በሰማይ ከተያዘላቸው አጀንዳ ውጭና ከችሎታቸው በታች በመጫወት ነው:: አንዳንዶች ደግሞ አንድን ነገር ሆን ብለው ለመጀመር ፈቃደኞች አይሆኑም ምክንያቱም የተለየ ድምፅና መገለጥ ስለሚጠብቁ ነው::

እነዚህ ሰዎች ያልተረዱት ነገር በእምነት በተረዳነው ነገር ላይ የመጀመሪያውን እርምጃ ካልወሰድን ቀጣዩን ሀሳብ ማግኘት እንደማንችል መርሳታቸው ነው:: በዚህ ሕይወት ልናውቀው የሚገባን ትልቁ ነገር ሁሉን ማወቅ ሳይሆን ሁሉን የሚያውቀውን አምላክ ይዘን መራመድ መቻል ነው:: የሰው ልጅ በየትኛውም ጊዜና ደረጃ ስለሚሄድበት መንገድ ሙሉ በሙሉ የመረዳት አቅም እንደማይኖረው ሊታወቅ ይገባል:: መጋቢ ኢዮብ ማሞ «ዓይንህን አንሣ» በሚለው ጽሑፉ ስለ ባለራእይ እርምጃ እንዲህ ብሎ ነበር *«ባለራእይ ተቀምጦ ሁኔታዎች እስኪከሰቱ አይጠብቅም:: በመጸለይ፣ በማየት፣ በመራመድና ጌታን በማመን ሁኔታዎችን ወደ መኖር ያመጣቸዋል::»*[34]

እግዚአብሔር የሚያስነሣው ባለራእይ በቤተ ክርስቲያን ሆነ በትውልዱ ፊት ለፊት እንደ እያሪኮ የተደቀነውንና የሰውን ሁሉ ልብ አሸብሮ ወገብን ለፈታው ችግር የመፍትሔ ራእይን በማስጨበጥ ይልካል:: ባለራእይ ችግር ፈጣሪ ሳይሆን ለዘመናት ችግር መፍትሔ ሰጪና የመውጫ መንገድ የሚያሳይ የመፍትሔ ሰው

[34] *በኢምፓክት. 1996*





ነው:: መፍትሔውን የሚያመጣበት መንገድ አንዳንዴ ያልተለመደ ስለሆነ አንዳንዶች እንደ ችግር ፈጣሪ ሊቆጥሩት ይችላሉ:: ባለራእይ ለሰው ሁሉ በልቡ ቦታ ቢኖረውም በሰው ልብ ሁሉ ቦታ እንዳለው አያስብም:: በእግዚአብሔርም ልብ ቦታን ያገኘ በሰው ልብ ቦታን ለማግኘት አይዋደቅም::

ባለራእይ ባለበት ቦታ ለዘመናት የፈረሰው ይገነባል:: አይቻሉም ተብለው የበላይነት የተሰጣቸው ሀሳቦች ባለ ራእይው በሚያቀብለው አዲስ የይቻላል ሀሳብ ተጽዕኖ ሥር ይወድቃሉ:: የመጨረሻ ጥሩ ናቸው የተባሉት ሀሳቦችና ውጤቶች ከፊት ለፊት ላለውና ከላቀው ሀሳብ የተነሣ እንደ መነሻ እንጂ እንደ መድረሻና ቋም ርስት አይቆጠሩም:: ሀገርን የረታና ያሸነፈ ማንኛውም ተግዳሮት በራእይ ጉልበት ይሸነፋል:: ይዋረዳል:: ስለሆነም አንድ ራእይ ሲመጣ የትኛውን ችግር ይፈታ ይሆን? ወይም ምን የላቀ ነገር ሊገለጥ ነው? ብሎ መጠየቅ የሚገባ ጥያቄ ነው::

የሙሴ የነፃ አውጭነት ራእይ የተወለደው ለአራት መቶ ዓመታት የእሥራኤል ሕዝብ ከተገዛበት የባርነት መከራና ጩኸት ነበር:: የታላቁ መሪ የነህምያ እንደገና የመገንባት ራእይ የተወለደው ለዘመናት ከፈረሰው የኢየሩሳሌም ቅጥርና በውርደት እየማቀቀ ከሚኖር ሕዝብ ነበር:: የኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ የመሞት ራእይ የተወለደው በኃጢአት ከወደቀው የሰው ልጆች ነበር:: የጀርመናዊው ማርቲን ሉተር የተሀድሶ ራእይ የተወለደው ቤተ ክርስቲያን ከአንድ ሺ ዓመታት በላይ ከወንጌል መንገድ ወጥታ በሰው ሥርዓትና ወግ መታሰርዋ ነበር:: *«ኢትዮጵያን በሚቀጥሉት 20 ዓመታት የመካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እናሰልፋለን»*[35] የሚለው የኢትዮጵያ መንግሥት ራእይ የተወለደው ከድህነት ጣሪያ በታች ለዘመናት ከማቀቀችው ኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ነው:: ዛሬ ራእይ አለን የምንል ሰዎች የትኛውን ቤተ ክርስቲያናዊና ሀገራዊ ችግር ለማቅለል ይሆን? ለዚህ ጥያቄ መልስ ከሌለን ራእያችን ጥያቄ አለበት:: ላለንበት ጥያቄ መልስ የማይጠቁም ራእይ ራሱ ጥያቄ ነው::

[35] *ኢትቪ፣2000 ዓ.ም*

## መርሆዎች

- የነገው ትልቅ ራእይ የሚወለደው ዛሬ በውስጥህ ካለው ትንሽ ሸክም ነው:: ራእይህን ለማወቅ እግዚአብሔር በውስጥህ ያስቀመጠውን ሸክም አስቀድመህ እወቅ::
- ሸክም ራእይን ወልዶ በተግባር ሜዳ ማደግ ካልቻለ ለውጥ ለማውራት እንጂ ለውጥን ለማምጣት ብቁዎች አይደለንም::
- ለምን እንደተፈጠርክ የፈጠረህን ሳትጠይቅና ውስጥህን ሳታጤን ምን መሥራት እንዳለብህ ሰዎችን ሆነ ገበያውን አታማክር:: ሰዎችም ሆኑ ገበያው ከአንተ ስለሚፈልጉት እንጂ ውስጥህን አጢነው እግዚአብሔር ካንተ ምን እንደሚፈልግ የመንገርም ሆነ የመምከር አቅም የላቸውምና::
- ሸክም በባለራእዩ ልብ ውስጥ እግዚአብሔር የሚያስቀምጠው ጥቅል ሀሳብ ሲሆን ራእይ ደግሞ ስለዚያ ሸክም እንድንሠራበት የሚሰጠን የተገለጠ የእግዚአብሔር የጊዜው አጀንዳ ነው::
- የተጻፈ ራእይ በሚያነቡት ሰዎች ሁሉ ላይ ኃያል ነው:: ስለዚህ ራእያችንን በጽሑፍ ማቅረብ መቻል አንድ ትልቅ እርምጃ እንደሆነ እንዘንጋ::
- ባለራእይ ችግር ፈጣሪ ሳይሆን ለዘመናት ችግር የመውጫ መንገድ የሚያሳይ የመፍትሔ ሰው ነው::





# 4 ራእያችን ከእኛ በፊት ነበር

*«በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ::» ኤር 1:5)*

*«እግዚአብሔር ለቀባሁት አህዛብን በፊቱ አስገዛ ዘንድ የነገሥታትንም ወገብ እፈታ ዘንድ በሮቹም እንዳይዘጉ መዝጊያዎቹን በፊቱ እከፍት ዘንድ ቀኝ እጁን ለያዝሁት ለቂሮስ እንዲህ ይላል:- በፊትህ እሄዳለሁ ተራሮችንም ትክክል አደርጋለሁ፣ የናሱን ደጆች እሰብራለሁ የብረቱን መወርወሪያዎች እቆርጣለሁ በስምህ የሚጠራህ አምላክህ እግዚአብሔር እኔ እንደሆንሁ ታውቅ ዘንድ በጨለማ የነበረችውን መዝገብ በስውርም የተደበቀችውን ሀብት እሰጥሃለሁ::» (ኢሳያስ 45: 1- 4)*

ቂሮስ ሳይወለድ (በ675 ዓ. ቅ. ክ) አካባቢ በነብዩ ኢሳያስ የትንቢት ቃል ከተነገረለት ከ138 ዓመታት በኋላ (በ538 ዓ. ቅ. ክ) አከባቢ እንደመጣ ታሪኩ ያወሳል:: ይህ በምድር ላይ ሳይወለድ የመፈጠሩን ዓላማ ገላጭ ድንቅ ቃል ቀድሞ የመጣለት ቂሮስ ይኽ የትንቢት ቃል ሲነገርለት እርሱ ቀርቶ አባትና እናቱ በምድር ላይ ስለመኖራቸው እርግጠኛ አይደለሁም:: ቂሮስ አይሁዳዊ አልነበረም፣ ኪዳን ካላቸው ቤተሰብም አልተገኘም፣ የተወለደውና የነገሠውም በእስራኤል ምድር አልነበረም፣ እግዚአብሔር ይጠቀምበት እንጂ የተለየ ኪዳን ከእርሱ ጋር እንዳለውና የእስራኤልን አምላክ ያመልክ እንደነበረ የተገለጠ ነገርም የለም:: ይህ ትልቅ የመለኮት አጀንዳ እርሱ ባልነበረበት ምድርና ዘመን በአንድ እስራኤላዊ ነቢይ ከእስራኤል አምላክ ሲመጣለት ማየት እግዚአብሔር ምን ያህል የተለየ ዓላማ ለእያንዳንዳችን እንዳለው ገላጭ ነው::

እግዚአብሔር እስራኤላዊያን ገና ሳይማረኩ ከ140 ዓመታት በፊት በስላም ቀያቸው እያሉ ወደ ባቢሎን ከተማረኩ ከ70 ዓመት በኋላ እነርሱን ነፃ በማውጣት ስለሚጠቀምበት ገና በምድር ያልተወለደውንና የማይታወቀውን ሰው የአሕዛብ ንጉሥ ስም ቂሮስ ብሎ ከራሱ የዘላለም አጀንዳው አውጥቶ ሲያውጅ ማየት ምንኛ ያስደንቃል? ቂሮስ በጊዜው ያልነበረው ለዓለም ታሪክ እንጂ ለእግዚአብሔር በእጁ ነበር::

## *ቂሮስ ማን ነበር?*

*ማቴው ሄነሪ* ቂሮስ - ንጉሥ ከመሆኑ በፊት ስለነበረው ታሪክ ሲገልጽ «በልጅነቱ በጫካ ተጥሎ በአንዲት የዘላን ሚስት ተገኝቶ ከሞት የተረፈ ሰው»[36] እንደነበር ይናገራል:: *ቂሮስ ክ* /559 – 530/ ከክርስቶስ ልደት በፊት በፋርስ የነገሠ ገናና ንጉሥ ነበር:: በነገሠ በ20 ዓመታት ከህንድ ጀምሮ እስከ ቱርክ የጥንት ዓለም ኃያል መንግሥታትን ሜዶንን፣ ላይድንየስንና ባቢሎናዊያንን /549, 547 እና 539/ ከክርስቶስ ልደት በፊት አሸንፎ በምድር ላይ ገናና የፋርስን መንግሥት የመሠረተ ኃያል ንጉሥ እንደ ነበር ይነገርለታል:: ዳንኤልም ከቂሮስ መንግሥት እንደራሴዎች አንዱ ነበር:: (ዳን. 1:21 6:28 10:1) ንጉሥ ቂሮስ በብሉይ ኪዳን በዋናነት የሚታወቅበት ከሰባ ዓመት ምርኮ በኋላ እስራኤላውያንን ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ከባርነት ነፃ አውጪ መሆኑና ለዚህ አገልግሎት በእግዚአብሔር እንደ «ተቀባ» ይህም «መሲህ» ተብሎ የተጻፈውን የዕብራይስጥ ቃል የተካ የአማርኛ ቃል ነው:: በሌላ ቦታም እግዚአብሔር ስለ እርሱ እንዲህ ብሏል «ቂሮስንም:- እርሱ እረኛዬ ነው» (ኢሳ. 44: 28):: በእግዚአብሔር ቃል ይህ ትልቅ ቦታና ተልዕኮ የተሰጠው ሰው በግሉ ከእስራኤል አምላክ ጋር ስላለው ግኑኝነት እግዚአብሔርም እርሱም ያሉት ምንም የለም:: በሮናልድ ኤፍ ያንግብላድ ቂሮስ ግላዊ ግኑኝነት ከእግዚአብሔር ጋር እንዳልነበረው ሲናገር «*ቂሮስ ለእስራኤል አምላክ መሣሪያ ሆነ እንጂ የእርሱ ተከታይ አልነበረም::*» ካለ በኋላ «ማርዱኪ»

[36] *Matthew Henry's, Commentary on the whole Bible, Hendrickson Publisher's, (tenth printing) USA. 1999.*





የተባለው የባቢሎናዊያን መሪ ጣኦት ቂሮስን «ቅዱስ ንጉሥ» ብሎ እንደ ሰየመውና «*በዓለም ሁሉ ላይ ገዢ አደረገው::*» ብሎ በባቢሎናዊያን ታሪክ ተጽፎአል::[37]

## የራሱ ባልሆነው ሰው እግዚአብሔር እንዴት ይጠቀማል?

ቂሮስ እንደ ተቀባ በቃሉ የተመሰከረለት በእግዚአብሔር «ቂሮስ:- እርሱ እረኛዬ ነው::» ብሎ የተነገረለትና እርሱ ራሱ በአንደበቱ «*የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን ነገሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል በይሁዳ ባለችው በኢየሩሳሌም ቤት እሠራለት ዘንድ አዝዞኛል*» (2ዜና.36:23) ከሚለው ድንቅ ሀሳብ ጋር በማያያዝ ቂሮስ የእሥራኤል አምላክ ተከታይ አይደልም ካልን ከላይ ያነሣነው ጥያቄ ሊያቃጭልብን ይችላል:: መልሱ ቀላልና ግልጽ ነው:: እግዚአብሔር በሰዎች ከመጠቀሙ በፊት የግድ ሰዎች ሁሉ እርሱን ሊያውቁትና ዕውቅና ሊሰጡት አይገባም:: እግዚአብሔር በሰማይና በምድር ያሰበውን በፈለገው ሰውና መንገድ የመሥራት ባለ ሙሉ መብት ብቸኛና ነፃ አምላክ ሲሆን ምክንያቱም ሁሉም የእጁ ውጤቶች ብቻ ሳይሆኑ ለእርሱ የዘላለም ተገዢዎች ናቸውና:: እኛም ዛሬ ኪዳን አለን ብለን ብንኩራራ የእግዚአብሔርን የጊዜውን ሀሳብ ቾል ብንል አምላካችን ባለ ብዙ አማራጭ እንደሆነ ያመለክታል::

## የቂሮስ መለኮታዊ ራእይ

እግዚአብሔር ገና ያልተወለደውን ሰው ምን ሊሠራበት ጠራው? ለሚለው ጥያቄ ቂሮስ ራሱ በራሱ ዘመን ተገልጦ ሲናገር «*በኢየሩሳሌም ያለውን ቤት እሠራለት ዘንድ*» (*ዕዝ. 1: 2*) ሲል እናያለን:: እግዚአብሔር አስቀድሞ የያዘልን ራእይ ማዕከል እግዚአብሔር ራሱ ነው:: እግዚአብሔር ከእኛ በፊት የያዘው ዓላማው በእኛ አልፎ የዘላለም መንግሥቱን በምድር ላይ ማግነንና ሰዎቹን ወደ መንግሥቱ ማፍለስ ነው:: ሰው የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ ከመሆን የበለጠ ሌላ ክብርም ሆነ ራእይ የለውም::

[37] *Ronald F.Youngblood, New Illustrated Bible Dictionary, Thomas Nelson Publishers, USA, 1995*

## ተግዳሮቶች

ቂሮስ በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት የመሥራት ራእይ አንግቦ ሲነሣ በፊቱ ሊኖሩ ስለሚችሉ ተግዳሮቶች እግዚአብሔር አስቀድሞ ሲናገር በሮች፣ መዝጊያዎች፣ ተራሮች፣ የናስ ደጆች፣ የብረት መወርወሪያዎች በማለት ይገልጣቸዋል:: ከላይ የተዘረዘሩ የተግዳሮት ዓይነቶች እግዚአብሔር በቂሮስ በኩል ለመሥራት የተነሣውን ራእይ ለማስጨንገፍ ካልሆነም ለማዘግየት ጠላት ለመጠቀም ቢቃጣም አግዚአብሔር ደግሞ የቂሮስን አቅም ልያጎለብትና መለኮታዊ ጣልቃ ገብነቱን ልያሳየው ይጠቀምበታል::በዚህ ላይ ሊሠመርበት የሚገባው የእግዚአበሔርን ራእይ ማንሣታችን በተግዳሮቶች ውስጥ እንጂ ከተግዳሮቶች ውጪ እንደማያደርገንና ዋናው ከተግዳሮቶች ሁሉ በላይ የሆነው እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑ ነው:: እግዚአብሔር መከራ እንደማይደርስብን ሳይሆን በመከራ እንደሚደርስልን ቃል ገብቶልናል:: እንደማንታመም ሳይሆን እንደሚፈውሰን ቃል ገብቶልናል:: እንደማንወድቅ ሳይሆን እንደሚያነሣን ቃል ገብቶልናል::

በዚህ ሕይወት ትልቁ ነገር ተራራ ላይ መሆን ወይም ወደ ሸለቆ መውረድ ሳይሆን ከሥፍራና ከሁኔታ በላይ የሆነና ሊያደርገንም የሚችል ጌታ ከእኛ ጋር መሆኑ አውቆ በእምነት መራመድ ነው:: እግዚአብሔር ከሌለበት ሰላም ይልቅ እግዚአብሔር ያለበት ጦርነት ይሻላል:: «ከእግዚአብሔር ጋራ ሲሄዱ አልጋ በአልጋ ነው መንገዱ!» የሚል ሀሳብ የመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን አንዳንድ የእግዚአብሔርን አሠራር ያልተረዱና የጥራዝ ነጠቅ አስተማሪዎች ትምህርት ነው::

ይህ ለእግዚአብሔር ወልድ በምድር አገልግሎቱ፣ ለሐዋርያቶችና ለቤተ ክርስቲያን አባቶች አልሆነላቸውም:: እርሱንና እነርሱን እንድንመስላቸው ከተጠራን ለእኛም ደግሞ አይሆንልንም:: ከዚህ ውጭ መስበክ ሰባቂ እንጂ የቃሉ ሰባኪ አያደርገንም:: ለእኛም በዓለም እስካለን ድረስ መከራ ምርጫ ሳይሆን ግዴታ እንደሆነና በእርሱ ሁሉን አሸንፈን መዓዝ እንደምንችል ክርስቶስ ራሱ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ» በማለት መከራ እንዳለ ከነገረን በኋላ «ነገር ግን አይዞአቸሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ::» (ዮሐ.16፡ 33) በማለት በመከራ ድሉ ከእርሱ የተነሣ የእኛ እንደሆነ አረጋግጦልናል::





ሐዋርያው ጳውሎስ መከራ የጥሪያችን አካል እንደሆነ ስናገር «ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም::» (ፊል. 1፡ 29) በማለት በግልጽ አስቀምጦአል:: መከራ ለባለራእይ እግሬ መንገድ እንጂ መድረሻው፣ መጫሚያው እንጂ መቀበሪያው አይደለም:: ሰው ያለ መከራ ልማር የማይችል ደነዝ ሥጋዊ ማንነት በውስጡ የተደበቀ ፍጡር ይመስለኛል:: ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የሆነ መከራ የክብር እንጂ የውርደት፣ የጥቅም እንጂ የጉዳት፣ የማሸነፍ እንጂ የሽንፈት ምልክት አይደለም:: ለዚህ ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ «ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል ያበረታችሁማል::» (1ጴጥ. 5፡ 10) በማለት ከመከራ በኋላ ያሉትን ጥቅሞች የነገረን:: ባለራእይ ለአንድ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ መከራ ምርጫ ሳይሆን ግዴታ መሆኑን በማወቅ ከጌታ ከተቀበለው ራእይ የተነሳ መከራ ትዕግሥትን እንዲያስተምረው እንጂ እንዲያስቀረው አይፈቅድም::

## መለኮታዊ አቅርቦት

ቂሮስ የተፈጠረለትን ዓላማ ይዞ ሲነሣ ከፊት ለፊቱ ተግዳሮቶች ብቻ ሳይሆን አስቀድሞ መፍትሔውንም እንዳዘጋጃለትና ቂሮስን የሚገጥሙትን ተግዳሮቶች ሁሉ እንደሚያሳልፈው ቃል ሲገባለት፡- *ቀኝ እጁን እንደያዘው፣ በሮችን ከፊቱ እንደሚከፍት፣ በፊቱ እንደሚሄድ፣ የናሱን ደጅ እንደሚሰብር የብረቱን መወርወሪያ እንደሚቆርጥ* መናገሩ እግዚአብሔር በቂሮስ ሕይወት በኩል ሊገልጥ ያለውን ራእይ አንዳች ችግር እንደማይገጥመው ሳይሆን የትኛውም ችግር እንደማይችለው መናገሩ ነበር:: የእግዚአብሔር እርዳታ የሌለበት የእግዚአብሔር ራእይ አልነበረም፣ የለም፤ ለዘላለምም አይኖርም:: እግዚአብሔር አስቀድሞ ባልወጣበት የራእይ መንገድ ባለራእይ እንዲሄድበት አይፈቅድም:: እግዚአብሔር የሚሰጠው ራእይ ብቻ ሳይሆን ልዩ አቅርቦት ለራእይው ግብአት አስቀድሞ ገና ሳልተወለደው ቂሮስ እንደተዘጋጀ ሲናገር እንዲህ ይላል፡- *«በጨለማ የነበረችውን መዝገብ በስውርም የተደበቀችውን ሀብት እሰጥሃለሁ» (ኢሳ. 45፡ 3) በማለት ቃል ሲገባለት እናያለን::* ቂሮስ ዘመኑን ጠብቆ ከተገለጠ በኋላ እግዚአብሔር አስቀድሞ በእርሱ ለመሥራት ላቀደው ዕቅድ ምን እንደሰጠው ሲመሰክር

*«የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል» (ዕዝ.1:2) ብሎ ሲናገር እንመለከታለን::* ቂሮስ በዘመኑ ገናናና ኃያል የነበሩ መንግሥታትን ያገኛቸው በጦርነት እንጂ በድርድር እንዳልነበረ አንዘነጋ:: በተባለለትና በተሰጠው ልክ የሚገለጥ ሰው እርሱ የተባረከ ባለራእይ ነው:: በዘላለማዊው የእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ በልጁ ወደ መንግሥቱ የፈለስን ቅዱሳን ሁላችንም የቀደመንና የተዘጋጀልንን የዘላለም ራእይ እግዚአብሔር ዘንድ መኖሩንና አስፈላጊ ግብአቶች ለራእይው ስኬት ከዘመናት በፊት መዘጋጀታቸውን የቂሮስ ሕይወትና አገልግሎት ጠቋሚ ናቸው::

ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ራእይ የእግዚአብሔር አስፈላጊው አቅርቦት በፍጹም አይጎድለውም:: የተቀበልከውን ራእይ ከእርሱ እንደሆነ እርግጠኛ ሁን እንጂ በምን እንዴት ይሆናል? ብለህ አትቁም:: በእምነት ተራመድ::

## ቂሮስና ኪዳን

«ስለ ባሪያዬ ስለ ያዕቆብ ስለ መረጥሁትም ስለ እስራኤል ብዬ በስምህ ጠርቼሃለሁ»(ኢሳ.45:4) አንዳንዶቻችን ቂሮስ ይህን ሁሉ የእግዚአብሔርን እይታ እንዴት አገኘ? የምንል ከሆነ እግዚአብሔር በቂሮስ እንዲጠቀም ያደረገው ነገር የእግዚአብሔር የጊዜው ራእይና ስለ ያዕቆብ የገባው ቃል ኪዳን እንጂ የቂሮስ አንዳች እጅ እንደሌለበት እርሱ ሳይወለድ አጀንዳው መታወጁ ራእይ ከእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል::

የቂሮስ ትልቁ ድርሻ ፈቃደኝነቱ ነው:: ይህ ትውልድ ከቂሮስ ጋር በብዙ ይመሳሰልብኛል:: ያለንበት ቤተ ክርስቲያናዊና ሀገራዊ ሁኔታዎች ልብን የሚያነሣሡ ባይመስሉም ይህ ትውልድ ከመምጣቱ በፊት ለዚህ ትውልድ በሰማይ የተነገረ ቃልና የተያዘ የመለኮት ቀጠሮ እንዳለ የእግዚአብሔር መንፈስ በልቤ ላይ ይህን ጽሑፍ ስጽፍ ደጋግሞ ሲናገረኝ ነበር:: እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ ከኢትዮጵያ ጀምሮ በምድር ላይ ሊሠራ ለተነሣው ትልቅ ሥራ ራእዩንም፣ ቅባቱንም፣ አቅርቦቱንም፣ ድሉንም፣ ዘመንና ጊዜውንም ለዚህ ትውልድ





ሰጥቶናል:: እኛስ መለኮታዊ ራእይ እንደ ቂሮስ ተቀብለናል ወይ? የመለኮታዊ ራእይ ኃይል የሚለቀቀው በመሰጠታችን ውስጥ እንደሆነ ለአፍታም አንዘንጋ:: ምዕራባዊያን "Availability is power" – «መሰጠት ኃይል ነው» የሚሉት ከዚህ በመነሣት ይሆን? የተሰጠንን የመለኮት ራእይ አንግበን ዛሬውኑ እያወጅን በእምነት እንነሣ::

### *የቂሮስ መነሣት:-*

> *«ነብዩ ኤርምያስ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በመጀመሪያው ዓመት እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ የቂሮስን መንፈስ አስነሣ እርሱም:- የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እንዲህ ይላል:- የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል በይሁዳም ባለችው በኢየሩሳሌም ቤት እሠራለት ዘንድ አዝዞኛል::» (ዕዝራ. 1:1-2)*

በፋርስ ዙፋን ላይ ተቀምጦ በእግዚአብሔር የተያዘለትን የቀደመ ራእይ ለመፈጸም «በመንግሥቱ ሁሉ አዋጅ አስነገረ ደግሞም በጽሕፈት አደረገ::» (2ዜና 36: 23) ይላል:: ይህን አስደናቂ ግጥምጥሞሽ ብየዋለሁ::

## ስለ እኛ በሰማይ

ዛሬ የብዙዎቻችን ችግር በሰማይ የተዘጋጀልን የቀደመ አውራ ሀሳብ ያለመኖሩ ሳይሆን ለማወቅ ባለመፈለጋችን፣ በራሳችን፣ በጊዜያዊና በምድራዊው የተለመደ የኑሮ አዙሪት ውስጥ ገብተን በአንድ ቦታ በመዞር ከተያዘልን ራእይ ጋር መተላለፋችን ነው:: ክርስቶስን መከተላችንና ማገልገላችን የተያዘልንን ራእይ ለማወቅ መንገድ ላይ መውጣታችንን እንጂ ማወቃችንን አያመለክትም:: ብዙ መንፈሳዊ መሪዎችና ጥሩ ሕይወት ያላቸው ቅዱሳን በምድራዊ ሀሳብ ተጠላልፈው የተያዘላቸውን ራእይ ሳያደርጉ ሳይሆን በጭራሽ መኖሩንም ሳያውቁ ዕድሜያቸውን ጨርሰው ወደ ቀጣዩ የሚሻገሩ ጥቂቶች አይደሉም:: አንተ ለተፈጠርክለት ራእይ የምትኖር ነህ? ወይንስ የሆድህን ጥያቄ ለመመለስ? ወገኔ አልመሸብህምና አሁን በራስህ ላይ ንቃ::

ከተፈጠረልህ ይልቅ ለተፈጠርክለት መለኮታዊ ራእይ መኖር የከበረ መኖር እንደሆነ አትዘንጋ:: አቤቱ! በሰማይ ስለእኛ ከተነገረልን ሀሳብ ጋር እንዳንተላለፍ እርዳን::

## ከቂሮስ በብዙ እንበልጣለን

ቂሮስ በዘመኑ ለእግዚአብሔር የሠራ ባሪያ ሲሆን እኛ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ የአዲሱና የዘላለማዊው ኪዳን ልጆቹ መሆናችን ልዩ ያደርገናል:: የናዝሬቱ ኢየሱስ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ባርኮናል» (ኤፌ. 1: 3) «የልጅነት ሥልጣን ስጥቶናል::» (ዮሐ. 1: 12) በሚበልጥ ዘመን፣ በተሻለ ኪዳንና ጥሪ ወደ ዘላለም መንግሥት የፈለስን የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን በእርሱ ዘንድ ያለውን የመፈጠራችንን ራእይ ዛሬውኑ በማንሳት ዓለምን በወንጌል ለመድረስ እንነሣ:: «ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ::» (ፊል. 3: 12) ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው እኛም በእርሱ ዘንድ ያለውን ፈቃዱንና የመፈጠራችንን ራእይ ለመቀበል ልንፈጥን ይገባል:: ዘመናችን ውስንና አጭር እንደሆነ አንዘንጋ::

## ዓለም ሳይፈጠር መመረጣችን

የቂሮስ ራእይ ቂሮስ ሳይወለድ ከ138 ዓመታት በፊት እንደ ተነገረ ተመልክተናል:: በክርስቶስ ኢየሱስ ለተጠራን ልጆቹ መቼና እንዴት እንደተመረጥን ሐዋርያው ጳውሎስ በእግዚአብሔር መንፈስ ሲገልጥ «ዓለም ሳይፈጠር ...በክርስቶስ ተመረጥን::» (ኤፌ. 1: 4) ብሎ በመለኮት ውሳኔ እንደመጣን ሲናገር ደግሞ «አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኖአልና::» (ሮሜ. 8: 30) በማለት በእግዚአብሔር የተዘጋጀልን ዕጣ ፈንታችንን እኛ ከመኖራችን በፊት አስቀድሞ እንደተዘጋጀልን ፍንትው አደርጎ ገልጾታል:: የዕብራዊያን ጸሐፊም ይህ ስለእኛ በእግዚአብሔር አስቀድሞ እኛ ሳንኖርና በምድር ላይ ሳንገለጥ ምን? እና መቼ? እንዳየልን ደግሞ ሲገልጽ *«እግዚአብሔር ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበርና» (ዕብ 11: 40)* እንዳለው በእግዚአብሔር ዓይን ብልጫን አግኝቶ ለታየ ነገር ከኖርን በምድር ላይ አማኞች





ብቻ ሆንን ሳይሆን ታሪክ ሠሪዎችም ሆንን ጥቂቱን የሩጫ ዘመናችንን የዘላለም ብድራት ባለቤቶች ሆነን እንደመድማለን::

ዛሬ የተያዘልን መለኮታዊ ራእይ ትልቅነትና የአጀንዳው ዓለም አቀፋዊነት ከገባን ስለራሳችንና ስለዘመናችን አልፎም ስለአገልግሎታችን ያለን አመለካከት ወዲያው ይለወጣል:: በሰማይ የተያዘልን አጀንዳ ትልቅነትን በትክክል ተረድተን፣ አምነንና በዚያ አቅጣጫ በእምነት መራመድ ስንጀምር በማይመች ቦታና ሁኔታም ውስጥ ያለ ፍርሃት አልፈን ለመሄድ አቅም ይኖረናል:: ትልቅ ራእይን ይዞ የሚጓዝ ሰው ለትልቅ መለኮታዊ ዕርዳታ የሚያዘጋጁት ጊዚያዊ ችግሮች እንጂ መንገድ ላይ ሊያስቀሩት የሚችል ጉልበት እንዳለ አያምንም::

## ሕይወት ውድ ስጦታ ናት

ሕይወት በዓላማ ለዓላማ የተሰጠችን ትልቅና ውድ ሰጦታ ስትሆን የታሰበችው ግብ ጋ መድረስ የምትችለው በተዘጋጀላት መለኮታዊ የራእይ መንኮራኩር ላይ ሆና ስትወነጨፍ ብቻ ነው:: በዚህ ሕይወት የምናደርገው ትልቁ ነገር በሰማይ አስቀድሞ የተዘጋጀልንን ለይተን በማወቅ ለዚያም ስንኖር ሲሆን ከዚያ ውጭ በራሳችን የፈለግነውን ብንሆንና ብናደርግ በእግዚአብሔር ዘንድ አይቆጠርልንም:: ከሠሪው የበለጠ ስለ አንድ መሣሪያ ዓላማና ተግባር መናገር እንደማይቻል ሁሉ ከፈጠረው አምላክ በላይ ሰው ስለራሱ ሊያውቅ አይችልም::

ለእግዚአብሔር ከምንም በላይ ውድ ሰው እንጂ ሰው እንደ ውድ የሚቆጥራቸው ነገሮች አይደሉም:: የሰው ዋጋ ውድነት የሚገባን እግዚአብሔር ለሰው የተመነ የዋጋ ውድነት መረዳት ስንችል ብቻ ነው:: የሰው የሕይወት ዋጋ ውድነት እግዚአብሔርን የልጁን ነፍስ አስከፍሎታል:: ውድ ዋጋ የተከፈለለት ሰው ውድ መለኮታዊ የሕይወት ዓላማ ተይዞለታል:: ያን ዓላማ ስናነሣ ዓለምን የሚናነጋግር ባለራእይ እንሆናለን:: በውድ ዋጋ የገዛን ውድ ራእይ ይዞልን ነው:: እግዚአብሔር ሰውን በክርስቶስ እንጂ በብሔሩ፣ በተወለደበት አከባቢ፣ በሀገሩ፣ በዕውቀቱ ደረጃና በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው ዕውቅና አይመለከትም:: በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ ለውርደትና ለተራ ነገር የታጨና የተፈጠረ ሰው የለም:: ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ወደ ዘላለሙና ወደ ከበረው መለኮታዊ ዓላማ የሰውን ልጆች ሊያገነኝ

ሲሆን እርሱ ሃይማኖት ሳይሆን የዘላለም ዓላማ ምንጭ ሆኖልናል:: በአሮጌው ኪዳን ቂሮስ በተባለው በአንድ ባዕድ ሰው እግዚአብሔር ይህን ያህል ከሠራ በአዲስ ኪዳን በደሙ በገዛን ልጆቹ ምን ያህል ይሠራ ይሆን? የእኛ ያለመነሣት እንጂ እግዚአብሔር የድርሻውን እኛ ሳንወለድ አጠናቆ እኛን በመጠበቅ ላይ ይገኛል::

እግዚአብሔር በሥጋ እንደወለዱን ወላጆቻችን በምድር ላይ ከተገለጥን በኋላ ስለ እኛ ዕቅድ የሚያዘጋጅ ሳይሆን በእርሱ ዘንድ ባለው የዘላለም ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ የከበረና ወደ ምድር የመምጣታችንን መለኮታዊ ዓላማ ከእኛ ቀድሞ በእጁ የያዘ አምላክ ነው::

አንድ አማኝ ባለራእይ የሚባለው ሳይሆን የሚሆነው ይህን ስለ እርሱ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረውን የዘላለም ሀሳብ አውቆ በዚያ ላይ ሕይወቱን ሲመሠርት ለዚያም ተሰጥቶ የሚኖር ሲሆን ነው::አንድ ቤት ሲሠራ አስቀድሞ ብሉ ፕሪንት ፕላን በወረቀት ላይ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ የቤቱ ሥራ በፕላኑ መሠራት ይጀመራል:: እኛም በምድር ላይ ከመፈጠራችን ወይንም ከመወለዳችን አስቀድሞ ማንነታችን ብቻ ሳይሆን የመፈጠራችን ዓላማ/ራእይ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደነበር ቃሉ በግልጽ ይናገራል:: ይህን እውነት ለመረዳት ከዛሬ 2800 ዓመታት በፊት ስለ ፋርስ ንጉሥ ስለ ቂሮስ እርሱ ሳይወለድ በነቢዩ ኢሳያስ በኩል እንደተናገረ አይተናል:: እኛ ሳንኖር ስለ እኛ የተነገረውን አውቀን በዚያ ልክ እንገለጥ::





## *መርሆዎች*

- መለኮታዊ ራእይ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረ መለኮታዊ አጀንዳ በጊዜው ለእኛ የሚገለጥ ገዢ ሀሳብ ነው::
- በእግዚአብሔር የተሠራውን ራእይ እንቀበላለን እንጂ ራእይን በስብሰባም ሆነ በትምህርት አንሠራውም::
- አንድን ውጤታማ እግዚአብሔርን የሚያከብርና ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ ለመሥራት መለኮታዊ ራእይ ወሳኝ ነው::
- ከተፈጠረልህ ይልቅ ለተፈጠርክለት መለኮታዊ ራእይ መኖር የከበረ መኖር እንደሆነ አትዘንጋ::
- ክርስቶስን ማወቅና ማገልገላችን የተያዘልንን ራእይ ለማወቅ መታደላችንን እንጂ ማወቃችንን አያመለክትም::
- መለኮታዊ ራእይ ጥቅምና በረከቱ ለሰዎች ሁሉ ቢሆንም የሰዎችንም ሆነ ግላዊ አጀንዳችንን የምንፈጽምበት ሜዳ ግን አይደለም::
- የራእይን ዘር ከጌታ የመቀበል፣ ራእይዩ በውስጣችን አድጎ እኛን መውረስ፣ የራእዩ በገሃዱ ዓለም መወለድና ለፍሬ መብቃት የአንድ የራእይ የዕድገት ደረጃዎች ናቸው::
- በውስጣችን ከሌለ ራእይ አይወለድም፣ ያልተወለደ ራእይም አያድግም፣ ያልተወለደ ራእይም ለሌሎች አይተርፍም::

# 5 በራእይ ወይስ በልምድ ?

*«በአሜሪካ ከሚገኙት አሥር የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት አንድ እንኳን ከእግዚአብሔር የተቀበለችውን ግልጽ ራእይ በትክክል ለአባላት አካፍላ ራእይ መር አገልግሎት የምትመራ ቤተ ክርስቲያን የለችም:: ከሃያ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ብቻ ግልጽ ራእይ ተቀብላና ጽፋ ለአባሎቿም አካፍላ ለተግባራዊነቱም ትኖራለች:: ከመቶ አራት ፐርሰንት /4%/ መጋቢዎች ብቻ በራእይ ቤተ ክርስቲያንን ሲመሩ ከመቶ ዘጠና ስድስት ፐርሰንቱ /96%/ በዳበረ ልምዳቸው ቤተክርስቲያንን ለመምራት ይታገላሉ»[38] ይላል:-*

*የባርና ግሩፕ ጥናት*

የአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊ፣ የቤተሰባዊ፣ የማህበራዊና የሞራል ቀውስ ባሕር ውስጥ እየሰጠመች ያለችው ከመለኮታዊ ራእይ ይልቅ በራሳቸው ብቃት የሚሰማቸው አገልጋዮች ስለበዙ ይሆን? በተለይ በአሁኑ ጊዜ የአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን እየመሩ ያሉ መጋቢዎችን በተመለከተ ያለው መረጃ ያስደነግጣል::

*«በአሜሪካ 1,300 መጋቢዎች በየወሩ ከልዩ ልዩ ችግሮች የተነሣ ከአገልግሎት ሜዳ ይባረራሉ ወይም አገልግሎታቸውን ለማቆም ይገደዳሉ:: ዛሬ በአገልግሎት ላይ የምናያቸው መጋቢዎች ከ15 ዓመት በኋላ 40% አገልግሎታቸውን ትተው በሌላ ሥራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ:: ባለፉት 25 ዓመታት የአሜሪካን መጋቢዎች ፍቺ ወደ 65% አሻቅቧል:::»[39]* ይላል::

[38]Ibid, p.60
[39] *Sowing & Reaping, Guido Evangelistic Association* *Terry Mattingly, SCRIPPS HOWARD NEWS SERVICE 1996*





የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ለአብነት ሚሆኑ መልካም እሴቶች እንዳላት የታወቀ ነው:: ራእይን በሚመለከት ግን ከዓመታዊ ኮንፍራንስና ማነቃቂያ፣ ከተለመደው ሳምንታዊና ወርሃዊ መርሐግብሮች ከማካሄድ፣ ከአጥቢያዊ የአገልግሎት ብዛትና ቤተ እምነታዊ ትጋት ያለፈ ሀገራዊ፣ አህጉራዊ፣ ዓለም አቀፋዊ ራእይ ያላቸው ምን ያህል ናቸው? የምድራችንን አብያተ ክርስቲያናት እየተጫነና አቅጣጫን እያሳተ ያለ መለኮታዊ ራእይ ወይስ ሰዋዊ ልምድ? በአሜሪካ ከሚገኙ ከሃያ ቤተ ክርስቲያናት አንድ ግልጽ ራእይ ተቀብላ የምትራመድ ቤተ ክርስቲያን ከተገኘች በምድራችን ካሉት ከመቶ ምን ያህል ይገኝ ይሆን? «ራእይ» የሚለው ቃል ወይም ጽንሰ ሀሳብ ተወልዶ፣ አድጎ ያረጀው በቤተ ክርስቲያን አከባቢ ቢመስልም በቅርቡ ምንነቱን የተረዱት ግለሰቦች፣ ታላላቅ የንግድ ድርጅቶችና መንግሥታት ሳይቀሩ ራእያቸውን መታወቂያቸው በማድረግ በቆሙበት ሥፍራ ሁሉ ሲያውጁና በራእይው ግልጽነትና ጉልበት ብዙዎችን አጋሮቻቸው ሲያደርጉ ትልልቅና አዳዲስ ሥራዎችን ሲፈጥሩ ይታያሉ ::

ዛሬ በሀገራችን ወደ የትኛውም የመንግሥት ቢሮዎች ከቀበሌ ጀምሮ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልልና የፌደራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መግቢያ ላይ ከማንም ጋር ሳንገናኝ የሚቀበለን የቢሮው ራእይ፣ ተልዕኮና እሴቶች የተዘረዘሩበት ሰሌዳ ነው:: የተጻፈ ራእይ የተግባራዊነት ጥያቄው እንዳለ ሆኖ ማለት ነው:: ይህም አደራረግ መንግሥታችን በራሱ ተሞክሮ ብቻ የደረሰበት ግኝት ሳይሆን ራእይ ተኮር አካሄድ በዓለማችን ላይ ትልቅ ለውጥና ዕድገት በብዙ ሀገሮች እያመጣ እንዳለ በመገንዘባቸውም ጭምር ይመስለኛል:: አንዳንዶች ይህን መጽሐፍ ሲያነቡ ዓለማዊ አሠራር በመኮረጅ ወደ ቤተ ክርስቲያን የማስገባት ትግል ሊመስላቸው ይቻላል::

ለእኔ ግን ቤተ ክርስቲያን ያልተጠቀመችበትን ድንቅ ሀሳብ መልኩን ቀይረው በውጪ ያሉት ሲጠቀሙበት ልዩና አዲስ መሰለን እንጂ ለመጽሐፍ ቅዱስ ሀሳቡ ባዕድም አዲስም አይደለም:: ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያን አከባቢ «ራእይ አለን» ወይንም «ራእያችን ወንጌልን መስበክ ነው» ከሚለው ጥቅል ሀሳብ ያለፈ ግልጽ ራእይ ያላቸው ስንቶች ናቸው?

ለሚቀጥሉት 10 እና 20 ዓመታት ዘመንና ቀኑን እንዳመጣጡ ከማስተናገድ በዘመኑ ላይ የመለኮትን አሻራ ለማሳረፍ በመጠቀ እይታ ዘመኑን የቀደሙ ምን ያህሉ ናቸው? በቤተ ክርስቲያናችን ከተለመደው ሳምንታዊና ዓመታዊ የአገልግሎት ቅደም ተከተል ባለፈ በእያንዳንዱ አባል ታውቆ፣ በልባቸውና በመንፈሳቸው ተጽዕኖን ፈጥሮባቸው ለተግባራዊነቱ ብዙ ሆነው እንደ አንድ አንድ ሆነው እንደ ብዙ ተሰልፈው እየተጉበት ያለ ራእይ አለ ወይ? በማለት አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸውን ቢጠይቁ ጥቅሙ ለራሳቸው ክብሩ ለእግዚአብሔር ይሆናል:: የሰው ልጅ የመልካምም የሆነ የክፉ ልምዱ ባርያ ነው::

## *የልምድና የራእይ ጦርነት በቤተ ክርስቲያን*

በአንድ መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት በክልል ደረጃ መሪ የሆነ «ተግባራዊ የመንፈሳዊ መሪነት» የአንድ ዓመት ስልጠና በትምህርት ቤታችን ተከታትሎ ከተመረቀ በኋላ ቤተ ክርስቲያን የመለኮታዊ ራእይ መር መሆን አለባት ከሚለው ጠንካራ እምነቱ በወሰደው እርምጃ በቤተ ክርስቲያን የተገረመበትን ገጠመኝ እንዲህ አጫወተኝ:-

*«አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን ከተመሠረተች 15 ዓመታት የተቆጠረ ሲሆን በከተማችን አንጻራዊ ፈጣን ዕድገት ላይ ከሚገኙት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት መካከል አንድዋ ነች:: ከ1500 በላይ የሚሆኑ አባሎቻችን ከተለያየ ሙያና ብሔር የተቀየጡ ሲሆኑ ከስድስት የሚበልጡ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችም አሉን:: ጌታ በብዙ ባርኮናል:: እናመሰግነዋለን:: በቅርቡም በተደረገው የሽማግሌዎች የአገልግሎት ምደባ ሰብሳቢ ሆኜ እንዳገለግል ጌታ ሲጠራኝ ለሚቀጥሉት 20ና 30 ዓመታት ግልጽ ራእይና ግባችንን አውቀን ለአባሎቻችን ለማሳወቅ ስላስፈለገን እንደ ቤተ ክርስቲያን ግልጽ ራእይና ግባችን ምንድነው? በሚል ጥያቄ አገልግሎታችንን አሀዱ ብለን ስንጀምር ውስጣዊ የአመለካከት ጦርነት በአሮጌውና በአዲሱ አሠራር መካከል መጀመራችንን የተገነዘብነው ቆየት ብለን ነበር:: «ወንጌልን የመስበክ ራእይ አለን» ከሚለው ጥቅል ሀሳብ ለቤተ ክርስቲያናችን ግልጽ፣ እምቅ፣ ትልቅ፣*





*ለመገምገም የሚያስችል፣ በጊዜ የተገደበ፣ የራሱ ግብ ያለው፣ የእግዚአብሔርንና የእኛን ሚና ለይቶ ያስቀመጠ የመነሻና የመድረሻው መቼት ገላጭ ራእያችን ምንድነው? ራእያችንን በአጭር አረፍተ ነገር እንዴት አውቀን እናሳውቅ? ዝም ብለን ከመሰብሰብና ከመዘመር ያለፈ ከፊት ለፊታችን የምንመለከተውን ግባችንን ማስቀመጥ እንችላለን ወይ? ስንል ድንገት ያልተጠበቀ የተቃውሞ ፍንዳታ በመካከላችን ፈነዳ «ይህን ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱ እነ ጋሽ እገሌና እገሌ እንዲህ አልመሩም? ቤተ ክርስቲያንን የሚመራ እግዚአብሔር ራሱ እንጂ የእኛ ዕቅድ አይሠራም:: ይህ አሠራር ዓለማዊ አሠራር ነው:: እኛ በፍጹም አልለመድነውም::» የሚሉ ጥያቄዎችና አስተያየቶችን ወደ አንድ አቅጣጫ ለማምጣት ትልቅ ምጥ ውስጥ አሳለፍን:: ከብዙ ክርክር፣ ውይይትና ጸሎት በኋላ በግልጽ ራእይ አስፈላጊነት ላይ ተስማማን:: በጌታ ፊት ለሳምንታት ቆይተን ትልቅ ራእይን ተቀብለን ገና ወደ ሕዝቡ ሳናወርድ ትልቅ መነሳሳት፣ የልብ አንድነት፣ የለውጥ ነፋስና የዓላማ ጭካኔ ሲያጥለቀልቀን አስተዋልኩ:: ሕዝቡ፣ ቤቱ፣ ቦታውና አገልግሎቱ ያው ቢሆንም እይታችን ስለ ታደሰ ነገራችን ሁሉ ታድሶአል:: እንደ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከየት ተነሥተን የት እንደምንደርስ ዓይናችን በርቶ ስላየን የማይቀዘቅዝ መቀጣጠል ውስጥ ገብተናል:: ክብሩ ለጌታ ይሁን::»* ብለዋል::

## ልምድ እንደ ባላንጣ

የትላንቱ ልምድ ዛሬ ወደ ሚበልጠው መወጣጫ መሰላል ካልሆነ አስሮ የሚያስቀር ወጥመድ መሆኑ አይቀሬ ነው:: ዛሬ የመለኮታዊ ራእይ ቀንደኛ ባላንጣ ሆኖ ዕድገታችንን እየሞገተ ያለው በልምድ የዳበረ የትላንትና አሠራሮቻችንና ለእነርሱም የሰጠነው ልዩ የአይነከኔት ደረጃ ነው:: የትላንቱን መልካም ጅማሬ ለዛሬ መስፈንጠሪያ (springboard) እንጂ መቀበሪያ ሥፍራ (cemetery) ማድረግ አይገባንም:: አንድ ጸሐፊ *«ለለውጥና ለዕድገት ትልቁ እንቅፋት የዳበረ የብዙ ዘመን ልምዳችን ነው::* እንዳሉትና፤ ታላቁ ባለራእይ ኢየሱስም *«አሮጌ ... ሲጠጣ አዲሱን የሚሻ የለም አሮጌው ይጣፍጣል::»* (ሉቃ 5: 39)

*ይላል።* ይህም ሰው ከአዲስ ነገር ይልቅ ለቆየውና ለለመደው የሚሰጠውን ዋጋ ለማመልከት አስቦ ነበር።

ሰው ጌታ እንኳ እየተናገረው «ጌታ ሆይ» ብሎ በፊቱ እየጸመና እየጸለየ ከቆየ ባህሉ፣ ልምዱና አሠራሩ ካልገጠመ «አይሆንም!» ለማለት ጠንካራ ልብ ያለው ደካማ ፍጡር ነው። ለዚህም ትልቅ ምሳሌ የሚሆነን የሐዋሪያቶች መሪ፣ የጸንጤቆስጠው ቀን ታላቁ ሰባኪ፣ የቤተ ክርስቲያን «አምድ» ተብሎ በሐዋርያው ጳውሎስ የተመሰከረለት (ገላ 2: 12) ሐዋሪያው ጴጥሮስ ነው። ጴጥሮስ ጌታ ከባሕሉ፣ ከአስተዳደጉና ከለመደው ቅኝት ውጭ ሲናገረው በአክብሮት «ጌታ ሆይ» ካለ በኋላ «አይሆንም!» (የሐዋ. 10:13) ሲለው እንመለከታልን።

*«ለሰው ትልቁ ችግር አዲስ ነገር ማመኑ ሳይሆን በውስጡ ያለውን አሮጌውን ማውጣት ነው»* ያለው ደግሞ አልበርት አንስታይን ነበር። ዛሬ እንደ ግለሰብና እንደ ቤተ ክርስቲያን ባለንበት ቦታ እንድንረግጥ፣ የጨውነታችንንና የብርሃንነታችንን ሚና እንዳንጫወት ደንቃራ ከሆኑብን አንዱ በራእይ ሳይሆን ባረጀውና በተለመደው አካሄዳችን መጭውን ለመግጠም መዘጋጀታችን ነው። የሙሴ አመራርና አሠራር ለኢያሱ፣ የሳኦል የጦር ልብስ ለዳዊት፣ አልሆነም።

ለኢያሱ እንኳ በኢያርኮ ላይ የተቀዳጀው የትላንቱ ድል ዛሬ በጋይ ለደረሰበት ትልቅ ሽንፈት ሊያግዘው በፍጹም አልቻለም። የእኔና የልጄ አምላክ አንድ ቢሆንም የምናገለግልበ ዘመን፣ ስጦታውና የጸጋው አሰራር እንዲሁም ትውልዳችን አንድ አይደለም። ልጄን ለራሱ ትውልድ እንጂ ለራሴ ትውልድ ማዘጋጀት አይቻልም። ለማደረግ ብሞክር የልጄን ዕጣ ፈንታ "Destiny" እንደ ማጨንገፍ ይቆጠራል። የትላንቱ አሠራር ለዛሬ የዛሬም አሠራር ለነገ እንዳማይሆን ማወቅ ብልህነት ነው። አሠራሮቻችን ለቃሉ ይገዛሉ እንጂ ቃሉ ለአሠራሮቻችን አይገዛም። የ20ኛው ክፍለ ዘመን ልምድና የተሞክሮዎቻችን እንዲሁም በድልም ሆነ በሽንፈት የተዘጉ ፋይሎቻችን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ትውልድ ለትምህርት እንዲሆነው እንነግረዋለን እንጂ የሕይወቱ መርህ እንዲያደርግ አናስገድደውም።





ያለፈ ትውልድ ልምድ ለመጪው ትውልድ መርህ እንዲሆነው በግድ እንደ ልብስ ብናለብሰውም ከፊታችን ዞር ሲል አውልቆ እንደምጥል ሳይታለም የተፈታ ነው። ትውልዱን ላለፈው ዘመናችን ሳይሆን በባለራእይነት ልብና መንፈስ ለመጪው እናዘጋጅ። እግዚአብሔር በራሳችን ላይ ያንቃን!

ዛሬ በሀገራችን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ራእይም ሆነ ጥሪ የሌላቸው እንዲሁም የማይማሩና የማያስተምሩ፣ ለመምራትም ሆነ ለመከተል የማይፈቅዱና የአገልግሎትን ወንበር በበላይነት ግን የያዙ «መሪዎች» ቁጥራቸው ቀላል እንዳልሆነ ይነገራል። ራእይ አልባ የአገልግሎት ሕይወት የሚመሩ፣ በልምዳቸውና በወረቀታቸው ብዛት፣ በሰዎች ሜዳዊ ሥርዓትና ሹሜት የቤተ ክርስቲያንን የመሪነትን ወንበር የተቆናጠጡ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ከመጉዳት በስተቀር ምንም አይፈይዱላትም። በቦታቸው ቢሆኑ ግን ጠቃሚነታቸው አያጠያይቅም። እንደነዚህ ያሉ «መሪዎች» ራእይ ስለሌላቸው ወደ ፊት ማስኬድ ቀርቶ ባለንበት እንኳ የማቆየት አቅም የላቸውም። መረን በሆነው የአኗኗር ዘይቤያቸው ስለሚታወቁ ለምሳሌነት የሚበቃ የሕይወትም የላቸውም።

በምዕራቡ ዓለም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ላይ የደረሰው መረን መሆን እኛ ጋ እንደሚጀመር ሳይሆን ከፈረንጅ ሀገር ስለመጡ ብቻ እንደ አዲስ መገለጥ ተቆጥረው እንደ ካርቦን ኮፒ እየተባዙ በመሰራጨት ላይ ያሉትን አሉታዊ ልምዶችና አሠራሮች ባሉበት እንዴት እንግታ? የሚለው ጥያቄም አፋጣኝ መልስ የሚሻ ጉዳይ ይመስለኛል። ዛሬ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የስም፣ የወንበር፣ የሹመት፣ የደመወዝ፣ ከጥሪ ይልቅ በዲግሪና በዲፕሎም ማተኮር፣ በመጡት ጥቂቶች ላይ የመረባረብና ውጭ ላሉት ሕዝብ ደንታ ቢስነት የመለኮታዊ ራእይ እጦት እንበለው ወይንስ ሌላ? ድግግሞሽ፣ ከለላ፣ ተመሳሳይነት፣ ፍሬ አልባነት፣ ኩረጃ፣ ሐሜት፣ እርስ በርስ መወነጃጀል፣ ጠባብ ብሔርተኝነት፣ ላለፈው ታሪክና ገድል ብቻ ልዩ ዋጋ የመስጠትና ከአቅም በታች የመጫወት አባዜ በገነነበት ምድር ራእይ ከስም ያለፈ በተግባር የመታወቅ እድል የለውም። ራእይ ባለበት ሀገር ዕድገት አለ። ራእይ በነገሠበት ምድር የአሮጌ አሠራርና አካሄድ ቦታ የላቸውም። ራእይ ባለበት ለውጥ አለ። በራእይ የሚመራ ሕዝብ ምርጫው በጥሩና በመጥፎ መካከል ሳይሆን በተሻለውና በሚበልጠው መካከል ይሆናል።

ራእይ ባለበት የተለየና ልባዊ ተነሣሽነት አለ:: በራእይው ወጤት ለመደሰት ብቻ ሳይሆን ራእይውን ለማስፈጸም ባለው ሂደት ለመሞት የቆረጡና የጨከኑ ሰዎች አሉ:: ራእይ ባለበት ጨለምተኛነት ሥፍራ የለውም:: ራእይ ባለበት ሥፍራ ምንደኝነትና ጥገኝነት ቦታ አይኖራቸውም:: ራእይ ባለበት ሥፍራ መታወቂያው ስም ሳይሆን ሥራ ይሆናል:: ራእይ ባለበት እርጅና፣ አቅም ማጣት፣ የገንዘብ እጦትና የእውቀት ውስንነት እንደ ደረጃ መውጫ እንጂ እንደ አሰናካይ እንቅፋቶች አይቆጠሩም:: ራእይ በተዘጋ በር ውስጥ የተከፈተ በር የምናይበት አዲስ ምዕራፍ ነውና::

## ትንሹ የራእይ ልዩነት ትልቅ መለያየት

ጆን ማክስዌል *«በሰዎች መካከል ያለው ልዩነት በጣም ትንሽ ቢሆንም ያ ትንሽ ልዩነት ግን ትልቅ መለያየትን ይፈጥራል»* ብለው ነበር:: በመጽሐፍ ቅዱሳችንም የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ሲወጡ ስለ ከነዓን እግዚአብሔር ማርና ወተት እንደምታፈስ፣ ክረምትና በጋው ሳይዛነፉ እንደሚፈራረቁባት፣ ለሰውና ለእንስሳትም መልካምና ምቹ የመኖሪያ ሀገር እንደሆነች ጠንካራ መረጃ በሁሉም እሥራኤላዊ ልብ ተከማችቶ ነበር::

ወደ ምድሪቱም ሲጠጉ 12 ሰላዮች በሁሉም ልብ ባለው መረጃ መሠረት የምድሪቱን ሁኔታ ለማረጋገጥ በሙሴና በእሥራኤል ጉባኤ ተልከው በእግዚአብሔር ተነግሮአቸው የነበረውን መረጃ ትክክለኝነት ሲያረጋግጡ *«የምድሩን ፍሬ አሳዩአቸው እንዲህም ብለው ነገሩት:- ወደላክኸን ምድር ደረስን እርስዋም ወተትና ማር ታፈሳለች ፍሬዋም ይህ ነው::»* (ዘኁ. 13: 26 - 27) የምድሪቷን ፍሬ በልተውና ሪፖርታቸውን ለማጠናከር የምድሪቷን ፍሬ ለናሙናነት ተሸክመው በማምጣት ለሙሴና ለሕዝቡም ካሳዩ በኋላ ውሳኔያቸውን ሲገልጹ *«ነገር ግን በምድሪቷ የሚኖሩ ኃያላን ናቸው.. ከተሞቻቸውም የተመሸጉና እጅግም የጸኑ ናቸው:: ደግሞም በዚያ የኤናቅን ልጆች አየን::»* (ዘኁ. 13: 28) *«እርስ በርሳቸውም ፦ ኑ አለቃ ሾመን ወደ ግብፅ እንመለስ»* (ዘኁ. 14: 4):: መረጃ በመረጃ ሆነው የራእይ ድህነት ወደ ፊት ሳይሆን ወደ ኋላ እንዲከጅሉ





አደረጋቸው:: ሁለቱ ባለራእይዎች ካሌብና ኢያሱ *«ማሸነፍን እንችላለንና እንውረስ» «እግዚአብሔር ከወደደን ማርና ወተት ወደምታፈስው ወዳዚያች ምድር ያገባናል እርሰዋንም ይሰጠናል:: ... እንደ እንጀራ ይሆኑልናል»* በማለት ከራሳቸውም፣ በልባቸው ካለው መረጃና በመንገዳቸው ላይ ካሉት ተግዳሮቶች ሁሉ በላይ የእግዚአብሔርን የበላይነት ሲያውጁ እንመለከታለን::

ከእሥራኤል ጉባኤ ተወክለው ከነዓንን እንዲሰልሉ የተላኩት ሁለቱንና አሥሩን የለያያቸው አንድ ነገር ሲሆን እርሱም ራእይ ነው:: ስለ ከነዓን ያላቸው መረጃ አንድ ሲሆን መረጃውን የተነተኑበት መንገድ አሥሩ በራሳቸው እይታ ሁለቱ ደግሞ በባለራእይነት መንፈስና ልብ ነበር:: አንድ መንግሥት፣ አንድ አምላክ፣ አንድ ሕዝብ፣ አንድ ኪዳን እያላቸው የመረጃው ልዩነት ሳይሆን አንድ የራእይ ልዩነት (መረጃውን የተነተኑበት መንገድ) የሁለቱንና የአስሩን ዕጣ ፈንታ /Destiny/ እንዲለያይ አደረገ:: የራእይ ልዩነት ብዙሃንን ለሞት ጥቂቶችን ብቻ ለሕይወት እንዲሆኑ የግድ አላቸው::

## በእምነት ስናይ እንወርሳለን!

እግዚአብሔር ያየልንን ማየት ምርጫ እንጂ ግዴታ አይደለም:: ድል አልያም ሽንፈት የማየት እንጂ የትግል ውጤት ብቻ አይደለም:: ካሌብና ኢያሱ በተሸናፊዎች መንደር «የአይቻልም» መንፈስ መረጃውን ገልብጠው እንዲተነትኑ በተጫናቸው ሕዝብ መሀል ከሰማይ ለመስማት በሕዝቡ ጩኸትና ተቃውሞ መስመሩ አልተጨናነቀባቸውም:: የተስፋን ቃል ሰምተው፣ በቂ መረጃ አሰባስበውና ትክክለኝነቱን በዓይናቸው አረጋግጠው ወደ ኋላ ለመመለስ መሪ በሾመው ትውልድ መካከል ሁሉን የሚችል እግዚአብሔርን ብቻ በማየት «እርሱ ይችላል! እኛም በእርሱ እንችላለን!» ብለው ውሳኔ ብቻ ሳይሆን ለጦርነት ዝግጁነታቸውን ሲገልጹ እግዚአብሔር እንዲህ አለ:-*«ባሪያዬ ካሌብ ግን ሌላ መንፈስ ከእርሱ ጋር ስለ ሆነ ፈጽሞም ስለ ተከተለኝ እርሱ ወደ ገባበት ምድር አገባዋለሁ ዘሩም ይወርሳታል::» (ዘኁ. 14: 24)*

## ያለ እምነት ስናይ እንወረሳለን!

ሰው ከእይታው በላይ አይሰፋም፣ ከእይታው በላይ አይሮጥም፣ ከእይታው በላይ አይወርስም፣ ከእይታው በላይ ፍሬን አያፈራም፣ ከእይታው በላይ አይኖርም፣ ከእይታው በላይ በመንፈሳዊም ሆነ በስጋዊ ሕይወቱ አያድግም:: *«ምን እንደምታይ ንገረኝና ምን እንደምትሆን እነግርሃለሁ»* የሚባለው ለዚህ ነው:: እግዚአብሔር ለእሥራኤል ልጆች *«ማርና ወተትን፣ ብልጽግናን፣ እረፍትና ደስታን፣ ጦርነት ቢኖርም ድልን፣ ሰላምን፣ ማሸነፍን»* አይቶ ሲመራቸው ያየላቸውን እነርሱ ካልፈለጉት በግድ እንደሚያወርሳቸው ግን ቃል አልገባላቸውም:: ዛሬም እንዲሁ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ትልልቅና ዘላለማዊ ራእይና ዕቅድ ቢኖረውም እኛ እንቢ ብንል በግድ አያወርሰንም:: እግዚአብሔር ተስፋ ይገባልናል እንጂ ተስፋውን አይወረስልንም:: ስጦታን ይሰጠናል እንጂ አይቀበልልንም:: ወደ ፊት እንድንሄድ ይነግረናል እንጂ እኛን ተክቶ አይሄድልንም:: መጭውን እንድናይ አይን ይከፍትልናል እንጂ አያይልንም:: አንዳንድ ግማሽ እውነት የሚናገሩ አማኞች *«ዋናው እግዚአብሔር ይናገር እንጂ እርሱ ያለው ሁሉ ይሆናል»* ይላሉ:: ይህ የእግዚአብሔርን ታማኝነትና ድርሻን ሲያመለክት ከእኛ ባለራእይነት፣ እምነትና እርምጃ እንደሚጠበቅ ይዘነጋሉ:: የእሥራኤል ልጆች ከእግዚአብሔር በላይ፣ እርሱ ከያዘላቸው ግብና ራእይ ውጪ ያዩትንና የመረጡትን ሽንፈትና ጥፋት ለእነርሱ ማውረሱ ታማኝነቱን እንጂ ጭካኔውን አያመለክትም:: አይቻልም፣ አይሆንም፣ ምነው በሞትን ኖሮ፣ በዚያ የዔናቅን ልጆች አየን፣ ኑ አለቃ ሾመን ወደ ግብፅ እንመለስ ሲሉ  እርሱም እንዲህ አለ፡-

*«እኔ ሕያው ነኝና በጆሮዬ እንደ ተናገራችሁት እንዲሁ በእውነት አደርግባችኋለሁ ይላል እግዚአብሔር በድኖቻችሁ በዚህ ምድረበዳ ይወድቃሉ:: የተቆጠራችሁ ሁሉ እንደ ቁጥራችሁ ከሀያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆነ ሁሉ እናንተ ያጉረመረማችሁብኝ ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ኢያሱ በቀር በእርስዋ አስቀምጣችሁ ዘንድ እጄን ዘርግቼ ወደ ማልሁላችሁ ምድር በእውነት እናንተ አትገቡም::» (ዘኍ. 14:28)*





## *መርሆዎች*

- ሰው ጌታ እንኳ እየተናገረው  ልምዱና አሠራሩ ካልገጠመ *«አይሆንም!»* ለማለት ጠንካራ ልብ ያለው ደካማ ፍጡር ነው::
- ዛሬ የመለኮታዊ ራእይ ቀንደኛ ባላንጣ ሆኖ ዕድገታችንን እየሞገተ ያለው በልምድ የዳበረው የቆየው አሠራራችንና ለእርሱም የሰጠነው ልዩ የአይነኬነት ደረጃ ነው::
- አሮጌ አቁማዳና አዲሱ ወይን ጠጅ አብረው እንዳማይሄዱ ሁሉ የድሮ ልምድና አዲሱ ራእይ በምንም አብረው ልሄዱ አይችሉም::
- ድግግሞሽ፣ ክለሳ፣ተመሳሳይነት፣ ኩረጃ፣ ሳለፈው ታሪክና ገድል ብቻ ልዩ ዋጋ መስጠት በነገሠበት ምድር ራእይ ከስም ያለፈ በተግባር የመታወቅ እድል የለውም::
- እግዚአብሔር ያየልንን ማየት ምርጫ እንጂ ግዴታ አይደለም:: ያየነውን መውረስ ግን ግዴታ እንጂ ምርጫ የለውም::
- ሰው የሚሆነው የእይታውን ያህል እንጂ የመረጃውን ያህል አይደለም::
- ሰው ከእይታው በላይ አይሰፋም፣ ከእይታው በላይ አይሮጥም፣ ከእይታው በላይ አይወርስም፣ ከእይታው በላይ ፍሬን አያፈራም፣ ከእይታው በላይ አይኖርም፣ ከእይታው በላይ በመንፈሳዊም ሆነ በስጋዊ ሕይወቱ አያድግም::

# 6 የራእይ ገዳዮች

*«ከባለራእዩ አሉታዊ ባህሪይ ይልቅ ራእይን ሊጎዳ የሚችል ውጫዊ ኃይል የለም»*

ራእይ ይዘን መጓዝ ስንጀምር ሰይጣንና ራእይ የለሽ ክፉ ሰዎች ከራእያችን ሊለዩን ካልተሳካለቸው ከራእዩ ጋር ሊገድሉን ሰልፍ ያውጁብናል:: አንድ በማሕፀን ዕድገት የጀመረ ሕይወት አስፈላጊው ጥንቃቄና ክትትል ለእናቱና ለፅንሱ እስካልተደረገ ድረስ ስለ ተፀነሰ ብቻ እንደማይወለድ የታወቀ ነው:: አንድ ሕጻን ቀኑን ጠብቆ ስለተወለደ ብቻ እንደማያድግ ሁሉ አንድ ራእይ በአንድ ሰው ልብ ስለ ተፀነሰ ብቻ አይወለድም፣ ስለ ተወለደም ብቻ አያድግም:: መለኮታዊ ራእይ በመንፈሳዊ ማሕፀን ውስጥ እያለ ወይም ከተወለደም በኋላ ከፍተኛ ጥንቃቄና ክትትል ሊደረግለት የሚገባ ውድና መለኮታዊ ዘር ነው::

መለኮታዊ ራእይን ተቀብለን በልባችን እያደገ በንግግራችንና በሥራችን እየተገለጠ ሲመጣ ጠላትም ራእዩን ለማፍረስ ይተጋል:: ፈርኦን ባለራእዩ ሙሴ ገና ሳይወለድ ሞትን እንዳወጀበትና ሄሮድስ ባለራእዩ ኢየሱስ እንደተወለደ ሰምቶ ሞትን እንዳወጀበት ሁሉ ዛሬ ጠላት በውስጣችን ያለውን ራእይ ለማስጨንገፍ የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም:: ጠላት በልባችን ያለውን ራእይ ለመግደል የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች:-

## 1. ፍርሃት

ግሪኮች ፍርሃትን φόβος,phóbos, ብለው ሲጠሩት ትርጉሙም ከፊት ለፊት ያለውን አደጋ እንድንሸሽ ወይም እንድንጋፈጥ የሚያደርገን ውስጣዊ ስሜት ነው ይላሉ:: ሌሎች *FEAR* የሚለውን የእንግልዝኛ ቃል ስተነትኑ *"False Evidence Appearing Real"* በግርድፉ ሲተረጎም «የውሸት እውነት መስሎ መታየት» እንደ ማለት ነው::





በፍርሃት ላይ ስፊ ጥናት ያደርጉ ምሁራን እንደሚናገሩት ከሆነ ፍርሃትን ውጫዊና ውስጣዊ በማለት በሁለት ይከፍላሉ:: ውስጣዊ ፍርሃት ከአቅም ውስንነታና ካለመዘጋጀት ይህ ቢመጣብኝ አልችልም:: ከሚለው ውስጣዊ ጫና የተነሣ የሚመጣ የፍርሃት ዓይነት ሲሆን ውጫዊው የፍርሃት ዓይነት ደግሞ ከእኛ ቁጥጥር ውጪ ከተፈጥሮ፣ ከሰዎች፣ ከሁኔታና ከሰይጣን ሊመጡብን ይችላሉ ከሚለው ሀሳብ የተነሣ የሚመጣብን የፍርሃት ዓይነት እንደሆነ ይናገራሉ::[40] "Neurobiology" ምሁራን ፍርሃትንና ቁጣን የሚያመነጭ ቁልፍ የአንጎላችን ክፍል "amygdala"ይሉታል::[41] ብዙዎቻችን ከምንፈራቸው ነገሮች 80% ፈጽሞ ሊደርሱብን የማይችሉ እንደሆነም ይገልጻሉ:: ፍርሃት የእምነት ተቃራኒ ነው:: ፍርሃት የራእይ ገዳይ ነው:: በተለይ ለባለራእይ አደናቃፊ የሆኑትን ከብዙ የፍርሃት አይነቶች ሦስቱ እንመልከት:-

### ሀ. የሰው ፍርሃት /Androphobia/

*«የሚሞተውን ሰው እንደ ሣርም የሚጠወልገውን የሰውን ልጅ ትፈራ ዘንድ አንተ ማን ነህ?» (ኢሳ. 51: 12)*

የሰው ፍርሃት አደገኛና ጎጂ ከሆኑት የፍርሃት ዓይነቶች አንዱ ነው:: ከዛሬ 3000 ዓመት በፊት ታላቁ የእሥራኤል ጥበበኛው ንጉሥ ሰሎሞን በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ «ሰውን መፍራት ወጥመድ ያመጣል::» (ምሳሌ. 29: 24) ብሎ ነበር:: ሰውን እንድንወደውና እንድናከብረው እንጂ በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንድንፈራ ቃሉ አያዘንም:: ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስ ስለተሰጠን መንፈስ ሲናገር *«እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስን የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንም::»* (2ጢሞ1:7) ብሏል:: ይህን የተረዱ የእምነት አባቶች በምያስፈራሩአቸው ሰዎች ፊት ቆመው *«ጌታ ይረዳኛልና አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?» (ዕብ.13:7) በማለት በእምነት ተጋድለዋል::* የመለኮታዊ ራእይ አንዱ ቀንደኛ ጠላት ብቻ ሳይሆን ገዳይ የሆነው የፍርሃት አይነት የሰው ፍርሃት ነው:: ብዙ ታላላቅ ራእይ የነበራቸውና ራእዩቻቸው የሞቱባቸው ሰዎች እንዲህ ባደርግ ሰው ምን ይለኛል? ይህን ባደርግ ሰዎች አይቀበሉኝም፣ እንዲህ ብሠራ ሰው

[40] *Kahoe, R. D., & Dunn, R. F. (1976). "The fear of death and religious attitudes and behavior". Journal for the Scientific Study of Religion 14 (4): 379–382.*
[41] *http://en.wikipedia.org/wiki/Trends_in_Neurosciences*

አይረዳኝም፣ እገሌና እጌሊት እያሉ ራእዩን ከግቡ ማድረስ አልችልም:: በማለት ሰውን ፈርተው ራእይን በተቀበሉበት ስፈር የቀሩ ናቸው:: ለራእዩዎቻቸው ያለመሳካት ሰውን ምክንያት የሚያደርጉ ባለራእይዎች በሰው ፍርሃት የተያዙ ስለሆነ ከሰማይ የሆነ ራእይ ቢኖራቸውም እንኳ ራእዮቻቸው ተወልዶ፣ አድጎና ለፍሬ ሲበቃ ለማየት አይችሉም:: የሰው ፍርሃትን ማሸነፍ የሚንችለው የሰው ፈጣሪ በሆነው ጌታ ተማምነን መጓዝ ስንጀመር ብቻ ነው:: ጌታንና ከጌታ የተቀበልነውን ራእይ ስንወድ ሰውን መፍራት በልባችን ውስጥ ቦታ አይኖረውም «ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን ይጥላል::» (1ዮሐ. 4: 18) ቃሉ ይላልና::

## ለ. የውድቀት ፍርሃት /Atychiphobia/

*«ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃልና ይነሣማል::» (ምሳ 24: 16)*

አንድ መጋቢ ዶክተር ጆን ማክስዌልን «አንድ ሰው ትልቅ ነገር ለእግዚአብሔር ለማድርግ እንዳይነሣ የሚከለክለው ምንድነው?» ብሎ ስጠይቀው «ቀዳሚው የውድቀት ፍርሃት ነው» ብሎ መልሶለታል:: ውድቀት አደገኛ የሚሆነው እጃችንን ስንሰጠው ብቻ ሲሆን ከተጠቀምንበት ወደ ቀጣዩ ተራራ ለመውጣት ልዩ ትምህርት ቤት ይሆነናል:: መውደቅ ከሌለ መነሣት የለም:: መነሣት ከሌለ መውደቅ የለም:: ስኬት ማለት «ተስፋ ሳይቆሪጡ ከሽንፈት ወደ ሽንፈት መሄድ መቻል ነው» ያሉት ቢሊ ኮስቢ ሲሆን ለስኬት በወድቀት ውስጥ የማለፍ ሰዋዊ ግዴታችንን ለማመልከት እንጂ ሽንፈት ስኬት ነው ለማለት እንዳይደለ ለማንም ግልጽ ይመስለኛል:: ማይክል ጆርዳን «የዓለማችን የቅርጫት ኳስ ንጉሥ» የሚል ቅጽል ስም የተሰጠው ታላቅ ተጫዋች ሲሆን ስለዚህ ተጫዋች ጆን ማክስዌል ባለመሳካት ውስጥ ስለተገኘው ስኬት ሲገልፁ እንዲህ ጽፈዋል *«ማክይል ጆርዳን ከቡድኑ ጋር ስድስት ጊዜ ሻምፒዮን ቢሆንም በተጫወተባቸው አጠቃላይ ጨዋታዎች 12000 /አሥራ ሁለት ሺ/ ባስኬቶችን ወርውሮ ስቶአል፣ በ400 /አራት መቶ/ ጫወታዎች ውጤታማ አልነበረም 25 /ሃያ አምስት/ ለማሸነፊያ የሚሆኑ ወሳኝ ባስኬቶችን ለመጠቀም አልቻልም::»*





ይህ ሁሉ ያለመሳካት ማይክል ጆርዳንን የዓለማችን አንድ ቁጥር የቅርጫት ኳስ ጀግና እንዳይሆን ካልከለከሉት የትኛውም የውድቀት ዓይነትና ሁኔታ አንተ እጅ ካልሰጠኸው በስተቀር በፍጹም ሊያስቀርህ አይችልም:: እግዚአብሔር ራእይን ሲሰጠን ብንወድቅም እንደምያነሣን በቃሉ ኪዳን ገብቶልን ነው:: ባለራእይ ፍጹም የማይወድቅና ውድቀቱን እየደገመ የሚኖር ሰው አይደለም:: ባንተ ያለው የእግዚአብሔር የራእዩ ዘር ከውድቀት ያነሣሃል እንጂ በውድቀት አይሸነፍም:: ሰው ውድቀትን ይፈራል፣ ወድቆም ከውድቀት ሊሸሽግ ይሞክራል፣ ወድቆም ውድቀትን ይክዳል፣ ይህን ሁሉ ብናደርግ ከውድቀት ማምለጥ ግን አንችልም:: ውድቀትን ለማሸነፍ ወድቆ በተነሣው አሁንም መውደቅ በሚችለው ነገር ግን በውድቀት ለመኖር በፍፁም በማይፈቅደው አዲስ ማንነት ለመግጠም ስንዘጋጅ ብቻ ነው::

በውድቀት ፍርሃት የተያዙ ሰዎች ምልክታቸው ይህን አደርጋለሁ ብዬ ባይሳካልኝስ? ይህን ንግድ ጀምሬ ብከስርስ? ለበሽተኛ ጸልዬ ባይፈወስስ? ይህን ጀምሬ ያለኝንም ባጣስ? የሚሉ ሲሆን በዚህ ፍርሃት ተይዘው ቁጭ ያሉ ሰዎች ለማለም እንጂ ህልማቸውን እውን ለማድረግ ከህልማቸው መንቃት አይሆንላቸውም:: ብዙዎች ለማግኘት ብቁ የሚያደርገን በእጃችን ያለውን ለማጣት መፍቀድ እንደሆነ ይዘነጋሉ:: ባለራእይ ያልወደቀ ሳይሆን ወድቆ የተነሣና በራእይው መንገድ ቢወድቅ እንኳ ራእዩን የሰጠው አምላክ ከውድቀቱ እንደሚያነሣው አውቆ የወጣ ሰው ነው:: ባለራእይ በውድቀት ፍርሃት ተሞልቶ ሳይሆን በትልቅ እምነትና ድፍረት ወደ ፊት የሚጓዝ ጨካኝ ሰው ነው:: ውድቀትን ፈርቶ ያለመሥራት ከውድቀት ሊጠብቀን አይችልም:: እንዲያውም ያለ ሥራ ለመክበር በሚፈለግ አደገኛ ውድቀት ውስጥ ያስገባናል:: የውድቀት ፍርሃት ራእይን የሚገድል ስለሆነ ባላራእይ በልቡ ቦታ ሊሰጠው አይገባም:: ከውድቀት ይልቅ የውድቀት ፍርሃት የሚያመጣብን ተጽዕኖ በጣም ትልቅ ነው::

## ሐ. የለውጥ ፍርሃት /Metathesiophobia/

የለውጥ ፍርሃት ለውጥን እንድንቃወም የሚያደርገን የመጀመሪያው ምክንያት ነው:: ሕይወት ያለ ለውጥ ሙት እንደሆነች አንዘንጋ:: ሐመረ ታደገ ሰዎች ለውጥን ለምን እንደሚጠሉ ስትገልጽ *«ለውጥ አስፈሪ፣ ግራ አጋቢ እና የነበረውን ሁሉ እንዳልነበረ የሚያደርግ በመሆኑ ሰዎች ከጅምሩ ለውጡን ቢጠሉት ሊያስገርመን አይገባም::»* [42] ትላለች:: ባለራእይ መሪ በለውጥ ያምናል:: የኬንያ ዝርያ ያለው የመጀመሪያው የአሜሪካ 44ኛው ጥቁር ፕሬዝዳንት ባራክ ሁሴን ኦቦማ በፍጹም ያልተጠበቀ ሰው ምርጫ በማሸነፍ ዋይት ሀውስ መርገጥ የቻለው «ለውጥ ይቻላል» በሚል ትኬት እንደ ነበር ይታወቃል::

ራእይ አይቻልምን በይቻላል የመቀየር ኃይል አለው:: ራእይ የለውጥ አባት ነው:: እውነተኛ ራእይ እውቅና ባገኘበት ለውጥ ይሆናል:: ብዙ ሰዎች ራእይ የሚያመጣውን ለውጥ ስለሚፈሩ ብቻ የራእይን ውጤት እየፈለጉ ከለውጥ ፍርሃት የተነሣ ራእይን በእጅ አዙር ለመዋጋት ይገደዳሉ:: ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ ራእይ መር እንዳትሆን ማነቆ ከሚሆኑባት ነገሮች መካከል አንዱ የለውጥ ፍርሃት ነው:: ለውጥን መፍራት ከለውጥ ሊታደገን አይችልም:: የላቀና የሚበልጥ ነገር ከተፈለገ ለውጥ የግድ ነው:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አመራር አንዱና ትልቅ ችግር ለውጥን መፍራት ብቻ ሳይሆን ፍጹም ያለ መፈለግ እንደሆነ ይነገራል:: የቀድሞ የኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ዋና ጸሐፊ የነበሩት መጋቢ ስዩም ገ/ጻድቅ በጥናታዊ ጽሑፋቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለለውጥ ያላትን አቋም ሲገልጹ *«ተተኪውን ትውልድ የማያሳትፍ! የለውጥ አቋም የሌለው ሆኖ መገኘቱ»*[43] ብለዋል::

ከእግዚአብሔር የተቀበልነው መለኮታዊ ራእይ የሚያመጣውን አዎንታዊ ለውጥ ለማስተናገድ ካልተዘጋጀን በተቃራኒው ለጥቅማችን የመጣውን ራእይ ከለውጥ

[42] *ሐመረ ታደገ:: <u>የሥራ ሂደት ለውጥ (ቢ.ፒ. አር)</u>:: ዛጎል መልቲ ሚዲያ አሳታሚ ኃ.የ.ተ.የግል:: አዲስ አበባ 2001 ዓ.ም*

[43] *ስዩም ገ/ጻድቅ:: <u>«ብሔራዊ የወንጌል አገልግሎት ወቅታዊ ሁኔታ»</u> በሚል ርዕስ በሶዶሬ የወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት ኅብረት መሪዎች በቀረበው ጥናታዊ ጽሑፋቸው ጥቅምት 1999 ዓ.ም*





ፍርሃት የተነሣ ለመግደል መነሣታችን አይቀሬ ነው:: የለውጥ ፍርሃት የያዛቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራእይን በመርህ ደረጃ ቢያስተናግዱም ከሚያመጣባቸው ነውጥ የተነሣ ሳያውቁት በግልጽ እያወቁት በስውር ይዋጉታል:: በአጠቃላይ ለውጥ ከሌለ ራእይ የለም:: መለኮታዊ ራእይ ፍርሃት ለኃይልና ለተስፋ ቦታውን እንዲለቁ ያደርጋል:: ያለማመንን ገርስሶ በሰላምና በእምነት ይሞላናል:: ስለመጪው በፍርሃት መሰቃየት ሁሉን የሚችለው አምላክ በአንተ አልፎ ሊሠራ ለተነሣው ታላቅ ሥራ እምነት የማጣት ምልክት ነው:: ጌታ ራእይን ሲሰጥህ አንዳች ነገር እንድትሠራለት አስቦ ሳይሆን በአንተ አንድ ነገር ለመሥራት ነው::

## 2. ልምድ /ባሕል/

እንዳለ ገ/መስቀል የልምድን አሉታዊ ተጽዕኖ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲገልጹ:- *«ልማዳዊ የዘመናት አመራር ከመዘውተሩም ባሻገር መዋቅሮች ቀኖና ይመስል ንቅንቅ ፣ ዝንፍ አይሉም:: ብዙ መዋቅሮች ራእይ አልባ የሆኑ መሪዎች ዓላማ መጫሚያና መረማመጃ ብቻ ናቸው::»*[44] ብለዋል:: «እግዚአብሔር ያለፈውንና ያለውን የዱሮ ልምዳችንን እንድንለውጥ *አያደርገንም»* የሚል አመለካከት በጠንካራ ልምድ ላይ እንደቆምን የሚያመለክት ሲሆን ይኸንንም በሚከተሉት ጠንካራ ቃላቶች እንገልጻቸዋለን *«እንደዚህ አልለመድነውም!» «ውስጠ ደንባችን አይፈቅድም»* «ጠቅላላ ጉባዔው አልተቀበለውም!» «አዲስ አሠራር ስለሆነ አይመቸንም!» *«አዲስ ስለሆነ አንቀበልም!» «ከእኛ አሠራርና አካሄድ ጋር ስለማይጣጣም አይሆንም!»*:: «ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ»[45] እነዚህ ሰዎች ቋሚ አሠራር እንደሌለ ያውቁ ይሆን? ይህ መንፈስ የራእይ ገዳይ መንፈስ ነው::

[44] *ሕይወት መጽሔት ቁጥር 49 <u>«መሠረታዊ የኢትዮጵያ ቤ/ክ ችግሮችና የመፍትሔ ሐሳቦች»</u> መጋቢት 1993 ዓ. ም ገጽ 15*

[45] *ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ:: <u>ደቂቀ እስጢፋኖስ በሕግ አምላክ</u>:: በተሰኘው መጽሐፍ መግቢያ ላይ ፕሮፌሰር መሰፍን ወልደማርያም ቀዳሚሁ ቃል በሚለው ርዕስ ሥር <u>«ሲወርድ ሲዋረድ»</u> የሚለውን ፈሊጣችንን ሲገልጹ:- የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሲወርድ ሲዋረድ በሚል በማያስብና በማያሳስብ የቁልቁለት አስተሳሰብ ለብዙ ዓመታት ተጉዘው ውጤቱ ያለንበት ደረጃ ነው:: ብለዋል*

## ልምዳችን መነሻችን እንጂ መድረሻን ሊሆን አይገባም

ልምድ በራሱ መጥፎ አይደለም:: የሁላችንም የዛሬ ማንነታችን የትላንቱ ልምድና ፈርጀ ብዙ የሕይወት ተሞክሮዎች ውጤቶች ነንና:: ነገር ግን የትላንትና ልምድና ባሕላችን ያለፈውንና መጪውን አገናኝ ድልድይ መሆኑ ቀርቶ የሁልጊዜ መመሪያ በማድረግ በእርሱ ላይ ብቻ ስናተኩር የራእይ ሳይሆን የልምድ አራማጆች ለመሆን እንገደዳለን:: የልምድ አዋላጆች እንኳ ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን በመቀበል የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት በታደሉበት ምድርና ዘመን ትላንት የታገዝንባቸው ዛሬ የተደናቀፍንባቸው የቆየ ልምዳችን እንደ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና የበላይ ሆነው የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ሲገቱ ማየት ያሳዝናል:: እግዚአብሔር ግን ያለፈው ልምዳችን የአሁኑን ዕድገት እንዲያግዝ እንጂ እንዲያደናቅፍ አይፈቅድም:: እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ዕድገትና ለሕዝቡ በረከት የሆኑትን ያለፉትን ልምዶችና መልካም ባሕላችንን የባረከው የማይነኩ ቅዱስ ልምዶች ስለሆኑ ሳይሆን ዕቅዱንና ዓላማውን ከማስፈጸም አኳያ በጊዜው ሚና በመጫወታቸው ብቻ ነው:: ከዚህም የተነሣ ያደግንበትን ልምድና ባሕል እንደገና ይቀርጻል፣ ያድሳል ወይም ሙሉ በሙሉ ይለውጣል:: የትላንቱ መንፈሳዊ ባህልና ልምድ የትላንቱን መለኮታዊ ዓላማ ተሸክሞ እንዲሄድ የተጠቀምንበት ተለዋዋጭ መሣሪያ እንጂ ሁሌ የምንኖርበት መለኮታዊ ቃል ወይም መርህ አይደሉም:: እግዚአብሔር ትልቅ ትኩረት እንድናደርግ የሚፈልገው በተለዋዋጭ አሠራርና ልምድ ላይ ሳይሆን በማይለዋወጠው ማንነቱና በቃሉ ላይ ብቻ ነው:: ልምድና ባህል ሁልጊዜ የባለፈው ነገር ነፀብራቅ ሲሆኑ ራእይ ግን የመጪው ነፀብራቅ ነው:: ያለፈው ታሪካችን ለአዲስ ራእይ የመውጊያ ብረት ሳይሆን ወደ ላይ መውጫ መሰላል ሊሆን ይገባል:: መንፈሳዊ ብስለት ማለት ከባለፈው ሙላትና ጉድለት በላይ ማደግ እንጂ በባለፈው ልምድና መልካም ነገር ተይዘን የአሁኑን ታላቅ የለውጥ ዕድል በከንቱ ማሳለፍ ማለት አይደለም:: በአገልግሎታችን ሳለፈው መጥፎም ቢሆን ጥሩ ልምድ እውቅና ልንሰጥ ይገባል:: እኛ የትላንቱ መልካም ነገር ብቻ ሳይሆን የመጥፎ ገጠመኝ ውጤቶች ነንና::





የትላንቱ መልካም አሠራር፣ አካሄድና አስደናቂ ውጤት ለዛሬው እርምጃችን እንቅፋት እንዲሆንብን ሳይሆን አገልግሎታችንን ወደ ላቀ ምዕራፍ ለማሻገር እንደ መወጣጫ ደረጃ ልንጠቀምበት ይገባል:: ያለፈውን ከአሁኑና ከመጪው ጋር ተደጋጋፊ እንጂ እርስ በርሱ ተናዳፊ እናድርገው:: ጌታ ይርዳን::

**መንፈሳዊ ቢ.ፒ.አር?**/*BPR-Business Process Re enginereeing*/ ቢ.ፒ.አር[46] በማሰቾሰት ኢንስቲትዮት ኦፍ ተክኖሎጂ የኮምፒዩተር ሳይነስ ፕሮፌሰር የነበሩ የማይክል ሐመር የአዕምሮ ውጤት ነው:: ታይምስ መጽሔት ከዚህ ሥራ የተነሣ ማይክል ሐመርን «ከ25 እውቅ የአሜሪካ ተጽኖ ፈጣሪዎች አንዱ ሰው» ብሎታል::[47] *«የመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ»* (ቢ.ፒ.አር) ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ሐመረ ታደገ *«የመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ»* (ቢ.ፒ.አር) በሚለው መጽሐፍዋ መግቢያ እንዲህ አስቀምጣለች:-

> *«ላለፉት ሁለት መቶ ዓመታት ሲሠራባቸው የነበሩትን የኢንዱስትሪ ሥራ አመራር ዕሳቤዎች መተው ማለት ነው:: … በሥራ ሂደት ለውጥ ውስጥ አሮጌ የሥራ መደቦችና አሮጌ ድርጅታዊ አወቃቀሮቻቸው (ዲፓርትመንቶች፣ ዲቪዥኖች፣ ክፍሎችና የመሳሰሉት) ሀልውናቸው ያከትማል:: የሌላ ዘመን መሣሪያዎች ናቸውና::»*[48]

ዛሬ በዓለም ላይ በሀገራችንም ጭምር ያልተለመደ ይህ «የመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ» (ቢ.ፒ.አር) አብዮት እየተካሄደ ያለ ይመስላል:: የዚህ የለውጥ አውሎ ንፋስ ዋና ዓላማ ያረጀውን የ200 ዓመታት የሥራን ሂደትን በመለወጥ ከ21ኛው ክፍለ ዘመን ትውልድና ዕድገት ጋር የሚመጥን አዲስ የሥራንና የአሠራርን ለውጥ ለማምጣት እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በአንዳንዶች ዘንድ ሀሳቡ

---

46 *"Reengineering is the fundamental rethinking and radical redesign of business processes to achieve dramatic improvements in critical, contemporary measures of performance, such as cost, quality, service, and speed."—Hammer and Champy, 1993*

47 *http://www.time.com/time/magazine/article/0,9171,984696-13,00.html*

48 Ibid, ገጽ viii

ተቃውሞ ቢገጥመውም በብዙ መንግሥታዊና የግል ደርጅቶች ተቀባይነትን አግኝቶ ያረጀውን የሥራ ባሕልና ሂደት በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ በመለወጥ ላይ እንደሚገኝ ጥናቶች ያመለክታሉ:: ስለ ቢ.ፒ.አር ምንነት ለማወቅ አንዳንድ መዛግብቶች ሳገላብጥ መንፈሳዊ ቢ.ፒ.አር ለቤተ ክርስቲያን ያስፈልግ ይሆን? ብያለው ካለ:: ባለራእይ አዲስ ራእይን በሚመጥንና ሊያስኬድ በሚችል አሠራር እንጂ «አሮጌው የዘላለም ነው» በማለት ለዱሮ አሠራርም ሆነ የሥራ ሂደት ጥብቅና አይቆምም:: እግዚአብሔር አንድን ሥራ በተለያየ መንገድ የሚሠራ አምላክ ነው:: በአንድ ዘመን የቀይ ባሕርን ውሃ በሙሴ በትር ሲከፍል በኢያሱ ዘመን የዮርዳኖስን ውሃ በካህናቶች እግር ከፍሎዋል:: በቤተ ክርስቲያን በሆነ ዘመንና ጊዜ አስፈላጊነታቸው በሁሉ ዘንድ ታውቆ የዛሬው ዕድገት እንዲገኝ ትላንት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ አሠራሮች ዛሬ ግን ቀኑ ያለፈባቸው የሉም? የትላንትናው አሠራርና አመራር ምርኩዝ እንድሆኑ ትላንት ከቃሉ በታች ሆነው የተሠሩ ውስጠ ደንቦች ዛሬ ግን የእግዚአብሔርን ቃል እስኪጋርዱና የቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ወደ መሆን ያደጉ ያረጁ አስተሳሰቦች የሉም? የባለፈው ትውልድ አሠራር ለአሁኑ ትውልድ ታሪክ እንጂ መመሪያ ሊሆን እንዳማይችል ስንቶቻችን እንቀበላለን? ኢያሱና ሙሴ አንድ አምላክ ቢኖራቸውም ትውልዳቸው፣ አሠራራቸውና የተሰጣቸው ተልዕኮ ለየቅል ነበር::

ይህን በዓለም ላይ እየነፈሰ ያለውን አሮጌ አሠራሮችን የሚያስወግድ የለውጥ አውሎ ንፋስ ቤተ ክርስቲያን ነቅታ በመረዳት እንደቃሉ ነገሮችን ማስተካከል ካልቻለች በአሉታዊ ጎኑ እንዳይለውጣት ያስፈራል:: አንድ መርህ በዓለም ላይ ተሠርቶበት ትልቅ እመርታን ስላሳየ ብቻ በቤተ ክርስቲያንም ለመተግበር ብንነሣ ውጤቱ መልካም ላይሆን ይችላል:: በቤተ ክርስቲያን ያረጀ አሠራር፣ ግልጽነት የጎደላቸው አካሄዶች፣ ወገናዊነትን ያጎሉ ውሳኔዎች፣ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያላደረጉ ሹመቶች፣ ግኑኝነት ተኮር ሳይሆን ተግባር ተኮር ሂደቶች፣ ያልዳነውን ዓለም ቻል ብሎ በዳኑት ጥቂቶች ብቻ ያነጣጠሩ አገልግሎቶች፣ ለአሮጌው እንጂ ለአዲስ ራእይ አንደበት እንጂ ቦታ የሌላቸው ድርጅታዊ መዋቅሮች፣ የመቀበል





እንጂ የመስጠት ዝንባሌ የማይታይበት አሠራርና አመራር አፋጣኝ ቃሉንና መንፈሱን ማዕከል ያደረገ ለውጥን ማስተናገድ ካልፈቀደ አሉታዊ የለውጥ ጎርፍ ቤተ ክርስቲያንን ሊያጥለቀልቃት ይችላል:: እንደ ቀደመችው የሰሜን አፍሪካና እንደ ዘመናችን የምዕራባዊት ቤተ ክርስቲያን:: ለአዲስ አቁማዳ አዲስ ወይን ጠጅ እንጂ ለአሮጌ አቁማዳ አዲስ ወይን ጠጅ አደገኛ እንደሆነ ኢየሱስም ከዛሬ 2000 ዓመታት በፊት እንዲህ ብሎ ነበር *«አሮጌውን የወይን ጠጅ ሲጠጣ አዲሱን የሚሻ ማንም የለም አሮጌው ይጣፍጣል ይላልና::»* (ሉቃ. 5: 39):: ይህ በአሮጌውና በአዲሱ አመለካከት መካከል እየተካሄደ ያለው ጦርነት በዓለም ብቻ ሳይሆን በዓለም ባለችው ቤተ ክርስቲያንም ያው ነው:: ፍጥጫው እንዲከር ያደረገው የአሮጌ ናፋቂዎች በቀላሉ ለአዲሱ አሠራር እጅ ያለመስጠትና የአዲሱ ሀሳብ አራማጆችም ለአሮጌው ዕውቅና ያለመስጠት ይመስላል:: ሊታወቅ የሚገባው ቁም ነገር አሮጌው የአዲሱ እንዲሁም አዲሱም የአሮጌ አንዱ ገጽታ መሆናቸውን ነው:: አንዱ ያለ አንዱ ብቻውን መኖር አይችልም:: አሮጌው አሮጌ የተባለው አዲስ ስለመጣ ነው:: አዲሱም አዲስ የተባለው አሮጌው በመኖሩ ነው:: ያላንዱ ሌላው መወለድም ሆነ ማደግ አይታሰብም:: ዕድገት የአሮጌና የአዲሱ ግጭት ውጤት ነው:: እግዚአብሔር አዲሱን ትውልድ ሁልጊዜ ለለውጥ ያስነሳል:: የቆየው ትውልድ ነገሮችን ማቆየት ስውድ አዲሱ ደግሞ ያንን ይተቻል:: በሁለቱም መካከል በሚደረገው ግጭት ሰበቃ /Friction/ ይፈጠራል:: ሰበቃው ለዕድገት ግብአት የሚሆን ኃይል ያመነጫል:: የቆየው ትውልድ ካለፈው አዲሱ ትውልድ ደግሞ ከመጭው ጋር የሚያገናኝን ድልድይ ስለሆኑ ሁለቱም ያስፈልጉናል:: አዲሱ ትውልድ የቆዩ ሰዎች ጥበብ ስያስፈልጋቸው የቆዩ ሰዎች ደግሞ የአዲሱ ትውልድ ራእይ ያስፈልጋቸዋል:: አንዱ ያለ አንዱ ሙሉ አይሆንም::

ዓለም በአዲሱና በአሮጌው መካከል ላለው ጦርነት ቢ.ፒ.አር *(መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ)* እየተጠቀመች ሲሆን ቤተ ክርስቲያን የራስዋን ቢ.ፒ.አር መርሆዎች ከቃሉ በማውጣት ለዘመናት ያረጀውን አሠራር መቀየር ካልቻለች ከትውልዱ ጋር የመተላለፍ አደጋ ተጋርጦባታል:: ቤተ ክርስቲያን በቃሉና በመንፈሱ፣ ትውልዱን በመቅደም፣ አርቆ በማየት፣ እግዚአብሔርን በመስማት በአሠራሮች፣ በአካሄዶች፣

ባረጀ አመለካከት ላይ ሥር ነቀል ለውጥ ለማድረግ ካልተዘጋጀች የዓለማዊው /Secular/ የመንግሥት ቢሮዎች ቢ.ፒ.አር ሞዴል ተጠቂ ላለመሆን ምርጫ የላትም:: አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቢሮ የሥራ ሂደት ለውጥን በቤተ ክርስቲያን ሲጠቀሙ ይታያሉ:: ይህ ሊሆን የቻለው ሆን ተብሎ የዓለምን አሠራር ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስገባት ታስቦ አይደለም:: በመንግሥት ቢሮዎች በቢ.ፒ.አር ላይ የሚሠሩ ብዙዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች(ሽማግሌዎች) ስለሆኑ ቤተ ክርስቲያንን ለማገዝ ብለው የውጪውን አሠራር በቤተ ክርስቲያን ለመተግበር ሲታገሉ ይታያሉ:: ይህም አደገኛ አካሄድ ነው:: የመረብ ኳስ ሕግ ለእግር ኳስ እንደማይሆን ሁሉ የፈለገ አመርቂ ውጤት ያስገኘ የዓለም የሥራ ሂደት ለውጥ ለቤተ ክርስቲያን አይሆንም:: የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ መለኮታዊ እንደመሆኑ መጠን መለኮታዊ አመራር የግድ ያስፈልጋታል:: ቤተ ክርስቲያን በዓለም እንጂ ከዓለም እንዳልሆነች ሁሉ በቃሉና በመንፈሱ መርህ ላይ የተመሠረቱ አዲስ ትውልድና አዲስ አሠራር ያስፈልጋታል:: ሁለቱም እንዲጠባበቁ::

### 3. ተስፋ መቁረጥ

*«ከጦር ሜዳ በመሸሽ ጦርነትን አናሸንፍም» ዊንስተ ቸርችል*

ትልልቅ ነገሮችን በማየት ለሚነሣ ሰው ፈተናው ብዙ ነው:: ዓለማችን በብዙ ተመልካቾችና ጥቂት ባለራእዮች ስለተጨናነቀች አንድን ባዕድ የምመስለውን ነገር ለማድረግ ስንነሣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንደማይሆን ሰዎች ደጋግመው በመንገር ተስፋ ሊያስቆርጡን ይከጅላሉ:: ኑኃሚን አማቶችዋን ዖርፋና ሩትን ያለችበትን ድህነትና አሳዛኝ ሁኔታ እንዲሁም የመጭውን ባዶነት በማሳየት እርሷን ከመከተል ተስፋ ቆርጠው እንዲመለሱ ነገረቻቸው:: እነርሱም «ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው እንደ ገና አለቀሱ ዖርፋም አማትዋን ሳመች ሩት ግን ተጠጋቻት::» (ሩት. 1:14) ሩትና ዖርፋ ሁለቱም ሞአባዊያን፣ የኑኃሚን አማቶች፣ በወጣትነት ባሎቻቸው የሞቱባቸው ባልቴቶች፣ አንድ ዓይነት ምርጫ ቀርቦላቸው አንድ ላይ ቢያለቅሱም ውሳኔቸው ለያያቸው:: ዖርፋ በጊዜያዊ ጨለማ፣ የልብ ስብራት፣ መከራና ባዶነት ተስፋ ቆርጣ ድምጽዋን ከፍ አድርጋ





በማልቀስ ወደ ኋላ የመመለስ አቅም ቢኖራትም ኑኃሚንን የመከተል ጉልበት ግን አልቀረላትም:: የዖርፋ አማትዋን መሳም የፍቅር ብቻ ሳይሆን የተስፋ መቁረጥ ምልክት ነበር:: ተስፋ ቆርጣ የተመለሰች የዖርፋ ታሪክ በዚሁ አበቃ:: *«ሩት ግን ተጠጋቻት» ይላል:: ሩት እንደ ዖርፋ ኑኃሚንን ባትስምም ልቧ ከእርሷ ጋር በመጣበቁ «በምትሞችበትም ስፍራ እሞታለሁ» (ሩት 1: 16) በማለት ለእርሷ ካላት ፍቅርና አክብሮት የተነሳ ከእርሷ ጋር ለመኖር ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለመሞት ወስና ተከተለቻት::* ሩት ተስፋ ሳትቆርጥ የራስዋን ጣኦቶች በኑኃሚን አምላክ ቀይራ ሀገሯን፣ ሕዝባንና ባሕሏን ሁሉ ወደ ኋላ ትታ በእምነትና በጭካኔ ባደረገችው ፈታኝ ጉዞ በክርስቶስ የዘር ሃርግ ውስጥ ተጋፍታ የገባች ብቸኛ ሞአባዊት ሆናለች::

ሩት የሚሆነውን ሳታውቅ ተስፋ የለሽ አማትዋን በእምነት ተከትላ ለትልቅ ክብር ከበቃች በሕይወት ዘመናችን ሊሆን ያለውን አሳውቆንና አመልክቶን ጌታ ከጠራን ተስፋ ልንቆርጥ በፍጹም አይገባንም:: ባለራእይ እስከ መጨረሻው ተስፋ አይቆርጥም ምክንያቱም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በውስጡ ስለሆነ ነው (ቆላ 1:23) ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች ስለሌሉ ሳይሆን ተስፋ ላለመቁረጥ ራእዩን በሰጠው ጌታ ላይ ስለሚታመን ነው:: ለዚህም ነው ጳውሎስ *«እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም»* (2ቆሮ 4:8) ከማለቱ በፊት *«የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ውስጥ አለን» (2ቆሮ4:7) ያለው::*

ተስፋ መቁረጥ የሚባል ቃል በባለራእይ በባለራእይ ልብ ውስጥ ባለው መዝገበ ውስጥ የለም:: አሸናፊ ተስፋ አይቆርጥም:: ተስፋ የሚቆርጥም አያሸንፍም:: *«በእምነትና በትዕግስት በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን::»* (ዕብ 6:11-12) «ትልቅ ድል ያለው ባለመውደቅ ውስጥ ሳይሆን ስንወድቅ ሁሌ ለመነሳት በመታገል ውስጥ ነው::» *ያሉት ራልፍ ዋልዶ ነው::*

## 4. በእግዚአብሔር ያልተጠሩ አገልጋዮች

*«...የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል::» (ዮሐ. 16: 1-2)::*

በቤተ ክርስቲያን ያሉ አገልጋዮች በሦስት ይከፈላሉ:: የመጀመሪያዎቹ ራሳቸውን የጠሩ፣ ሲሆኑ ነገሮችን ከግላዊ ጥቅም አንጻር ብቻ የሚያዩ ናቸው:: ሁለተኛዎቹ በሰው (በዘመድ፣ በጎሳ፣ በጎጥ ወዘተ) የተጠሩ - ነገሮችን ከወከሉት ግለሰብና ቡድን አንጻር ብቻ የሚያዩና ሦስተኛዎቹ በእግዚአብሔር የተጠሩና ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰው ልጆች መዳን ብቻ የሚኖሩ ናቸው:: እነኝህ ራሳቸውን የጠሩና በሰው የተጠሩ «አገልጋዮች» የጫማ ውስጥ እሾክ ሆነው የአገልግሎት ራእይ ያለውን በእግዚአብሔር የተጠራውን አገልጋይ ወደ ፊት እንዳይሄድ ይታገሉታል:: *«ሴዴቅያስ ቀረበ ሚክያስንም ጉንጩን በጥፊ መታው»* (1ነገ. 22: 24- 28):: በብሉይ ኪዳን ዘመን የነቢዩ ሚክያስን አገልግሎት የተገዳደሩት ከቤተ መንግሥት እስከ ቤተ መቅደስ በመዋቅር የተደራጁና የተሳሰሩ ቅልብ የንጉሥ አክአብ «ነቢያቶች» ዋና ሥራቸው ሁለት ነበር:: አንደኛ የአክአብን የልቡን ምኞት አንብበው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በሚለው መሸፈኛ የውሸትን እንጀራ ማጉረስ ሁለተኛው እውነተኛ ቃል ያላቸውን አገልጋዮች እስከ ሞት ማሳደድ ነበር:: ጳውሎስ «ሆዳቸው አምላካቸው» እንዳለው እንደነዚህ ያሉትን ምግብ አምላኪዎች እንላቸዋለን:: ለነቢዩ ኤርምያስ አገልግሎትም ጋሬጣ የሆኑበት እንደነዚህ «ዋሽቶ አዳሪ» የነቢይነትን ስም የተሸከሙ ዋሾዎች ነበሩ::

በእኛም ዘመን ለህብታም እንጂ ለድሃ የትንቢት ቃል ሳይሆን ሰላምታ ቃል እንኳ የሌላቸው፣ የእግዚአብሔር ስም ኑሮአቸው ያደረጉ እንደ ኤሊ ልጆች እግዚአብሔርን ግን የማያውቁ፣ በእግዚአብሔር ስም ለመክበር እንጂ ስለ እግዚአብሔር መዋረድን እንደ ትልቅ ውድቀት የሚቆጥሩ፣ ከፍታ ላይ ዘሎ ለማዘለል እንጂ ሸለቆ ወርደው መጋፈጥ የማይፈቅዱ፣ ዓርብ ሳይሞቱ እሑድ የተነሱ፣ ከእውነተኛ አገልጋዩች ይልቅ የብርሃን መላእክት መሳዮች በየጓዳው





እንደ እሸን ፈልተው ትልቅ ግራ መጋባትን በመፍጠር ላይ ይገኛሉ:: ነገሮች እንዲህ በመሆን ግን አይቀጥሉም::

«በነቢይ»ና በነቢይ መካከል፣ «በሐዋርያ»ና በሐዋርያ መካከል፣ በ«በመጋቢ»ና በመጋቢ መካከል ልዩነት በኢትዮጵያ ይሆናል:: የሚመስሉ ሳይሆን የሆኑ ባለራእይ አገልጋዮች በምድራችን የሚገለጡበት ዘመን አሁን ነው:: *«ነቢዩ ኤርምያስ ነቢዩ ሐናኒያን:- ሐናኒያ ሆይ ስማ ይህ ሕዝብ በውሸት እንዲታመን አድርገሃል እንጂ እግዚአብሔር አልላከህም::»* (ኤር. 28: 15) በጣም የሚገርመው የመጽሐፍ ቅዱስ ለእነዚህ አደገኛ የውሸት መልዕክተኞችም «ነቢይ» ብሎ መጥራቱ ሲሆን ይህም ስም እያላቸው ሙት መሆናቸውን ለማመልከት ነው:: «ስም አለህ ሞተህማል» (ራእ. 3: 1)::

እነዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነው የባለራእይን ልብ በአንደበታቸው መራራ ቃል፣ በአድመኝነት፣ ስሙን በማጥፋት /Character Assenassions/ ከቻሉም ለመግደል በሙሉ ኃይላቸው ይንቀሳቀሳሉ:: እነዚህ ሰዎች «ሰባኪዎች» የተባሉ ሊሆኑ ይችላሉ፣ በመሪነት ወንበር የተቀመጡ ሊሆኑ ይችላሉ፣ በብዙሃን ዘንድ መልካም ስም ያላቸው የተመሰከረላቸው «አገልጋዮች» ሊሆኑም ይችላሉ:: ባለራእይን ሲያገኙ «ጌታ ይባርክህ! በርታ!» እያሉት በሌሎች እጅ የባለራእይን ራስ የመምታት የረኸርም ዘመን መሰሪ ልምድ ስላላቸው ለጊዜው በቀላሉ አይለዩም:: አንዳንዶች የባለራእይ ወዳጅና የጸሎት አጋር መስለው የልቡን ትርታ አድምጠው ወዲያው ራእዩን ለማሰጨንገፍ በስውር ሸንጎ ለጠራው ቡድን መረጃን ያቀብላሉ:: ታላቁ ባለራእይ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እንደዚህ አይነት ሰዎች የፍርሃቱ አንዱ ምክንያት እንደሆኑበት ሲናገር *«በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት...» (2ቆሮ. 11: 26) ይላል::* ባለራእይ ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሲሠራ ከእርሱ ጋር ውለው እያደሩ አብረውም ስለቅጥሩ እየተመካከሩ ለባለራእዩ ባላንጣ ለጦቢያ በደብዳቤ መረጃ በማቀበልና የወሬ አመላላሾች እጅግ እንደ ተፈታተኑት ይናገራል *«በዚያ ወራት ብዙ የይሁዳ አለቆች ወደ ጦብያም ደብደቤዎች ይልኩ ነበር::*

*«.. ደግሞም በፊቴ ስለ እርሱ መልካም ይናገሩ ነበር ቃሌንም ያወሩለት ነበር ጦብያም ሊያስፈራራኝ ደብዳቤዎችን ይልክ ነበር::» (ነሀ. 6: 18 - 19)* ደስ የሚለው ግን እግዚአብሔር ባለራእይን የተወውና የዘገየ ቢመስልም በራሱ ጊዜ

ከባለራእይው ጋር ማንነቱን ለሁሉ ሲገልጥ ክፋትን አቅደው ይሠሩ የነበሩ ሁሉ እፍረትን ይከናነባሉ:: ነህምያ ስለዚህም ስናገር «ጠላቶቻችንም ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ በዙርያችን የነበሩ አሕዛብ ሁሉ ፈሩ በራሳቸውም አሳብ እጅግ ተዋረዱ ይህም ሥራ በእግዚአብሔር እንደ ተደረገ አወቁ::» (ነህ: 6: 15 - 16) እግዚአብሔር ነገሩን ይገለብጣል:: እግዚአብሔርም ክብሩን ይወስዳል::

## 5. የገንዘብ ፍቅር

*«ዳሩ ግን ባለጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና፣ በመፍረስ፣ ሰዎችን በሚያሰጥምና፣ በሚያስነፍ፣ በሚጎዳም፣ በብዙ ምኞትና፣ በፈተና በወጥምድም ይወድቃሉ:: ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና አንዳንዶች ይህን ስመኙ ከሃይማኖት መንገድ ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ::» (1ጢሞ. 6: 9 - 10)*

ገንዘብ ከተጠቀምንበት ታማኝ ባሪያ ሲሆን ከተገዛንለት ጨካኝ ጌታ ነው:: አንዳንድ መለኮታዊ ራእይን ይዘው የወጡ የእምነት ፋና ወጊዎች መከራን፣ ማጣትን፣ጥላቻን፣ ድህነትን፣ ስድብንና ስይጣንን ሁሉ አሸንፈው አልፈው ገንዘብ ጋ ሲደርሱ መቀነታቸው ተፈቶ መንገድ ላይ ቀርተዋል:: ገንዘብ ለራእዩ ግብዓት እንዲሆነን በራእዩ ባለቤት በእግዚአብሔር የተሰጠን አንዱ ስጦታ እንጂ እንዲገዛንና አቅጣጫችንን እንዲያመለክተን የተላከልን መሪ አይደለም:: በገንዘብ ተጠቅመን ወንጌልን እንድናደርስ እንጂ በአገልግሎት ስም ገንዘብን እንድናገለግልም ሆነ እንድንሰበስብ አልተጠራንም:: ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ለባለራእይ የመጀመሪያ ፈተና ገንዘብ ማጣት ነው:: በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያሉ አገልጋዮች ብዙ ጊዜ የሚከፈላቸው ገንዘብ ለቤት ኪራይ፣ ለልጆች ትምህርት ቤትና ለቤተሰባቸው ምግብ እንኳ በቂ አይደለም:: በዚህ ውስጥ እየኖሩ ስለ ትልቅ ራእይ ማውራት አይችሉም ባይባልም ትልቅ እምነትን ይጠይቃል::

ለነገሩ ለራሱ ባከማቸ ገንዘብ መለኮታዊ ራእይን ጀምሮ የጨረሰ ሰውም የለም:: እግዚአብሔር ራእይ ስለጠን ኪሳችንን ሳይሆን ክርስቶስን በእኛ ውስጥ አይቶ ነው:: መለኮታዊ ራእይ ከግቡ የሚደርሰው በባለራእይው መታዘዝ እንጂ በእጁ ባለው በገንዘብ አይደለም:: መለኮታዊ ራእይን በምድር ላይ ለመተግበር ገንዘብ አንድ ነገር እንጂ ሁሉ ነገር አይደለም::





እውነተኛ ራእይ ገንዘብን ያመጣል እንጂ የዓለም ገንዘብ ሁሉ አንድ ላይ ቢሰበሰብ አንድ መለኮታዊ ራእይ ሊገዛም ሆነ ሊወልድ አይችልም:: ብዙ የሀገራችን አገልጋዩች ለገንዘብ ያለን አመለካከት ጤነኛ ስላልሆነ በተለይ ብዙ ቦታ ተጠርተን ለማገልገል ጸጋውንና ዕድሉን ያገኘን ሰዎች በሰዎች የነገ ዕጣ ፈንታ ላይ አንድ አዎንታዊ እሴት ለመጨመር ሳይሆን ከአገልግሎት በኋላ የሚሰጠን ወፍራም ፖስታ ውሳኔዎቻችንን ሲገለባብጡ ይታያል:: የገንዘብን ፈተና ላላለፈ አገልጋይ ከገንዘብ የሚበልጥ ፈተና አይቀርብለትም:: የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር እንደመሆኑ መጠን በገንዘብ ፍቅር ልቡ የተነደፈ አገልጋይ ሕይወቱ በክፋት ኃይሎች ሥር የወደቀና በብዙ ሥቃይ በገዛ እጁ ራሱን እንደ ወጋ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ ተናግሮአል::

በዓለምና በቤተ ክርስቲያን ያለው የገንዘብ አመለካከት በጣም በተመሳሰለበትና አገልግሎት ሁሉ በገንዘብ በሚለካበት በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ለሰጠን ራእይ እስከ መጨረሻው መገዛት ትልቅ ድል ነው:: ባለፉት ዘመናቶች ገንዘብ ሁሉ ነገር አልነበረም:: በአሁንም ዘመን ገንዘብ ሁሉ ነገር አይደለም:: ከእንግዲህም ገንዘብ ሁሉ ነገር ሊሆን አይችልም:: ባለራእይ ለራእይው ስለተገዛ ገንዘብን የሚገዛ አቅምና ጉልበት ጌታ ይሰጠዋል:: በመለኮታዊ ራእይ ውስጥ ገንዘብ አለ እንጂ በገንዘብ ውስጥ መለኮታዊ ራእይ የለም:: ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ገንዘብ ሊያመነጭ የሚችል ዓለምን በወንጌል የመድረስ ራእይ እንጂ ዓለምን በወንጌል የማድረስ ራእይ ልያመነጭ የማይችል ገንዘብ አልሰጣቸውም:: ስለዚህ ለገንዘብ ሳይሆን ለጌታ የተዛ ሕይወት ይኑረን::

### አገልጋይ በገንዘብ ፍቅር ልቡ ሲነደፍ:-

ሀ. ያልተጠየቀውን መስዋዕት ማቅረብ ይጀምራል

ለ. ጌታን ትቶ ገንዘብን ያገለግላል

ሐ. ስጦታንና ጥሪን እንደ ሸቀጥ ለገበያ ያቀርባል

መ. እንደ ሐናንያና ሰጲራ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ይዋሻል

ሠ. ከእግዚአብሔር ጸጋ ይልቅ በቁሳቁስ መሃል ይደበቃል

ረ. ስኬቱ ባለው የገንዘብ መጠን እንደሆነ ያስባል

ከዚህ አኳያም ሊታወቅ የሚገባው ትልቁ ሚስጢር በገንዘብ ሌላውን ማገልገልና መገልገል ኃጢአት እንዳልሆነ ነው:: ለገንዘብ ብሎ ማገልገል ግን ጣኦትን እንደ ማምለክ ነው:: ትልቁ ማስተዋል፣ ሽሽት ከገንዘብ ሳይሆን ከገንዘብ ፍቅር ሊሆን ይገባል::

## 6. ዝሙት

ብዙን ጊዜ የዝሙት ኃጢአት ጤናማ ያልሆነ የተቃራኒ ጾታ ግኙኝነት ውጤት ነው:: ጤናማ ያልሆነ ጾታዊ መቀራረብ አንዱና ዕድሜ ጠገብ የባለራእይ ፈተናና እንደ ማንኛውም ሰው በልቡ የሚታገለው ብርቱ ፈተና ነው:: ለመሆኑ ታላላቅ ባለራእይዎች ለምን በዝሙት ኃጢአት እንደሚወድቁ ያውቃሉ? የመጀመሪያው ብቸኝነት ነው:: አንዳንድ ባለራእይ የሆኑ ሰዎች ብርታታቸውንና ድካማቸውን በግልጽነት የሚያካፍሉት የልብ ሰው ስለሌላቸው በሰዎች ተከበው በሰው ማጣት ይሰቃያሉ:: ለባለራእይ ሦስት ዓይነት ሰዎች ያስፈልጋሉ:: የመጀመሪያው እንደ ጳውሎስ የአባትነት ልብ ያለው ድል ሽንፈቱን የሚነግረውና በሕይወቱ ላይ ሊናገር የሚችል ሰው:: ሁለተኛ እንደ ባርናባስ የአገልግሎት አጋር ሆኖ አብሮ ተጠምዶ የሚያገለግል ሰው:: ሶስተኛው እንደ ጢሞቴዎስ ታማኝ ተማሪ ሆኖ የሚከተለውና ከእርሱ የሚማር ሰው የግድ ያስፈልገዋል::

ዶክተር ሪቻርድ ከአሥር ዓመት በላይ በአሜሪካ መጋቢዎች ላይ ያደረጉትን ጥናት ውጤት ሲገልጹ «70.3% መጋቢዎች የልብ ጓደኛ በማጣት በብቸኝነት እንደሚሰቃዩ፣ 60% በትዳራቸው ደስተኞች እንዳይደሉ 35% ከዝሙት ኃጢአት ጋር እየታገሉ ይኖራሉ»[49] ይላሉ:: የሀገራችንን አገልጋዮች በተመለከተ በጥናት የተደገፈ መረጃ ለማግኘት ባልችልም የሞራል ውድቀትና ዱሮ በሀገራችን የማይታወቅ ፍቺና ዳግም ጋብቻ በኢትዮጵያ አገልጋዮች ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ በመዛመት ላይ እንደሚገኝ የአደባባይ ምስጥር ነው:: ፈረንጆቹ ገና ሲታመሙ ሕመማቸውን የመናገር ልምድ አላቸው::

[49] *Dr. Richard J. Krejcir* some startling statistics on pastors; *FASICLD* (*Francis A. Schaeffer Institute of Church Leadership Development*). This quest started in 1989 as a *Fuller Institute* project that was picked up by *FASICLD* in 1998.





እኛ ደግሞ ሕመሙ እስኪገድለን ድረስ መታመማችንን እንኳ ስለማንቀበል ነገራችን የአደባባይ ሚስጢር ሆኖ ከመንገድ ካስወገደንና ከሞትን በኋላ እንደ አዲስ ነገር መወራት ይጀምራል:: ጌታ ይርዳን::

ሌላው ባለራእይ በዝሙት ኃጢአት እንዲወድቅ ከሚያደርጉት መካከል ዝንጉነት፣ በጊዜያዊ ስኬት መታለል፣ ትቢዕት፣ ከመጠን በላይ በራስ መደገፍ፣ ደባል ስዕብና፣ የሌሎችን ምክርና አስተያየት ቸል ማለት፣ ሁሉን አዋቂና አስተዋይ አድርጎ ራስን መቁጠር፣ ከውድቀት በላይ እንደሆነ ማሰብ፣ለማንም ተጠያቂ ያለመሆን፣ ከቤተሰብ ራእይን ማስቀደም፣ ለትዳር ጓደኛ በቂ ጊዜ ማጣት ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: አገልጋይ ብዙውን ጊዜ በሕዝብ ፊት በጣም የተመቸው፣ ሁሉን የሚያውቅ፣ ለጋስና የፍቅር ሰው ስለሚመስል አቅጣጫን፣ ምሪትና ምክርን ለብዙኋኑ ስለሚሰጥ አንዳንዴ የተቃራኒ ጾታን እይታ በተለየ ሁኔታ መሳቡ አይቀሬ ነው:: አንዳንዶች በባለራእይ አገልጋይ በንግግሩና በአገልግሎቱ ብቻ በመማረክ የተቃራኒ ጾታ ፍላጎት እንኳ እንዳለው ለማሰብ ይቸገራሉ:: ከዚህም የተነሣ በባለራእዩ ዙሪያ ካሉት ሰዎች አንዱ መሆን ልዩ ደስታና ታዋቂነትን እንደ ሚያተርፍላቸው ስለሚያስቡ በጣም ከመቅረባቸው የተነሣ ለራስና ለባለራእዩም ወጥመድ ይሆናሉ:: ከበደ በከሬ ስለዚህ ጉዳይ በመጽሐፋቸው «አገልጋይ ከውስብ ፈተና ራሱን ለመከላከል የተፈጥሮ ወይም መንፈሳዊ ክትባት አልወሰደም::»[50] በማለት ያለውን እውነት አስቀምጠዋል:: ብዙ ገንዘብ፣ የአገልግሎት በር፣ የጠራ ራእይ ሳያጡ በዝሙት ቀስት ጉልበታቸው ተወግቶ ሳይፈልጉ ከባለራእይነት መንገድ ወጥተው ተራ ሕይወት እየመሩ ያሉ ባለራእይዎችን ቤቱ ይቁጠራቸው:: ባለራእይ በተቃራኒ ጾታ በኩል የሚመጣ ፈተና ጠንካራ እንደ ሆነ ስለሚያውቅ በፍቃዱ ላይ ዕለት ዕለት ጌታን እያነገሠና ከማንኛውም አሰናካይ ሁኔታዎች በጌታ ጸጋ በመሸሽ ይኖራል:: እንደ ዮሴፍም አምላኩን ለማክበር ቆርጦ ይራመዳል:: ጌታም ይረዳዋል:: ሰይጣን ከማንኛውም ኃጢአት ይልቅ ይበልጥ በዝሙት ኃጢአት ባለራእይን ለመጣልና ለማቁሰል ይጥራል:: የዚህ ኃጢአት ልዩነት የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የሆነውን የሰውን ልብ ማርከሱ ነው (1ቆሮ6:15-18) :: የተቀደሰን ጋብቻ ያበላሻል:: (ዕብ 13:4)

[50] *ከበደ በከሬ:* *ሚዛን የጠበቀ ሕይወት እና አገልግሎት* *ራዕይ አሳታሚ አዲስ አበባ 1998 ዓ.ም ገጽ 95*

## የዝሙት ኃጢአት

- ታላቁን የእምነት አርበኛ ሳምሶንን ያዋረደ
- እንደ ልቤ የተባለውን ንጉሥ ዳዊትን ብዙ ዋጋ ያስከፈለ
- ልጁ አምኖንን በልጅነቱ የቀጨ
- ሰሎሞንን በመከረው ምክር እንዲደናቀፍና በመጨረሻም ጣኦት አምላኪ ያደረገ መርዝ መሆኑን በመረዳት ከዝሙት እንሽሽ!

## 7. ለዝናና ለሙገሳ ማገልገል

ባለራእይ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰዎች ልጆች በረከት እንጂ ለዝናና ለሙገሳ ብሎ ለማገልገል አይገለጥም። ባለራእይ በትልቁ እግዚአብሔር ዓይን ስለታየና ክብሮ ስለተሳከ በሰዎች ዘንድ ክብርን ለመፈለግ ወደታች አይወርድም። ሙገሳን የሚጠሙ መሪዎች የሰዎችን ስሜትና ሙገሳ ተለዋዋጭነት ያለመረዳት አንዱ ችግራቸው ነው። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ዝናውን ሰምተውና አይተው <u>ረቡዕ</u> «ሆሳዕና » «አሁን ቶሎ አድነን» ያሉት ከአንድ ቀን በኋላ <u>ዓርብ</u> ይሰቀል! ይሰቀል! እንዳሉ አንዘንጋ። የሰዎች ሙገሳና ዝናን መራብ የመመለክ ምኞትና ፈተና ውስጥ ይከተናል። ይህ የቀደመውን መልአክ የዛሬውን ሰይጣን ውድቀት እውን ያደረገ አደገኛ የኃጢአት ዘር ነው። የእግዚአብሔርን ክብር መሻማት ስንጀምር ውድቀት በልባችን ሊገድለን እያደባ እንደሆነ አውቀን በጠላት እጅ ሳንወድቅ በእግዚአብሔር ፊት በትልቅ ንስሐ ልንወድቅ ይገባል።

ብዙ ባለራእዮች በእግዚአብሔር ምህረትና መልካምነት ከታች ከፋንዲያ ተነሥተው ጌታ በእነርሱ አነጋጋሪ ነገር ማድረግ ሲጀምር፦ እንደ ናቡከደነፆር «ይች እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር ... የሠራኋት ታላቂቷ አይደለችምን?» (ዳን. 4: 30) ማለት ሲጀምሩ ኢካቦድ ይሆንባቸዋል። ባለራእይ እንዴውኑ በጌታ ስለከበረ በተሰጠው ራእይ ለመክበር አይታገልም። ባለራእይ እግዚአብሔር በእርሱ ሲከብር ለደስታው ወደር የለውም። ባለራእይ የእግዚአብሔርን መክበር በእያንዳንዱ እርምጃው ስለሚፈልግ እግዚአብሔርም ዕለት ዕለት ድል እየሰጠው ያራምደዋል።





ሰው ለማይታመን ሰው ሁሉን እንደማይሰጥ ሁሉ እግዚአብሔርም እርሱ ባደረገው የክብሩን ምርኮ ለመካፈል ለሚቋምጡ ብልጥ መሳይ ሰነፎች ምንም የለውም። ሙገሳና ክብር ለታይታ እንድናገለግል ያደርገናል (ማቴ 6:1)። በትልቁ እግዚአብሔር የታየ ሰው በትንሹ የሰው ዓይን ለመታየት አይታገልም።

## 8. ቅናት

ቅናት፦ *«ለባልንጀራችን በሆነው መልካም ነገር መናደድ ነው»* በማለት ዌብስተር መዝገበ ቃላት ይፈታዋል። ቅናት በውስጣችን እንዳለና እንደሌለ ለመፈተሽ ከፈለግን ጓደኞችን ወይም በታናሽነቱ የምናውቀው አንድ ሰው ድንገት ከእኛ በጣም የተሻለ ሹመት እድገት ብልጽግና ቅባት የአገልግሎትና የኑሮ ስኬት እንዳገኘ ስንመለከት የሚሰማንን ስሜት ማጤን በቂ ነው። እሉታዊ የልብ ምላሽና ዝንባሌ በውስጣችን ካለ ቅናት በውስጣችን አለ ማለት ነው። በቀልድም ሆነ በቁምነገር አንዳንድ ሰዎች ኢትዮጵያዊያን ቅናተኞች እንደሆንን ሲናገሩ እንሰማለን። ይህ የጅምላ ፍርድ ባይመቸኝም ለእርስ በርሳችን በተለይም በመንፈሳዊ ሥራ ላይ በዚህ ምድር የተሰማራን አገልጋዮች በእውነት ምን ያህል የመቀባበል ልብ አለን? የሚለውን ስመለከት ከማጠቃለያው ጋር በከፊል እስማማለሁ። ብዙ ጊዜ ኮንፈራንስ ተጋብዤ ለማገልገል ስሄድ አንዱ ጭንቀቴ ምን ልስበክ ሳይሆን ከእኔ ጋር ስለሚያገለግሉ ሰዎች ይሆናል። ምክንያቱም የኮንፈራንሱ «ዋና ሰው» ለመሆን መልዕክቱ ባልገባቸው መልዕክተኞች መካከል በሚደረግ ሩጫ የራስን ዋጋ ከፍ ለማድረግ የሌላውን መልዕክት የመናድ አካሄዶች ብዙ ጊዜ አይቼ ልቤ አዝኖአል። ይህም ለራሴ ሳይሆን ግራና ቀኙን ያልተረዳው መንጋ በቅናትና በእኔነት ተሞልተው ጢመትን በድፍረት የሚሰብኩ ሰባኪዎች ተጠቂ በመሆኑ ነው። ይህ ከቅናት ወይስ ከቅባት? የሚል ጥያቄን ሁሌ በውስጤም ይጭራል። ባለራእይ ማንም እርሱን መሆን እንደማይችል እርሱም ማንንም መሆን እንደማይችል በትክክል የተረዳ ሰው ነው። ባለራእይ የሌላው መነሣት እያስደነግጠውም። ባለው ሁሉ ሌላውን ከማገዝ ውጪ ማሰናከያን ለማኖር አይተጋም።

ለምሳሌ በከተማችን አንድ ስሟን ሰምተነው የማናውቅ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ብትተከልና ከእኛ በተሻለ ልዩ የወንጌል እንቅስቃሴዋ ከተማችንን ብታናውጥ ስንቶቻችን «እንኳን መጡ!» ብለን እግዚአብሔርን ለማመስገን የምንችለው? እውነተኛ ባለራእይ ደስታው የቤተ ክርስቲያኑን ስም፣ የቤተ እምነቱን ድንበርና የራስን ቡድን ማስጠራትና ማስፋት ሳይሆን የእግዚአብሔር ክብር በማንም ይሁን በምን ተገልጦ ማየት ነው:: በዚህ 21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እግዚአብሔር በፍጹም ባልገመትነውና ባልጠበቅነው መንገድ ኢትዮጵያዊያን ከራሳቸው አልፈው በወንጌል ለዓለም በረከት እንደሚሆኑ አምናለሁ:: አብርሃም ለኪዳን መንገድነት እስማኤልን ሲያቀርብ እግዚአብሔር አልተቀበለም::

በጊዜው ተስፋ ካልነበራት ሣራ የኪዳን ዘር ይስሐቅ እንደመጣ ሁሉ እግዚአብሔር ዛሬም እኛ ከምንገምተውና ከምንጠብቀው በተለየ መንገድ ክበሩን ይገልጣል:: እግዚአብሔር በዚህች ምድር በፈለገው መንገድ ለመገለጥ ይናገራል እንጂ ከየትኛ ውም መንግሥታዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች፣ ብሔራዊም ሆነ ክልላዊ መንፈሳዊ ቢሮዎች ማረጋገጫም /Approval/ ሆነ ፊርማ /signature/ ፈቃድ /certificate/ አይፈልግም:: አንዴ በሀገራችን እንደሆነ የሰማሁት ታሪክ ትዝ አለኝ:: የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1960ዎች ዓ.ም በተለይ በዮንቨርስቲና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መካከል መቀጣጠል በጀመረ ጊዜ በሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል አነጋጋሪ ሆኖ እንደነበር ይነገራል:: ከዚህም የተነሣ በመንግሥትም ሆነ በነባር የሃይምኖት ክፍሎች እንቅስቃሴው አይወደድም ነበር ይባላል:: የዛሬን አያድርገውና::

በእንቅስቃሴው ውስጥ የነበሩ ወጣቶች በመንግሥት የታሰሩ፤ በነባር አብያተ ክርስቲያናት የተወገዙ፣ የተሰደዱና ብዙም የተባሉ እንደነበር ታሪካቸው ያወሳል:: መንፈስ ቅዱስ ሲወርድባቸው በልዩና አዲስ ቋንቋ ይናገራሉ እንዲሁም «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» በማለት ትንቢትም ይናገራሉ ተብለው የተወሰኑ ወጣቶች ወደ አንድ በሀገር ደረጃ የሃይማኖት መሪ ተብለው ወደሚገሙቱ አባት በተሰጣቸው ወንበርና ስም እንዲመረመሩ ተብለው ሲወሰዱ እንዲህ አሏቸው ይባላል:–





*«ኢትዮጵያን በሚመለከት እኔ ለእግዚአብሔር በጣም የቀረብኩ እያለሁ በእናንተ በኩል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብሎ የሚናገረው ደግሞ የትኛው አምላክ ነው?»* ብለው ወጣቶቹን ጠየቁ ይባላል::

ዛሬም ኢትዮጵያን በሚመለከት እግዚአብሔር የሚመጣው በዚህና በዚህ ብቻ ነው ብለው የሚያስቡና የሚያስተምሩ ይኖሩ ይሆን? ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደሚባለው በየትኛውም የእርከን ደረጃ ያለን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያ የሃይማኖት መሪ የፈጸሙትን ታሪካዊ ስህተት እንደማንደግም ተስፋ አደርጋለሁ:: ጌታ ይርዳን!

## መርሆዎች

- መለኮታዊ ራእይ በመንፈሳዊ ማሕፀን ውስጥ እያለ እና ከተወለደም በኋላ ከፍተኛ ጥንቃቄና ክትትል ሊደረግለት የሚገባ ውድና መለኮታዊ ዘር ነው::
- እውነተኛ ራእይ እውቅና ባገኘበት ለውጥ ውጼታ ሳይሆን የግጼታ ነው::
- ያለፈው ታሪካችን ተስፋ ሊያስቆርጠን ሳይሆን ወደተሻለው ማስፈንጠሪያ ሊሆን ይገባል::
- መንፈሳዊ ብስለት ማለት ከባለፈው ሙላትና ጉድለት በላይ ማደግ እንጂ በባለፈው ልምድና መልካም ነገር በታች ተይዘን የአሁኑን ታላቅ የለውጥ ዕድል በከንቱ ማሳለፍ አይደለም::
- ባለራእይ አዲስ ራእይን በሚመጥንና ሊያስኬድ በሚችል አሠራር እንጂ «አሮጌው የዘላለም ነው» በማለት ለራእይው እንጂ ለዱሮ አሠራርም ሆነ የሥራ ሂደት ጥብቅና አይቆምም::
- ውድቀትን ለማሸነፍ ወድቆ በተነሣው አሁንም ሊወደቅ በሚችለው ነገር ግን በውድቀት ለመኖር በፍፁም በማይፈቅደው አዲስ ማንነት ለመግጠም ስንዘጋጅ ብቻ ነው::
- እውነተኛ ባለራእይ ደስታው የቤተክርስቲያኑን ስም፣ የቤተእምነቱን ድንበርና የራስን ቡድን ማስጠራትና ማስፋት ሳይሆን የእግዚአብሔር ክብር በማንም ይሁን በምን ተገልጦ ማየት ነው::
- በእግዚአብሔር ራእይ አንጼ የተገዛ ሕይወት በገንዘብና በዝሙት ለመገዛት እሺ አይልም::
- ሙገሳና ክብር ለታይታ እንድናገለግል ያደርገናል:: (ማቴ 6:1) በእግዚአብሔር አይን መታየቱን በትክክል የተረዳ ሰው በሰው ዘንድ ለመታየት ታች አይወርድም::





- ገንዘብ ለራእይው ግብዓት እንዲሆነን በራእይው ባለቤት በእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታ እንጂ እንዲገዛንና አቅጣጫችንን እንዲያመለክተን የተላከልን መሪ አይደለም::
- እኛ የእግዚአብሔር መንግሥት ሠራተኞች እንጂ ምን መሥራት እንዳለበትና እንዴት መሥራት እንዳለበት ለእግዚአብሔር ነጋሪዎች አይደለንም::
- እግዚአብሔር ተናግሮን ይሠራል እንጂ የእኛን የእጅ ብልጫ /Vote/ አይጠብቅም::